አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# በአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ የዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት አሳሳልና ጭብጥ ትንተና

ለኤምኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ

በ

ጌታቸው ሞገስ

ታኅሳስ፣ 2018 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# በአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ የዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት አሳሳልና ጭብጥ ትንተና

ለኤምኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ

በ

ጌታቸው ሞገስ

አማካሪ፦

አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር)

ታኅሳስ፣ 2018 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ በር

# በአማርኛ አጫጭር ልብወለዶች ውስጥ የዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት አሳሳልና ጭብጥ ትንተና

በ ጌታቸው ሞገስ

የፈተና ቦርድ አባላት

<u>የአማካሪዎች</u>

ስም ዶ/ር አየለ ፍቅሬ ፊርማ ------------ ቀን 10/4/2018

የውጭ ፈታኝ ፕ/ር አለማየሁ ወ/ማርያም ፊርማ ------------ ቀን 10/4/2018

የውስጥ ፈታኝ ዶ/ር መሐመድ ዓሊ ፊርማ ------------ ቀን 10/04/18

# ምስጋና

ከምንም በላይ ከብዙ ውጣ ውረድ ጠብቆ ለዚህ ያበቃኝን ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ፡፡ የጎበጠውን በማቃናት እንደ አባት ሆነው በመምከርና አቅጣጫም በመጠቆም እንደመምህርነታቸው የማያሰልስ ምክር በመስጠት ከጎኔ ላልተለዩኝ አማካሪዬ አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር) ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ መምህር ጌታቸው ተስፋ ኣለማየሁ ኣሰፋ፣ ይርዳኝ ዳመሳ፣ ታደሰ ትኩ፣ ሰላም ማርክስ እና ጸሐፊ ኪያ ጎሮ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በመለገስ ስለረዱኝ ኣመሰግናለሁ፡፡ መረጃ በመስጠት የቤተ መጽሐፍት ባለሙያዎች የተባበሩኝን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ባጠቃላይ ከሩቅም ከቅርብም ሆነው ሲያግዙኝ ለነበሩ ሰዎች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የተካሄደበት ዋነኛው ምክንያት በዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት አሳሳል ላይ በቂ ጥናታዊ ጽሑፎች ባለመኖራቸው ነው። ስለሆነም ይህ ጥናት በዘርፉ ያለውን የጥናታዊ ጽሑፍ ክፍተት ለመሙላት ይረዳል። ስነ ማህበረሰባዊ ሂስ ደግሞ በመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብነት አገልግሏል። ጥናቱ በአምስት የአማርኛ አጫጭር ልብ ወለዶች (“ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ፤“ “የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ፤“ “እራትና መብራት”፣ “ወይ አዲስ አበባ፤“ እና “ቦርጨቅ“) ውስጥ የዐይነ ስውራንን ገጸ-ባህሪያት ውክልና መርምሯል። ጥናቱ እነዚህ ገጸ-ባህሪያት በስነ-ጽሑፍ ውስጥ እንዴት እንደተሳሉ፣ ምን ዓይነት ማኅበራዊ ሚናዎች እንደተሰጣቸው እና በአጠቃላይ ዐይነሥውርነት እንዴት እንደቀረበ ተመልክቷል። የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት፣ ደራሲያኑ ዐይነ ሥውራንን ከማኅበራዊ ሚና አንጻር ሲስሉ፣ በአምስቱም ገጸባህሪያት ላይ የሚታይ አንድ የጋራ ጅምላ ፍረጃ (stereotype) ተገኝቷል፤ ይህም ሁሉም ገጸባህሪያት በአንድም ሆነ በሌላ ወቅት ከልመና ሕይወት ጋር መያያዛቸው ነው። በአሳሳል ቴክኒክ ረገድ በአንድ በኩል፣ አንዳንድ ገጸባህሪያት (እንደ “ታሪኩ“ እና “አሮጊቷ“)፣ ምንም ዓይነት ሰብዓዊ ግድፈት የሌላቸው፣ “ፍጹም ሰናይ“ (idealized) ተደርገው በመቅረባቸው የተአማኒነት ክፍተት መኖሩ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል፣ እንደ “ሽማግሌው“፣ “ውበቴ“ እና “በርጠሎሜዎስ“፣ እንደ ፍርሃት፣ ተንኮል፣ ሱስ፣ ጸጸትና ጥርጣሬ ያሉ ጥልቅ ሰብዓዊ ድክመቶችን ተላብሰው በመገኘታቸው፣ ከጅምላ ፍረጃ የጸዱና እጅግ ተአማኒነት ያላቸው ሆነው ተስለዋል። በጭብጥ ደረጃም፣ ደራሲያኑ ዐይነ ሥውርነትን ተጠቅመው ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን አንስተዋል፦ (1) ዐይነ ሥውርነት የሚያስከትለው ማኅበራዊ ጥገኝነት፣ ብዝበዛና መገለል፣ እና (2) “እውነተኛ ብርሃን“ ምንድን ነው? በሚለው ዙሪያ አካላዊ እይታን ከልቦና ማስተዋል ጋር የሚያነጻጽር ጥልቅ ፍልስፍናዊ ጥያቄ በሰፊው ተቃኝቷል።

## ማውጫ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ አላማ ........ 3
1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ ........ 3
1.3.2. የጥናቱ ንዑሳን አላማዎች ........ 3
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........ 3
1.5 የጥናቱ ፋይዳ ........ 3
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 የጥናቱ ዘዴ ........ 4
1.7.1 የጥናቱ ዓይነት ........ 4
1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 4
1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ ........ 5
1.8 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 5
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1. ንድፈሀሳባዊ መሠረት ........ 6
2.2. ጽንሰሐሳባዊ ማህቀፍ ........ 7
2.2.1 አካል ጉዳተኝነት ........ 7
2.2.2. ዐይነ ስውርነትና ስነጽሁፍ ........ 8
2.2.3. የገፀ ባህሪያት አሳሳል ........ 13
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 17
3. የመረጃ ትንተና ........ 20
3.1 አጽመ ታሪክ ........ 20
3.2 ታሪኩ (ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ) ........ 23
3.2.1. ገጸባህሪው ከግለወጥነት አሳሳል አንፃር ........ 23
3.2.2 ገጸባህሪው ከዘላቂነቱ አሳሳል አንፃር ........ 25
3.2.3. ገፀ ባህሪው ከኢፍጹምነት አሳሳል አንጻር ........ 27

3.3. ሽማግሌው (ራትና መብራት) ........ 29
3.3.1. ገፀ ባህሪው ከግለ ወጥነት አንፃር ........ 29
3.3.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር ........ 30
3.3.3. ገፀ ባህሪው ከኢ-ፍፁምነት አሳሳል አንፃር ........ 31
3.4. አሮጊቷ ........ 33
3.4.1. ገጸባህሪዋ ከግለወጥነት አንፃር ........ 33
3.4.2. ገጸባህሪዋ ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር ........ 34
3.4.3. ገጸ ባህሪዋ ከኢ-ፍፁምነት አሳሳል አንፃር ........ 35
3.5. ውብቴ ........ 35
3.5.1. ገፀባህሪው ከባህሪ ግለወጥነት አንፃር ........ 36
3.5.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር ........ 38
3.5.3. ገጸባህሪው ከባህሪ ኢ-ፍፁምነት አንፃር ........ 39
3.6. በርጠሎሜዎስ (የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ) ........ 40
3.6.1. ገጸባህሪው ከባህሪ ግለወጥነት አንፃር ........ 41
3.6.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ከዘላቂነት አንፃር ........ 42
3.6.3. ገጸባህሪው ከባህሪ ከኢ-ፍፁምነት አንፃር ........ 43
3.7 የዋና ገጸባህርያት ተመሳስሎ ........ 49
3.7.1 የአመለካከት/የአቋም ተመሳስሎ ........ 49
3.7.2 የትምህርት ታሪክና የሥራ መስክ ተመሳስሎ ........ 52
3.7.3 ጽናት፤ ችግር የወለደው ጽናት ተመሳስሎ ........ 54
3.7.4 ባይተዋርነት ........ 59
3.8 የአምስቱ ልቦለዶች ጭብጥ ........ 69
3.8.1 «ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ» (በተፈራ ይኄይስ) ጭብጥ ........ 69
3.8.2 «ወይ አዲስ አበባ» (በአውግቼው ተረፈ) ጭብጥ ........ 71
3.8.3 «ራትና መብራት» (በበዕውቀቱ ሥዩም) ጭብጥ ........ 73
3.8.4 «ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ» (በስብሐት ገብረ እግዚአብሔር) ጭብጥ ........ 75
3.8.5 «የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ» (በዳንኤል ታዬ) ጭብጥ ........ 76
4. ማጠቃለያ ........ 78
ዋቢ ጽሁፎች ........ 85

# 1. መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ ፋይዳ፣ ወሰን፣ ዘዴ እና አደረጃጀትን ይዟል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሥነጽሑፍ ሥራዎች የገሀዱ አለም ነጸብራቅ ናቸው። በዙሪያችን ያለውን ዓለም፣ የሰዎችን ባህሪና አኗኗር ያሳዩናል። በአማርኛ ልብ ወለድ ውስጥ የተለያዩ ሰዎችን ታሪክ እናነባለን። ነገር ግን አንዳንድ የኅብረተሰባችን ክፍሎች በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ብዙም አይታዩም። ለምሳሌ ያህል አካል ጉዳተኞችን፣ በተለይም ዐይነ ስውራንን በስፋት አናገኝም።

በሀገራችን ዐውድ ዐይነ ስውራን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የህብረተሰብ ክፍል ነው (እንደ ኢትዮጵያ ጤና እድገት መጽሔት ዘገባ ከ1.6 እስከ 1.8 ሚሊዮን ዐይነ ስውራን እንዳሉ ይገመታል።) ይሁን እንጂ ይህ የህብረተሰብ ክፍል በሀገራችን ስነጽሁፍ ውስጥ ተገቢውን ያህል ትኩረት አላገኘም። ለመመረቂያ ጽሁፌ ርዕስ በማፈላልግበት ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የታተሙ ጥናታዊ ጽሁፎችን ስቃኝ፣ በተለይ በዐይነ ስውራን ገጸባህርያት አሳሳል ላይ የተሰሩ ጥናቶችን አላገኘሁም። ይህም በጉዳዩ ላይ ቢጠና በዘርፉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በተወሰኑ የልብወለድ ሥራዎች ውስጥ ዐይነ ስውራን ገጸባህርያትን ብናገኝም፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚሳሉበት መንገድ አድሎአዊ አመለካከት (stereotype) ነው። ብዙ ደራሲያን ዐይነ ስውራንን ከረጂነትና ተረጂነት የዘለለ ሚና አይሰጧቸውም፤ አሳዛኝ፣ ረዳት የለሽና ጥገኛ ብቻ አድርገው ያቀርቧቸዋል።

ይህ ጥናት፣ ዐይነ ስውራን ከዚህ የተዛባ አመለካከት ውጭ በልብወለድ ውስጥ ሲቀርቡ፣ እንደማንኛውም ገጸባህሪያት ሊኖራቸው የሚገባቸውን መሠረታዊ የገጸባህሪይ አሳሳል መርሆች (የባህሪ ዘላቂነት፣ ግለ ወጥነትና ኢ-ፍጹምነት) ያሟሉ መሆን አለመሆናቸውን ይመረምራል።

አካል ጉዳተኞች በየሚኖሩበት የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የየራሳቸው ሚናና ተሳትፎ አላቸው። በልብወለድ ውስጥ ሲሳሉም ይሄንን ተጨባጭ እውነታ ግምት ውስጥ ባስገባ

መልኩ መሆን አለበት:: በዚህ የምረቃ መርሀ ግብር "prose fiction" እና "Amharic Novel" የሚባሉ ኮርሶችን ስንወስድ ስለ ገጸባህርያት አሳሳል ተምረናል:: ማንኛውም ዓይነት ገጸባህርይ በምንቀርጽበት ወቅት መረሳት የሌለባቸው ሦስት ቁምነገሮች አሉ:: እኒህም ቁምነገሮች የባህሪ ዘላቂነት፣ ግለ ወጥነትና ኢ-ፍጹምነት ናቸው:: ዐይነ ስውራንም ከዐይነ ስውርነታቸው በስተቀር ከዐይናማ ገጸባህርያት የሚለዩበት ምንም ነገር ስለሌለ በልብወለድ ውስጥ ሲቀርቡ ህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ነባራዊ እውነታ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት::

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደ ጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ይቆጠራሉ::

1. በልብወለዶቻችን ውስጥ ዐይነ ስውራን ገፀባህርያት እንዴት ተስለዋል የሚለውን ለመመርመር ከመነጨ ፍላጎት፣

አካል ጉዳተኝነት የህይወት አንዱ ገጽታ እንደመሆኑ መጠን በልብወለድ ውስጥ በዋና ርዕሰ ጉዳይነት የሚነሳበት ልዩ ልዩ አጋጣሚ አለ:: ስለ አካል ጉዳተኝነት ሲነሳ ደግሞ አካል ጉዳተኞች አብረው ይነሳሉ:: ለዚህ ጥናት መካሄድ ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ‘prose fiction’ በሚል ርዕስ የወሰድኩት ኮርስ እንደ አነሳሽ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል::

2. በአካል ጉዳተኛ ገፀባህርያት አሳሳል ዙሪያ የተደረጉ በቂ ጥናት አለመኖር፣

ከላይ በዳራው ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋነኛ ትኩረት አካል ጉዳተኞች ሲሆኑ በማህበረሰብ ውስጥ  ቁጥር ቢኖራቸውም በልብወለዱ ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት አግኝተዋል ብዬ አላምንም::

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማጥናት ከመወሰኔ በፊት በዩኒቨርስቲው ውስጥ በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በቂ ጥናታዊ ጽሁፎች መኖር አለመኖራቸውን ለመቃኘት ሞክሬ ነበር:: ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር ሲታይ ይሄ ዘርፍ እምብዛም ያልተጠናበት በመሆኑ፣ ቢጠናበት በዘርፉ ያለውን ክፍተት ከመሙላት ረገድ የራሱ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ::

## 1.3. የጥናቱ አላማ

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና አላማ በተመረጡ 5 አጫጭር ልብወለዶች ውስጥ የዐይነ ስውራንን ገጸ ባህርያት አሳሳልና ጭብጥ መተንተንና የተገኘውን ውጤት ማሳየት ነው።

### 1.3.2. የጥናቱ ንዑሳን አላማዎች

1. ከግለወጥነት አንጻር ገጸባህሪያቱ እንዴት ተስለዋል የሚለውን መገምገም፣
2. ከባህሪ አንጻር ገጸባህሪያቱ እንዴት ተስለዋል የሚለውን መገምገም፣
3. ከኢ-ፍጹምነት አንጻር ገጸባህሪያቱ እንዴት ተስለዋል የሚለውን መገምገም፣

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

1. ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት በገጸባህርያት አሳሳል ወቅት መዘንጋት ከሌለባቸው ቁምነገሮች፦ የባህሪ ዘላቂነት፣ ኢ-ፍጹምነትና ግለወጥነት አንጻር እንዴት ተስለዋል?
2. በዓይነ ሥውራን ገጸባህሪያቱ መካከል የተስተዋለ ተመሳስሎ አለ ወይ?
3. በገጸባህሪያቱ አሳሳል ወቅት የተስተዋሉ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ምን ምን ናቸው?

## 1.5 የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት ሲያልቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ፋይዳዎችን ያስገኛል፦

1. በዐይነ ስውራንና በዐይነ ስውርነት ገጸባህሪያት አሳሳል ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በመስኩ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።
2. በተመሳሳይ ዘርፍ ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ አጥኚዎች ርዕስ ያስገኛል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በተመረጡ 5 የአጫጭር ልብወለድ መድበሎች ውስጥ የዐይነ ስውራን ገፀባህርያትን አሳሳል የሚገመግም ሲሆን በህትመት ጊዜ ቅደም ተከተል ሲቀርቡ፤ ከተፈራ ይኼይስ **"ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ"** (1960 ዓ.ም.) ራሱ «ምራኝና ልሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ»፣ ከአውግቼው ተረፈ **ወይ አዲስ አበባ** (2011 ዓ.ም.) ራሱ **«ወይ አዲስ አበባ»**፣ ከበዕውቀቱ ሥዩም በራሪ ቅጠሎች (1995 ዓ.ም.) «እራትና መብራት»፣ ከስብሀት ገብረ እግዚአብሔር **ቦርጨቅ** (2003 **ዓ.ም**.) «ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ»፣ ከዳንዔል ታዬ **ቅዡት** (2007 **ዓ.ም**.) «የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ» ተመርጠዋል:: ትንተናው በዐይነ ስውራን ገፀባህርያት አሳሳል ዙሪያ ብቻ የሚያተኩር ይሆናል:: እነዚህ ልቦለዶች የተመረጡበት ብቸኛው ምክንያት አምስቱም ልቦለዶች በዐይነ ሥውርነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑና ዐይነ ሥውራን ገጸባህሪያትን በዋና ገጸባህሪያትነት የያዙ ልቦለዶች በመሆናቸው ነው::

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

ወደ ዋናው የጥናታዊ ጽሁፉ ክፍል ከመግባታችን በፊት የጥናቱን አካሄድ በተመለከተ ወጥና መደበኛ የሆነ ቅርጽ መስጠት (framework of the research project) እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ምን አይነት መረጃዎች መሰብሰብ እንዳለባቸውና መሰብሰብ እንደሌለባቸው መመሪያ በመስጠት የጥናቱን ሂደት ያሳልጣል::

### 1.7.1 የጥናቱ ዓይነት

የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ ነው:: ይህ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት የገጸባህሪያት አሳሳል ትንተናን ለማካሄድ አመቺ ዘዴ በመሆኑ ነው::

### 1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ጥናቱ ለመረጃ መሰብሰብያነት ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ መዛግብት ፍተሻና ንባብን ተጠቅሟል:: ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት መረጃዎቹ የሚገኙት አንድም ጥናቱ በተካሄደባቸው አጫጭር ልብወለዶች፣ አንድም ከጥናት ምርምር፣ ከንድፈ ሐሳብና ተዛማጅ ጽሁፎች ላይ ጥልቅ ዳሰሳ በማድረግ ስለሆነ ነው::

### 1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ

ለጥናታዊ ጽሁፉ እንደ መረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ የሚያገለግለው ደግሞ ሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሀሳብ ነው። ሥነ ማኅበረሰባዊ የአንድን ማህበረሰብ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁናቴ አጉልቶ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው። የሥነ ማኅበረሰባዊ ትኩረት ማህበረሰቡ ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ የማህበረሰቡ አንድ ክፍል የሆኑት ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት ከሚኖሩበት ማህበረሰብ አንጻር እንዴት ተስለዋል የሚለውን የሚመረምር በመሆኑ ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ መረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብነት ተመርጧል።

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በአራት ምእራፎች ተደራጅቷል። ምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ እና የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉ ክፍሎችን ይዟል። ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳድርሳን የተካሄደበት፣ ከጥናታዊ ጽሁፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የንድፈሐሳባዊ መሠረት፣ ጽንሰሐሳባዊ ማህቀፍና የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳን አጠቃሎ የያዘው ክፍል ነው። ምዕራፍ ሦስት ላይ ደግሞ የመረጃ ትንተናን ተካሂዷል። ምዕራፍ አራት ላይ ደግሞ የጥናታዊ ጽሁፉ ማጠቃለያ ቀርቧል።

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ንድፈ-ሐሳባዊ መሠረት፣ ጽንሰ ሀሳባዊ ማሕቀፍና ከጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ዳሰሳ ቀርበዋል።

### 2.1. ንድፈ-ሀሳባዊ መሠረት

የሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ (Sociological Literary Theory) የአንድን ሥነ ጽሑፍ ሥራ ከሚገኝበት ማኅበራዊ አውድ ጋር በማያያዝ የሚያጠና ዘርፍ ነው። ይህ ንድፈ ሐሳብ፣ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የገሀዱ ማኅበረሰብ ነጸብራቅ እንደሆኑና በማኅበረሰቡ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎች እንደሚቀረጹ ይገልጻል። የሥነ ጽሑፍ ሥራን ለመረዳት፣ የጸሐፊውን ዘመን፣ የማኅበረሰቡን እሴቶች፣ ግጭቶች፣ እምነቶች እና የሥልጣን ተዋረድ መረዳት ወሳኝ እንደሆነ ኤገልተን ይገልጻል (Eagleton, 1976)።

ይህ ንድፈ ሐሳብ ሥነ ጽሑፍ የማኅበረሰብ ውጤት ብቻ ሳይሆን፣ ማኅበረሰብን የመቅረጽና ተጽዕኖ የማድረግ ኃይልም እንዳለው ያሰምርበታል። ካርል ማርክስ እና የማርክሲስት ሥነ ጽሑፍ ሂስ ደግሞ ሥነ ጽሑፍ በዋነኛነት ኢኮኖሚያዊ መሰረትን የሚያንፀባርቅ ልዕለ-መዋቅር እንደሆነ ያስቀምጣሉ (Marx and Engels, 1846)። በዚህ እይታ፣ ጽሑፎች በውስጣቸው ያለውን የመደብ ትግል፣ የሥልጣን ግንኙነት እና የኢኮኖሚ አፈጣጠር እንዴት እንደሚያሳዩ ይመረምራሉ። የሀንጋሪው ምሁር ጆርጅ ሉካች (Georg Lukács) ደግሞ ሥነ ጽሑፍ የማኅበራዊ እውነታን በትክክል በማንፀባረቅ የገሀዱን ዓለም ውስብስብነት ማሳየት አለበት ሲሉ ተከራክረዋል። እርሱ እንደሚለው፣ ታላላቅ ልቦለዶች የማኅበረሰቡን ተጨባጭ ሁኔታ በሕያው ገጸባህርያትና እውነተኛ ትግሎች አማካኝነት ይገልጻሉ (Lukács, 1971)።

ሌሎች ምሁራን እንደ ሬይመንድ ዊሊያምስ (Raymond Williams)፣ ሥነ ጽሑፍን እንደ ተለዋዋጭ ማኅበራዊ ሂደት (social process) የሚመለከቱ ሲሆን፣ ጸሐፊው በማኅበራዊ ታሪካዊ አውድ ውስጥ ሆኖ እንዴት ሥነ ጽሑፍን እንደሚፈጥርና የራሱንም አስተዋጽዖ እንደሚያደርግ ያብራራል። ዊሊያምስ ባህል የማኅበረሰብን አኗኗርና ልምድ የሚገልጽ እንጂ የማይንቀሳቀስ አካል አለመሆኑን በማሳየት፣ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የማኅበረሰባዊ ለውጦችን የሚያሳዩበትን መንገድ ይዳስሳሉ (Williams, 1977)። በዘመናዊው ሥነ ማኅበረሰባዊ ትችት ውስጥ፣ ሥነ ጽሑፍ ማኅበራዊ ማንነት

(social identity)፣ መገለል (marginalization)፣ የጾታ ግንኙነት (gender relations) እና የዘር ልዩነትን (racial differences) እንዴት እንደሚያንፀባርቅና እንደሚተች ይመረምራል።

ይህ ሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት በመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሐሳብነት አገልግሏል። ዐይነ ስውራን በማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን ቦታ፣ ሚና፣ ተግዳሮቶችና የሌሎች ሰዎችን አመለካከት በተመለከተ የሚቀርቡትን መስተጋብሮች ለመተንተን ይህ ንድፈ ሐሳብ ወሳኝ ነው። የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የገሀዱን ዓለም ነጸብራቅ እንደመሆናቸው መጠን፣ በአጫጭር ልቦለዶቹ ውስጥ ያሉት ዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት አሳሳል፣ የማኅበረሰባችንን ስለ ዐይነ ስውርነት ያለውን ግንዛቤ፣ አስተሳሰብ፣ አድሏዊ አመለካከቶች (stereotypes) እና ተጨባጭ ሁኔታን ያሳያል። የዐይነ ስውራን ገጸባህሪያትን ከግለ ወጥነት፣ ከባህሪ ዘላቂነትና ከኢ-ፍጹምነት አንጻር መገምገም የሚያስፈልግ ከሆነ፣ እነዚህ ባህርያት በማኅበራዊ አውዳቸው እንዴት እንደተቀረጹ የሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ በመጠቀም መመርመር ይቻላል። ለምሳሌ፣ ጸሐፊዎቹ ዐይነ ስውራንን እንደ ረጂና ተረጂ ብቻ አድርገው የሚያቀርቡ ከሆነ፣ ይህ በዐይነ ስውራን ላይ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከት የሚያንፀባርቅ ይሆናል። ይህ ንድፈ ሐሳብ፣ የዐይነ ስውራን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ፣ የታሪክ እይታዎች እንዲሁም የፖለቲካዊ ውክልናቸው በልቦለዶቹ ውስጥ እንዴት እንደተንፀባረቁ ለመተንተን ይረዳል። የዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት ትግል፣ ተስፋ፣ መገለል ወይም ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ከሰፊው ማኅበራዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ዳራ አንጻር በጥልቀት ለመመርመር ያስችላል። ለጥናቱ መረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብነት የሚያገለግለው ሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሀሳብ ነው። ሥነ ማኅበረሰባዊ የአንድን ማህበረሰብ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁናቴ አጉልቶ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው። የሥነ ማኅበረሰባዊ ትኩረት ማህበረሰቡ ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ የማህበረሰቡ አንድ ክፍል የሆኑት ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት ከሚኖሩበት ማህበረሰብ አንጻር እንዴት ተስለዋል የሚለውን ይመረምራል።

## 2.2. ጽንሰሐሳባዊ ማህቀፍ

### 2.2.1 አካል ጉዳተኝነት

የአንድ አካል አገልግሎት መስጠት አለመቻል ወይም የአበቃቀል ችግር ወይም ልዩ ልዩ የእለት ተእለት ተግባራትን ለመከወን መቸገር አካል ጉዳት ይሰኛል። Disability is a

condition of body or mind or impairment that makes it more difficult for the person to do certain activities or activity limitations and interfere with participation restrictions. [አካል ጉዳተኝነት የአካል ወይም የአእምሮ ውስንነት ሲሆን አንድን ሰው ከተወሰኑ ተግባራት ወይም እንቅስቃሴዎች ይወስናል።] (Lijalem, Yosef, Tadele, Eyob 2022. p.2) አካል ጉዳተኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ በስነ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ450 ዓ.ዓ. ገደማ በሶፎለስ ኦዲፐስ ሥራ እንደሆነ ይታመናል። ከዚያ ጊዜ አንስቶ አካል ጉዳተኝነት በስነ ጽሁፍ፣ በአፈታሪክ፣ በታሪክ መዛግብትና በመንፈሳዊ ሰነዶች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። በየዘመኑ የተነሱ ከያኒያንም አካል ጉዳተኞችን በተለያዩ ሥራዎቻቸው ውስጥ ሲያሳትፏቸው ኑረዋል።

## 2.2.2. ዐይነ ስውርነትና ስነጽሁፍ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ተቋም ያዘጋጀው የዐማርኛ መዝገበ ቃላት አይነ ስውር እና እውርን እንዲህ ይተረጉመዋል፦

"አይነ ስውር (የቃል ክፍሉ፦ ስም) አይኑ ለማየት የማይችል፤ እውር።" (ገፅ 336)

እውር (የቃል ክፍሉ፦ ቅጽል) 1. አይኑ የጠፋ፣ ማየት የማይችል፣ አይነ ስውር። 2. (ስድብ፣ ዘይቤ) ደንባራ፥ ጠምባራ። (ገፅ 330)

ዐይነ ስውርነት በተለያዩ ሰው ሰራሽ እንዲሁም የተፈጥሮ አደጋዎች፣ በዘረመል አወቃቀርና በተለያዩ የውስጥ ደዌ ሕመሞች አማካኝነት የሚከሰት ማየት ያለመቻል ችግር ሲሆን እ.ኤ.አ በመጋቢት 2023 ዓ.ም. የአለም ጤና ድርጅት (WHO) ባወጣው ሪፖርት መሠረት በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙሪያ 43 ሚሊዮን የሚጠጉ አይነ ስውራንና 270 ሚሊዮን የሚደርሱ ከፊል የእይታ ችግር ያለባቸው ሰዎች እንዳሉ ይታመናል።

እንደ አለም ጤና ድርጅት ዝርዝር ዘገባ ዐይነ ስውርነት (blindness) አራት ልዩ ልዩ ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው partial blindness ወይም ከፊል አይነ ስውርነት የሚባለው ሲሆን በከፊል ብቻ የሚያዩ ሰዎችን ይመለከታል። ሁለተኛው ደግሞ complete blindness ወይም ሙሉ በሙሉ ማየት አለመቻል የሚባለው ነው። ይሄ ችግር ያለበት ሰው ምንም አይነት ብርሃን መለየት አይችልም። ይሄ አይነቱ አይነ ስውርነት እምብዛም አይከሰትም ይባላል። ሦስተኛው legal blindness ነው። የ'ሊጋል ብላይንድነስ' ችግር

ያለባቸው ሰዎች በእድሜ መግፋት ሊሆን ይችላል ወይም በተመሳሳይ የጤና እክል የማየት አቅማቸው ከአይናማዎች ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም አነስተኛ ሲሆን ለእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች ባይቸገሩም፣ መኪና መንዳት ወይም ማንበብ የመሳሰሉ ጥንቃቄና ትኩረት የሚጠይቁ ተግባራትን መፈጸም የማይችሉ ሰዎች ናቸው፡፡ አራተኛውና የመጨረሻው congenital blindness ወይም አብሮ የሚወለድ የእይታ ችግር ነው፡፡ ይሄ በእጅጉ የተለመደው የእይታ ችግር ሲሆን ከቤተሰብ ወይም በዘረመል(DNA) አወቃቀር መዛባት አማካኝነት የሚፈጠር የእይታ ችግር ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ የሚጠኑት ገጸባህርያት ሙሉ በሙሉ የማየት ችግር (complete blindness) እና አብሮ የሚወለድ የእይታ ችግር (congenital blindness) ያለባቸው ገጸባህርያት ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ደራሲያን አካል ጉዳተኛ ገጸባህርያትን መሳል ከጀመሩ ሁለት ሺህ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት ልክ እንደ አይናማ ገጸባህርያት በስነጽሁፍ ውስጥ ተገቢው ቦታ ተሰጥቷቸዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሞንቤክ (1973፣ 25) በዐይነ ስውራን ገጸባህርያት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ካደረገ በኋላ በልብወለድ፣ በአፈታሪክ፣ በመንፈሳዊ ሰነዶች፣ በታሪክ መዛግብትና ተውኔትና በመሳሰሉት የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ያያቸውን ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት በተለያዩ አስራ አምስት ክፍሎች ይመድባቸዋል፡፡ ማለትም በየትኛውም የኪነጥበብ ሥራ ውስጥ የተካተቱ ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ዝርዝር ውጭ ሊሆኑ እንደማይችሉ ይደመድማል፡፡

1. ርህራሄና አዘኔታ የሚገባቸው (Deserving of pity and sympathy)

2. መከረኞች (miserable)፦ እንግልትና መከራ የሚበዛባቸው፣

3. በጨለማ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ (in a world of darkness)፦ ይህ ሲባል “literally and figuratively“ ሊሆን ይችላል፡፡ በጽንሰሀሳብም በገሀድም እንደማለት፡፡

4. ረዳት የለሾች (helpless)

5. ቂሎች (fools)

6. ረብ የለሾች (useless)

7. የኔ ቢጤዎች (Beggars)

8. “ማድረግ የሚችሉ” (Able to function)፦ ማድረግ የሚችሉ ሲባል፣ ብዙ ጊዜ የሚሳሉት ዐይነስውራን ማድረግ አይችሉም ተብሎ የሚታመነውን ነገር እንደሚችሉ ተደርገው ነው ለማለት ነው። ለምሳሌ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ያለ መሪ ይወጣሉ፣ የብር ኖት ይለያሉ፣ ያነብባሉ ይጽፋሉ፣ የሰዎችን አጸፋ (Reaction) ይረዳሉ፣ ራሳቸው ይለብሳሉ፣ ወዘተ. እኒህና መሰል ድርጊቶች በተወሰኑ ዐይነ ስውራን ዘንድ ብቻ የሚቻሉ እንጂ ሁሉም ዐይነ ስውራን በቀላሉ የሚያደርጓቸው አይደሉም።

9. ዐይነ ስውር ቢሆኑም በሌላ ተሰጥዖ የተካሱ (Compensated for their lacks of sight)

10. ላለፈ ሀጥያት ወይም እርግማን የሚቀጡ (Being punished for some past sin)

11. የሚፈሩና የሚገለሉ (To be feared, avoided, and rejected)

12. ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር የማይስማሙ (Maladjusted)

13. ሞራለቢሶችና እኩያን (Immoral & evil)

14. ከዐይናማዎቹ የተሻሉ (Better than sighted people (idealized))

15. ድብቆች (Mysterious)

ሞንቤክ ደራሲያን አካል ጉዳተኞች ላይ ከሚለጥፉባቸው ማንነቶች ውስጥ ልመና አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ይገልጻል። አንዳንዴ ርህራሄና አዘኔታ የሚገባቸው (Deserving of pity and sympathy) ረዳት የለሾች (helpless) ሌላ ጊዜ ስለራሳቸው ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ከዐይናማዎቹ የተሻሉ (Better than sighted people (idealized)) አድርገው ያቀረቧቸዋል። እኒህ ሁሉ ማንነቶች እውነት ቢሆኑም እንኳ አንዳንዴ ግነት ይበዛባቸውና ከገሀዱ ዓለም እውነታ ጋር ሚጣረስ ምስላ ማየት የተለመደ ነው። ለአብነትም የታሪኩና የምንተስኖትን የአትክልተኝነት፣ የቀለም ቀቢነትና የመካኒክነት ስራዎችን እንደ አብነት መጥቀስ እንችላለን። ከሞላ ጎደል ግን በዓይነ ስውራን ገጸባህርያት የሥራ መስክ ላይ የሆነ ቅርርብ አለ።

ይሄ የሞንቤኮ ድምዳሜ ደግሞ ከያኒያን በዐይነ ስውራንና በዐይነ ስውርነት ዙሪያ ስላላቸው የተዛባ አመለካከት የተወሰነ ነገር ይነግረናል። አሊስ (2016፣ 96) ይሄንን ሀሳብ በመደገፍ እንዲህ ትላለች፦ Scholars points out, in many literary texts and everyday contexts blindness is “devalued metaphor“ (Alice 2016, p.96) በርካታ ምሁራን እንደሚገልጹት ከያኒያን ዐይነ ስውርነትን የዝቅተኝነት መንገሪያ (Devalued metaphor)

አድርገው ይጠቀሙበታል። አሊስ (2016፣ 91-6) ትቀጥልና አይናማ ተኮር የሆኑት የነገረ-እውቀት የፈጠራ ሥራዎች ማየትንና ብርሃንን ከአብሮሆትና ከማስተዋል ጋር ሲያያይዙት ዓለማየትንና ዐይነ ስውርነትን ደግሞ ከማይምነትና ከድንቁርና ጋር እንደሚያያይዙት ትገልጻለች፦ Blindness becomes linked into uncertainty, to a state of not knowing, and a lack of clarity or rationality. ...Sight-Centered epistemologies are embedded in literary critical language that "focus on" or "illuminates" a text and seeks critical enlightenment and insight. (Alice 2016, p.91-6) ክሊናርድ (2008፣ 384) ከያኒያን ዐይነ ስውራን ገጸባህርያትን በመሳል ረገድ ስላላቸው የተዛባ አመለካከት እንዲህ ይላል፦ Today's stereotypes about the blind promote mainly a negative image, which reinforces the social stigma of blindness. At the center of stereotypes are the expectations that the blind people are helpless, docile, dependent, and melancholical. (Clinard, 2008. p 384) ዛሬ ዛሬ የተለመደው 'እስቴርዮታይፕ' የዐይነ ስውርነትን መጥፎ ገጽታ ብቻ የሚያንጸባርቅና የዐይነ ስውርነትን ስም የሚያጎድፍ ሲሆን ከያኒያኑ ዐይነ ስውራን ገፀባህርያትን የሚያቀርቡልን አሳዛኝ፣ ረዳት የለሽ፣ ጥገኛና ታዛዥ ብቻ አድርገው ነው።

ሌላኛው ደግሞ ማመሳሰል (stereotypes) ነው። 'ስቴሪዮታይፕስ' ስንል ደራሲያኑ ገፀባህርያቱን በመሳል ረገድ በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ከሚታመነው (Collective thinking) ባሻገር ማየት ሳይችሉ ሲቀሩ ነው። ለአብነት ያህል ሁሉንም ዐይነ ስውራን ድምጸ መልካም አድርጎ መውሰድ እጅግ የተለመደ እሳቤ ነው። ካትሪን ይሄንን ሀሳብ ደግፋ እንዲህ ትላለች፦ Historically, disabled people have been discriminated against, stigmatized, and oppressed in literature for as long as the printing press existed. <u>These characterization acted as mirrors of how society at large viewed disability.</u> (Catherine, 2020, p.50) (ሰረዝ የእኔ) የህትመት መሣሪያ ከተፈለሰፈበት ጊዜ ጀምሮ ዐይነ ስውራን ዝቅ ዝቅ ሲደረጉ፣ መጥፎ ስም ሲሰጣቸው እንዲሁም ሲጨቆኑ ኖረዋል። ዐይነ ስውርነትም ከጭብጥ መንገሪያነት በዘለለ የረባ ሚና ሲሰጠው አይስተዋልም። ይሄ የሆነው ደግሞ ደራሲያን ለዐይነ ስውርነት ባላቸው የተዛባ አመለካከት የተነሳ ነው። ይሄ የተዛባ የደራሲያን አመለካከት ደግሞ ደራሲያኑ ከራሳቸው ያፈለቁት ሳይሆን ከፈለቁበት ማህበረሰብ የቀዱት ነው። (ሰረዙን ይመለከቷል።) ጥናሰው

ይሄንን ሀሳብ በመደገፍ እንዲህ ትላለች፦ The hardest burden to bear for the person with the disability is not merely the disability itself but the stereotypes and the negative attitudes society attaches to disability. (Tirusew 1994, p.1) ለአካል ጉዳተኞች ትልቁ ፈተና ራሱ አካል ጉዳቱ ሳይሆን አካል ጉዳተኝነት በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው የተዛባ አመለካከት ነው። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ያለው የተዛባ አመለካከት በከያኒያኑ ሥራ ላይ መንጸባረቁ አይቀርም። ስነ ጽሁፋችን ውስጥ ግን ይሄን እምብዛም አንመለከትም። ዐይነ ስውራን፣ ከዐይነ ስውርነታቸው ባሻገር የልብወለድ መሪ ገጸ ባህሪ መሆን፣ ታሪክን መምራት፣ ጀብዱ መፈጸም እንዲሁም የጽናትና የአይበገሬነት ተምሳሌት መሆን ይችላሉ።

የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ እንደመሆኑ መጠን የእርስበርስ መስተጋብርና አብሮ መኖር የሕልውናው መሠረት ናቸው። አብሮ መኖርና መስተጋብር ስንል ታድያ ራስን በራስ ከማስተዳደር አንስቶ በማህበረሰብ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና እስከ መወጣት ድረስ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው። ታድያ አካል ጉዳተኞች የማህበረሰብ አንድ አካል እንደመሆናቸው መጠን በአንድ ማህበረሰብ እድገትና ለውጥ ላይ የራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል።

ቆየት ባለው ጊዜ ግን ለአካል ጉዳተኞች ይሰጥ የነበረው ቦታ እምብዛም ነበር። ይሄ ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ከመጋፋት ባሻገር በማህበረሰቡ ውስጥ፣ ከተራው ማህበረሰብ ዝቅ ያለ ሕይወት እንዲመሩ አስገድዷቸው ኖሯል። አካል ጉዳተኝነትን በሚመለከት የግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹና ሰባዎቹ ገደማ እንደሆነ ይታመናል። ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላላቅ ክስተቶች ውስጥ ሁለተኛው የአለም ጦርነት የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። ከአምሳ ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው ጦርነት ሲጠናቀቅ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወታደሮችን አካል ጉዳተኛ አድርጎ አልፏል። ታድያ እኒህ ወታደሮች ከጦርነት ሲመለሱ እንደማንኛውም ዜጋ ደፋ ቀና ብለው ቤተሰባቸውን የሚያግዙበትና ሕይወታቸውን የሚለውጡበት እድል አልነበራቸውም። ሕይወታቸውን የሚመሩት ከመንግሥት በሚያገኙት ድጎማ ብቻ ነበር። ይህ ሁኔታ ታድያ ዘላቂ ዋስትና ሊሰጣቸው አልቻለም። አካል ጉዳተኞች ጎዳና ወጥተው ተቃውሟቸውን ማሰማት የጀመሩት ከዚህ በኋላ ነው ይባላል። በመንግሥት ደረጃም ለአካል ጉዳተኞች ሰፊ እቅድ ተነድፎ እንቅስቃሴ የተጀመረው ከዚህ በኋላ ነው። ይህንን የወታደሮችን ፈለግ በመከተል በርካታ የዘመኑ ጸሐፊያን አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ በማህበረሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ እንግሊዛዊውን ሀንት መጥቀስ

ይቻላል፡፡ (Hunt 146) (Alice, 2016 p.3) እ.ኤ.አ አቆጣጠር በ1966 ዓ.ም ሀንት የሚባል ሰው «stigma: the experience of disability» የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ አወጣ፡፡ መጽሐፉ፣ አካል ጉዳተኞች ስለሚደርስባቸው ፈተናና ጫና ያትታል፡፡ ሀንት ይህንን ችግር ለመቅረፍ ጉዳዩን ወደ ማህበረሰቡ ማምጣት ዋነኛው መፍትሔ እንደሆነ ያምናል፡፡ አካል ጉዳተኞች የሚደርስባቸውን ፈተናና ጫና በተመለከተ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ መፍትሔውን ለማፈላለግ ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የሚደርስባቸው ጫና የሚመነጨው ከማህበረሰቡ እንደመሆኑ መጠን፣ ማህበረሰቡ ችግሩን ካወቀላቸው አካላዊ ጉድለታቸውን ብቻ ተመልክቶ እንዳይገምታቸው ይሆናል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎቹ ዋና ዓላማም አካል ጉዳተኞች ከጥገኝነትና ከተረጂነት ወጥተው ሥራ ሰርተው፣ ሀብት አፍርተው፣ ቤተሰብ መስርተው እንደማንኛውም ዜጋ ነጻነት የተሞላበት ሕይወት ለመምራት ይችሉ እድሉን ማመቻቸት ነው፡፡

## 2.2.3. የገፀ ባህሪያት አሳሳል

ከልብወለድ አለባዉያን መካከል አንዱ የሆነውን የገጸባህርያት ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች የየራሳቸውን ብያኔ ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ለአብነት ዘሪሁን (2002፣160) የገጸባህርያትን ምንነት በተመለከተ እንዲህ ይላል፦

> ገፀባህሪያት በልብወለድ ዓለም ስጋ ለብሰው፣ ባህሪ ተጎናጽፈው፣ መጠሪያ ተሰጥቷቸው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው፣ የሚንቀሳቀሱ፣ የሚተነፍሱ፣ የሚናገሩ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ እንደእውኑ አለም ሰዎች የሚኖሩ የሚሞቱ፣ የሚርባቸው የሚጠማቸው፣ የሚፋቀሩ የሚጣሉ፣ የሚደሰቱና የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው፡፡

ጌታቸው (2004፣ 138) ደግሞ ይህንን ሀሳብ ደግፎ እንዲህ ይላል፤ "ገጸባህሪያት ደራሲው በፈጠረው መቼት ውስጥ እየተንቀሳቀሱ የልብወለዱን ታሪክ የሚከውኑ የደራሲው የአዕምሮ ፍጡራን ናቸው፡፡ የእያንዳንዶቹ ህይወት የተቀረፀውና የሚቀረጸው በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ አካላት ህይወት ተቆንጥሮ... ነው፡፡" ገጸባህርያት ልብወለዱ ከተቀዳበት ቦታና ዘመን የሚፈልቁ የዚያው ቦታና ዘመን ውጤቶች ናቸው፡፡ ገጸባህርያት የደራሲው የፈጠራ ውጤቶች ይሁኑ እንጅ በልብወለድ ዓለም ውስጥ ህልውናቸውን ካገኙ በኋላ እንደራሳቸው

ስሜትና ፍላጎት የሚመሩ እንጂ በደራሲው ህልውናና ፍላጎት የሚመሩ አይደሉም። ይህን በማስመልከት ዘሪሁን (2002፣ 164-5) የሚከተለውን ብለዋል፦

> ደራሲው ለገፀባህሪያቱ የህይወት ጎዳና ካበጀላቸው በኂላ በድርጊታቸውም ሆነ በአስተሳሰባቸው ጣልቃ እየገባ አቅጣጫቸውን መለወጥ የለበትም። ...አላዋቂው ደራሲ ገፀባህሪያትን ከቀረጸ በኂላ በህይወታቸው ገብቶ በዚህ ውጡ በዚህ ውረዱ ይላቸዋል። አዋቂው ግን ገፀባህሪያትን የራሳቸውን ኑሮ ሲኖሩ ይከታተላቸዋል። ሲናገሩ ያዳምጣቸዋል።

ልብወለድ የደራሲው የህይወት ልምድ ውጤት መሆኑ ባይካድም ሁሉም ገጸባህሪያት ግን የየራሳቸው መለዮ ያላቸው እንጂ የደራሲው የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ አይደሉም።

አንድ ደራሲ ገጸባህሪያትን የሚፈጥረው የእውኑን ዓለም ሰዎች መነሻ በማድረግ፣ የራሱን ፈጠራና ጥበብ በማከል፣ ታማኝነት ባለው መልኩ የሰዎችን የተወጣጣ ባህሪ አዋህዶ ህልውና በመስጠት ነው። ይህን አስመልክተው ዘሪሁን (2002፣160) የሚከተለውን ብለዋል፦

> ደራሲ ገጸባህሪ የሚፈጥረው ለህይወትና ለሰው ልጅ ካለው አተያይና አጠቃላይ እውቀት በመነሳት የራሱንና በእውኑ አለም የሚያውቃቸውን ሰዎች አካላዊና ህሊናዊ መልክ ወይም አጠቃላይ ስብእና መነሻ በማድረግ ነው ። የአንድ ገፀ ባህሪ መጠንሰሻው በእውኑ አለም የሚኖር ወይም የኖረ አንድ ግለሰብ ሊሆን ቢችልም በልቦለዱ ውስጥ የተቀረፀው እራሱ አይሆንም። ገፀባህሪ ደራሲ በህይወት ገጠመኙ ካያቸውና ካወቃቸው የተለያዩ ሰዎች ከዚህም ከዚያም የቃረማቸውን ባህሪያት ያጨቀበት ምናባዊ ፍጡር ነው።

የገፀ ባህሪያት ማንነትና ያሉበትን ሁኔታ ለማሳወቅ ደራሲያን የሚጠቀሙባቸው ሁለት አይነት ዘዴዎች አሉ። (ዝኒ ከማሁ) የገፀ ባህሪያት አቀራረብ ዘዴዎችን ርቱዕ /ዘርዛሪ/ እና ኢ-ርቱዕ /ተውኔታዊ/ አቀራረብ ዘዴዎች በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል።

ርቱዕ የአቀራረብ ዘዴ ገፀባህሪያቱን በመግለፅ ወይም በመተንተን የሚያቀርብ ሲሆን ገፀባህሪያቱ ምን እንደሚመስሉ ተራኪው ወይም ዳር ቁሞ የሚታዘብ ገጸባህሪ ይነግረናል፡፡ በዚህ አይነቱ የአቀራረብ ዘዴ በአብዛኛው የገፀባህሪያቱ አካላዊና ህሊናዊ መልክ በዝርዝር ይገለፃል፡፡ ርቱዕ ወይም ዘርዛሪ አቀራረብ የገፀባህሪውን ብዙ መልኮች በጥድፊያ ማሳየት የሚችል በመሆኑ ደራሲያን እንዲጠቀሙበት የሚስብ ቢሆንም የገፀባህሪውን አካላዊም ሆነ ህሊናዊ መልክ ባንዴ ዝርግፍ አድርጎ የማቅረብ ሁኔታ ስለሚታይበት አንባቢው በጉጉት ንባቡን እንዲቀጥል አይጋብዝም፡፡ (ዝኒ ከማሁ) በዚህ አይነት የአቀራረብ ዘዴ በአብዛኛው የገፀባህሪያት አካላዊ መልክ ይህን ይመስላል ወይም እንደዚህ አይነት ነው ቁመቱ፣ መልኩ፣ ፀጉሩ የመሳሰሉትን አያሌ አካላዊ መልክ ይዘረዝራል፡፡ እንዲሁም በገፀባህሪያት ህሊናዊ መልክ ታጋሽነት፣ ታታሪነት፣ ብስጭት፣ ጨካኝነት፣ የመሳሰሉትን ይዘረዝራል፡፡

ኢ-ርቱዕ ወይም ተውኔታዊ የአቀራረብ ዘዴ ገጸባህሪውን በድርጊት ያሳያል፡፡ በዚህ አይነቱ የአቀራረብ ዘዴ ደራሲው ገጸባህሪያቱን በመድረክ ላይ እንደሚታዩ እያናገረና ድርጊት እያስፈፀመ ስለሚያቀርባቸው አንባቢ መልካቸውንና ባህሪያቸውን ለማወቅ አያዳግተውም፡፡ በእውኑ ዓለም የምናገኛቸውን ሰዎች ከንግግራቸውና ከግብራቸው ማንነታቸውን ለመለየት እንደሚቻል ሁሉ ገፀባህሪያቱም በኢ-ርቱዕ ዘዴ ከቀረቡ መልካቸውንም ሆነ ሰብዕናቸውን ለማወቅ አይከብድም፡፡ ገፀባህሪው ረጅም ይሁን አጭር ጠይም ይሁን ቀይ ዳማ፣ ወፍራም ይሁን ቀጭን ወይም ታጋሽ ይሁን ግልፍተኛ፣ ቸር ይሁን ንፉግ በውል መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንባቢው ድርጊታቸውን ተመልክቶ የገፀባህሪያቱን ሁኔታ መረዳት የሚችልበት አቀራረብ ነው፡፡

ደራሲያን በልቦለድ ዓለም ታሪክ ውስጥ በፈጠሯቸው ገፀ ባህሪያት ወይም ባለታሪክ የታሪኩ ድርጊት እንዲፈፀም ያደርጋሉ፡፡ የድርጊት አፈፃፀማቸው የሚታወቀውም በተጠቀሱት የአቀራረብ መንገዶች ነው፡፡ በመሆኑም በርቱዕም ሆነ በኢ-ርቱዕ የአቀራረብ ዘዴ የገፀባህሪያቱን ሰብዕና በታሪኩ ውስጥ የሚኖራቸው ሚና እና የርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለተደራሲያን ያቀርባል፡፡ ተደራሲያንም አንዱን ገፀባህሪ ከሌላው ለይቶ የሚያውቅበት ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ደራሲው ገፀ ባህሪያት በሚቀርፅበት ጊዜ መዘንጋት የሌለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች (ዝኒ ከማሁ) እንደሚከተለው ገልፀዋቸዋል፡፡

### 2.2.3.1 የገጸ ባህሪያት ግለወጥነት

አንድ ገፀ-ባህሪ ከአለባበስ ጀምሮ እስከ አስተሳሰቡ ድረስ የራሱ የሆነ ባህሪና አስተሳሰብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ የአንድ ገፀ- ባህሪ ልዩ የሆነ የግል አቋም፣ ስነ- ምግባር፣ አስተሳሰብ ደግሞ የግሉ ባህሪ ይባላል፡፡ እንደ ዘሪሁን (2002፣164) ‹‹ ገፀ-ባህሪያት በታሰቡበት ቦታና ጊዜ የየራሳቸው ባህሪና ድርጊት እንዲሁም አስተሳሰብ ኑሯቸው አንዱ ከሌላው የሚለይባቸው መልኮች በውል ከታዩ ግለ-ወጥነት አላቸው፡፡›› በማለት ይገልፁታል፡፡

### 2.2.3.2 የገጸ ባህሪያት የባህሪ ዘላቂነት

እንደ ዘሪሁን (2002፣162) አገላለጽ ገፀ- ባህሪያት በባህሪያቸው፣ በድርጊታቸውና በአስተሳሰባቸው በልቦለድ ውስጥ ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፍጻሚያቸው ድረስ ዘላቂነት እንዲኖራቸው ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ደራሲያን በልቦለድ ድርሰታቸው ውስጥ የሚስሏቸው ገፀ- ባህሪያት ዘላቂነት ያለው ባህሪ ሊኖራቸው ይገባል በማለት ያብራራሉ፡፡

ይህ ማለት ገፀ-ባህሪያት የእውኑ ዓለም ሰው ወኪሎች እንደመሆናቸው መጠን የተለያዩ ለውጦች ይታይባቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነውም በእድሜ፣ በሆነ ነገር ምክንያት ነው፡፡ የባህሪ ዘላቂነት ሲባል ፍፁም ለውጥ መታየት የለበትም ሳይሆን ለውጡ ምክንያታዊ መሆን አለበት፡፡

### 2.2.3.3 የገጸባህሪያት ኢ- ፍፁምነት

የገፀ- ባህሪ አቀራረፅ መታወቅ ያለበትጉዳይ ገፀ- ባህሪያት በስብዕና መልካቸው ፍፁም ወይም አንድ ወጥ ሆነው መሳል የሌለባቸው መሆኑ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ዘሪሁን (2002፣163) ሲያብራሩት

> የእውኑ አለም ሰዎች በስብዕናቸው አንድ ወጥ አይደሉም፡፡ የሰናይ እና እኩይ፣ የጠንካራና የደካማ ባህሪያት ጥንቅር ናቸው፡፡ በድርጊታቸውም ሆነ በባህሪያቸው በጎና ክፉም ተጣምረው ይገኙባቸዋል፡፡ ትጉህ ሰራተኛ፣ ትቢተኛ፣ ሰነፍ፣ ቅን፣ ትእግስተኛ፣ ቀናተኛ፣ ብልህ፣ ኩራተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በጣም የዋህ የሆነው ሰው ትንሽ መሰሪነት፣ በጣም ግንፍልተኛ፣

መጠነኛ ታጋሽነት፣ በጣም ውብ የምትባለው እንደ ስንክ መልከቀና ያልሆነችው ደግሞ በመጠኑ ሳቢነት አያጡም።

ከላይ ከቀረበው ጥቅስ መገንዘብ እንደሚቻለው በልቦለድ ውስጥ ሲሳሉ በመልካቸው፣ በባህሪያቸው እና በስራቸው ፍፁም አንድ ወጥ ሆነው አይሳሉም ምክንያቱም ደግሞ በልቦለድ የእውነተኛውን አለም በሚወክል እና ሊወክል በሚችል መንገድ ስለሚቀርቡ የእውነተኛው አለም ሰዎች ደግሞ ፍፁም የሆነ አንድ አይነት ባህሪ የላቸውም።

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተያያዘ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በተለያዩ ተማሪዎች የተጠኑ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው ሦስት ጥናታዊ ጽሑፎች ተዳስሰዋል። ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተያያዘ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በተለያዩ ተማሪዎች የተጠኑ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው ሦስት ጥናታዊ ጽሑፎች ተዳስሰዋል። በቀዳሚነት የተዳሰሰው "Employment opportunities of and discrimination against person with disabilities" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በምንዳሁን ገብረ ጻዲቅ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሶሻል ወርክ ትምህርት ክፍል እ.ኤ.አ. በ2006 ዓ.ም. የቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። የምንዳሁን ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ሥራ ማግኘት እድላቸውንና የሚደርስባቸውን መድልዎ ለመዳሰስ የሞከረና ለችግሮች እልባት ለመስጠት ህጋዊና አካዳሚያዊ መፍትሄዎችን የጠቆመ ነው። አካል ጉዳተኞች ላይ በሥራ ቦታ የሚደርሰውን መድልዎ ለማጥናት 15 ተጠኝዎችን የመረጠ ሲሆን አስሩ ማየት የተሳናቸው ሲሆኑ 5ቱ ደግሞ አካል ጉዳተኞች (physically disabile) ናቸው። ከጥናቱም በኋላ በደረሰበት ውጤት መሠረት አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታና ሥራ ማፈላለግ ሂደት የሚደርስባቸው መድልዎ ስር የሰደደ ሲሆን ከዩኒቨርስቲ ከተመረቁ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ውስጥ በተማሩበት መስክ ሥራ የሚያገኙት ሶስት በመቶ ብቻ ናቸው። ለዚህ የዳረጋቸው ደግሞ የፈታኝ መስሪያ ቤቶቹ ህግና ደንብን አለመከተልና አካል ጉዳተኞችን በመስሪያ ቤታቸው የመቅጠር ፍላጎታቸው አነስተኛ በመሆኑ ነው። ይህ ሁኔታ አካል ጉዳተኞችን ለስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጫና ይዳርጋቸዋል። በእኔና በምንዳሁን ጥናት መካከል መሠረታዊ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ እኔም የዐይነ ስውራኑን ገጸባህርያት የሥራ ሁኔታና ከሌሎች ገጸባህርያት ጋር

ያላቸውን ግንኙነት የምመረምር መሆኔ ያመሳስለናል፡፡ ይሄም ገጸባህርያቱን ይበልጥ ለማወቅና በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ለመረዳት ያስችለኛል፡፡ የምንዳሁን ጥናት፣ በገሀዱ ዓለም በየጊዜው የምናያቸው መሆናቸውና ለመድልዖዎቹ ህጋዊና አካዳሚያዊ መፍትሄ የጠቆመበት መንገድ እንደ ጥናታዊ ጽሁፉ ጠንካራ ጎን ተስተውሏል፡፡ ነገር ግን ከ15 በማይበልጡ ተማሪዎች ናሙናነት የ18 ሚሊዮን አካል ጉዳተኞችን እጣ ፋንታ ለመፈረጅ የሞከረበት መንገድ አሳማኝ አለመሆኑ እንደ ጥናታዊ ጽሁፉ ደካማ ጎን ተስተውሏል፡፡

በሌላ በኩል ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል በሚል የተዳሰሰው "በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቀልዶች" በሚል ርእስ በ2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በየኔዓለም ካሳሁን የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ የየኔዓለም ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚነገሩትን ቀልዶችንና አባባሎችን መሰብሰብን እንደ ዋና ዓላማው በመውሰዱ ነው፡፡ ዘርፉ ፎክሎር በመሆኑ የጥናቱ ዋና ዓላማ ቀልዶችንና አባባሎችን መሰብሰብ ነው፤ ስለሆነም ቀልዶቹ አካል ጉዳተኞች ላይ ስለሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ አያብራራም፡፡ የኔ ጥናት ከየኔዓለም ጥናት የሚለይበት ዋነኛው ነጥብ ዐይነ ስውራን ገጸባህሪያት በተመረጡ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ ያላቸውን አሳሳል መገምገምን እንደ ዋና ዓላማ በመውሰዱ ነው፡፡ የየኔዓለም ጥናት በፎክሎር የጥናት መስክ የሚያተኩር ሲሆን የኔ ደግሞ በስነጽሁፋዊ ቴክስቶች በተለይም በኣጭር ልቦለዶች ላይ የሚገኙ ዐይነስውር ገጸባህሪያትን አሳሳል የሚመለከት ነው፡፡ የየኔዓለም ጥናት በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች፣ ኣባባሎችና ቀልዶች አካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦችን ከማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እንዴት እንዳቀባቸውና አካል ጉዳተኞች ከተቀረው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ስላላቸው የቀዘቀዘ ግንኙነት ትገልጻለች፡፡ ይህንን በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ በጥናቷ፣ ቀልዶቹ አካል ጉዳተኞች ላይ ስለሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ አለመጠቆሟና በአባሪ ላይ እንደተመለከትኩት በቂ ቀልዶች አለመሰብሰቧን እንደ ጥናቱ ደካማ ጎን ተመልክቻለሁ፡፡

በመጨረሻም ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በርቀትም ቢሆን ይዛመዳል በሚል የተዳሰሰው "Challenges and opportunities in learning through technology... the case of students with visually impairment" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2013 ዓ.ም በአልማዝ አበሁሃይ ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ለ'ሶሻል ወርክ' ትምህርት ክፍል በአዲስ አበባ

ዩኒቨርስቲ የቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። ይህም በእኔ ጥናት ውስጥ ገፀባህርያት በዐይነ ስውርነታቸው ምን ተጠቀሙ? ምንስ ጎደለባቸው? በሚል ከማየው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የአልማዝ ጥናት የ'ሶሻል ወርክ' እንደመሆኑ መጠን አላማው የገጠሟቸውን ተግዳሮቶች በመለየት መንስዔዎቹን ለይቶ ህጋዊ መፍትሔ ማፈላለግ ነው። የአልማዝ ጥናት በገሀዳዊ እውነታ ላይ ያተኮረ ሲሆን የኔ ጥናት ግን በጥበባዊ ቴክኒኮች ላይ ያተኩራል። አልማዝ በቴክኖሎጂ ታግዞ በመማር ሂደት ዐይነ ስውራን ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶችና የሚያገኟቸውን እድሎች ለመለየት ጥረት አድርጋለች። በጥናቷ፣ አብዛኞቹ ተማሪዎች በቴክኖሎጂ መማራቸው ከጉዳቱ ጥቅሙ እንደሚያመዝን ገልጸው ይህም በራስ መተማመናቸውን እንደጨመረላቸውና የማንንም እርዳታ ሳይፈልጉ በራሳቸው የሚሰጧቸውን የግል የቤት ሥራዎችና ጥያቄዎች ማየት እንዲችሉ እንዲሁም መጻህፍትን ባሰኛቸው ሰዓት እንዲያነቡ በር እንደከፈተላቸው ገልጸዋል። የአልማዝ ጥናት ብዙም ትኩረት በማይሰጠው በገሀዱ አለም እውነታ ላይ ትኩረት አድርጋ ማጥናቷ እንደ ጠንካራ ጎን ሊነሳ ቢችልም በናሙናነት የተጠቀመችው ውስን አካል ጉዳተኞችን መሆኑ እንደ ጥናቱ ውስንነት ይወሰዳል። እነዚህ ከላይ የተዳሰሱት ቀደምት ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይዛመዳሉ ተብለው የተወሰዱት ናቸው። ይህ ጥናት ከሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች የሚለየው ዐይነ ስውራን ገፀባህሪያት እንዴት ተስለዋል? የሚለውን በተመረጡ 5 አጫጭር ልብወለዶች ላይ ለመዳሰስ የሚሞክር ሲሆን ሶስቱም ጥናቶች በአካል ጉዳተኞች ላይ ያጠነጠኑ መሆናቸው ደግሞ ያመሳስላቸዋል።

# 3. የመረጃ ትንተና

## 3.1 አጽመ ታሪክ

በቀጥታ ወደ ትንተና ከመግባቴ በፊት ልቦለዱችን በአጭር በአጭሩ ማስተዋወቅ ስለሚያስፈልግ የልቦለዶቹ አጽመ ታሪኩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1. ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ

ድኃ ብርቱ በምትባል አነስተኛ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ እኒህ ጥንዶች ለረጅም ጊዜያት በአብሮነት ቢቆዩም ልጅ ወልደው ለመሳም አልታደሉም ነበር፡፡ ያያቸውም ሁሉ ያዝንላቸው ከንፈር ይመጥላቸው ነበር፡፡ ቤተሰቦቻቸውም እንዲወልዱ ይገፏፏቸውና ያበረታቷቸዋል፡፡ በዚህም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለአስራ ሁለት ዓመታት ከጠበቁ በኂላ ሚስት ወንድ ልጅ ለመጸነስ በቃች፡፡ ዘመድ ወዳጁም በጣም ደስ አለው፡፡ ልጁም ተወለደ፡፡ ታሪኩም ብለው ጠሩት፡፡ ይሁንና ወላጆች እጅግ በጣሙን ለልጅ ፍቅር ስሱ ስለነበሩ ማንም እንዲያይባቸው ወይም እንዲያንገላታባቸው አይፈቅዱም ነበር፡፡ ህጻኑም በምግብ በኩል ምንም ነገር ይጎድልበት ስላልነበር አስተዳደጉና ጤናማነቱ ሁሉንም ያስቀና ነበር፡፡ ይሁንና በጨለማ ክፍል ውስጥ ተዘግቶበት ስለሚውል ከዚህ ጨለማ የተሻለ ሌላ ዓለም ያለ አይመስለውም፡፡ በዚህ መልኩ ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ይህ ልጅ አሁን የቤተሰቦቹ እንክብካቤ ሰልችቶታል፡፡ በዚህም ምክንያት ሳይታይ ሹልክ እያለ ከእኩዮቹ ጋር መጫወት ጀምሯል፡፡ ይሁንና ህጻኑ እንደልቡ መጫወት የሚችልበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡ ዐይኖቹ የፀሐይ ብርሃን አርፎባቸው ማየት አቁመዋል፡፡ ዐይኖቹም በጊዜ ብዛት የማየት ችሎታቸውን አጥተዋል፡፡ ያለመሪ አይንቀሳቀስም፡፡ በተመሳሳይ ምክንያት የተነሳ ሽባ የሆነ ታዳጊ ደግሞ አለ፡፡ ምንተስኖት ይባላል፡፡ የምንተስኖት ወላጆች ለልጃቸው ከነበራቸው መጠን ያለፈ ፍቅር የተነሳ በህጻንነቱ መሬት እንዲነካ አይፈቅዱለትም ነበር፡፡ ሁሌም ከእቅፍ ወደ እቅፍ እንዳሸጋገሩት ነበር፡፡ ከጊዜያት በኂላም እግሮቹ መስለል ይጀምራሉ፡፡ ህጻኑም ከወገብ በታች ሽባ ይሆናል፡፡ እኒህ ሁለት ታዳጊዎች የጉርምስና የእድሜ ክልል ላይ ሲደርሱ አንድ ያደጉበትን ቀዬ ጥለው ወደ ሌላ ከተማ ይሄዳሉ፡፡

## 2. የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ

በርጠሎሜዎስ ከልጅነቱ ጀምሮ ዐይነ ስውር ነበር። ከዚህ በፊት ስለዓለም የነበረው እውቀት በዙሪያው በነበሩት ሰዎች የእውቀት አድማስ የተወሰነ ነበር። ከሚሰማው ውጭ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። እናም ከእለታት አንድ ቀን የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ ደውይ የሚያቀናው እውር የሚያበራው ኢየሱስ በአጠገቡ እያለፈ መሆኑን ይሰማል። በዚችም ቅጽበት በርጠሎሜዎስ ድምጹን ከፍ አድርጎ መጮኽ ይጀምራል። "የዳዊት ልጅ አድነኝ!" ኢየሱስም ምራቁን ከአፈር ጋር ይለውስና ሲቀባቸው ዐይኖቹ ማየት ይጀምራሉ። ይሁንና የበርጠሎሜዎስ ደስታ ብዙ አልዘለቀም። ባየው ነገር ደስተኛ አይደለም። ዓለም ላይ ያለውን ኢ ፍትሃዊነት ከማየት እውርነትን መርጧል። ታድያ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደግሞ ኢየሱስ ነው። በርጠሎሜዎስም ዐይነ ስውርነቱን ይመልስለት ዘንድ ኢየሱስን ፍለጋ ገባ።

## 3. ወይ አዲስ አበባ

ውብቴ በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚኖሩ፣ በልመና ከሚተዳደሩ ጥቂት ዐይነ ስውራን መካከል አንዱ ነው። በየመጠጥ ቤቱ፣ በየቤተክርስቲያኑ፣ በየጎዳናውና በየአቅጣጫው እየተመላለሰ በሚያጠራቅማት ትንሽ ሳንቲም ባለቤቱንና ራሱን ያስተዳድራል። እጅግ በጣም ትሁትና ቅን ሰው ነው። ይሁንና አንድ ትልቅ ችግር ነበረበት። እሱም ካልጠጣና ካልሰከረ እንደልቡ መለመን አይሆንለትም። በዚህም የተነሳ ከመሪዎቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት የለውም። አንዳንዶቹ ሲሰክር ጠብቀው በመደብደብ ገንዘቡን ይቀሙታል። በመጨረሻም ውብቴ ገንዘቡን ፈጽሞ ሊቀማው የማይችል፣ ጨዋ፣ ቅንና ታዛዥ ታዳጊ ያገኛል። ይሄ ታዳጊ ከጎጃም ክፍለ ሀገር ጠፍቶ የመጣ ሲሆን አዲስ አበባ ውስጥ መኖር ከጀመረ የተወሰኑ ወራት ተቆጥረዋል። ውብቴን በመምራት ለምኖ ከሚያገኘው ሳንቲም በጣም የተወሰነውን ይሰጠዋል። ይህም ለታዳጊው ከመጠን በላይ ነበር።...

## 4. ቦርጨቅ

ከእለታት አንድ ቀን ወንዳፍራሽ ፍራሽ አዳሽ አስደንጋጭ ህልም ያያሉ። ህልሙ የሚከተለውን ይመስላል። ጥድፊያ ነው ግፊያ ነው መንግስተ ሰማያት ለመግባት! "ተመልከት! አንተ ሰው ተመልከት!" አላቸው የአሮጊት ድምጽ። አቶ ወንዳፍራሽ ዘወር

ብለው ሲያዩ ያልጠበቁትን ነገር ተመለከቱ። ወንድማቸው አቶ መላኩን ሁሉም ሰው እየቀደማቸው ያልፋል። ጥድፊያ ነው ግፊያ ነው መንግስተ ሰማያት ለመግባት! "ኧረ አሳልፉን ጾመናል ጸልየናል" እያሉ ይመጻደቃሉ። ይሁንና የሰማቸው አልነበረም። ወደ በሩ ሲቀርቡም መላዕክቱ ይይዟቸውና "አይገቡም!" ይሏቸዋል። "ለምን?" ብለው ሲጠይቁም "ዱዳ ልጅዎ እረግምዎታል... እሱ ሲያለቅስ መላዕክት ወደ ቋንቋ ለወጡትና ተረዱት። አይገቡም!" ይሏቸዋል። አቶ መላኩም ሲያንገራግሩ በጣም የተበሳጨት መላዕክት አቶ መላኩን ወሳንሳ ይይዙና ወደ ገሀነም ይወረውሯቸዋል። በዚህ ጊዜ አቶ ወንዳፍራሽ ከእንቅልፋቸው በድንጋጤ ብንን ይላሉ። ተመሳሳይ ይዘት ያለው አስፈሪ ህልም ካዩ በኂላ አንደኛውን ለመነሳት ቆርጠው በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ቤተክርስቲያን ያቀናሉ። አቶ ወንዳፍራሽ ቤተክርስቲያን ተሳልመው ሲመለሱ አንድ የሚያውቁት የሚመስላቸውን ድምጽ ይሰማሉ። አንዲት አሮጊት የቤተክርስቲያኑ አጥር ላይ ተጠግተው ይለምናሉ። ድምጹን የት ነው የማውቀው እያሉ ሲጨነቁ በህልማቸው "አንተ ሰው ተመልከት!" እያለ ታላቅ ወንድማቸው በገነት በመላዕክት እጆች ተይዘው ሲወረወሩ ያሳያቸው ድምጽ ነው። አቶ ወንዳፍራሽ በግጥምጥሞሹ በጣም ከመገረማቸው የተነሳ ቀረብ ብለው አሮጊቷን ማውራት ይጀምራሉ። አሮጊቷም ሁሉንም ነገር በዝርዝር ትነግራቸዋለች። የአሮጊቷ ታሪክ ይህንን ይመስላል። ሰባት ጊዜ ወልዳ ሰባቱም ሞቱባት። በስምንተኛው ግን አዋቂ ቤት ሄደች። አዲስ አበባ ሞት የለም አሏት። ወደ አዲስ አበባም ይዛው ሄደች። አዲስ አበባ ውስጥ ጠላ እየጠመቀች አሳደገችው። ለወግ ለማረግ በቃ። አገባ። እናትም እርጅናው እየተጫጫናት ስለነበር ከልጇ ጋር መኖር ትጀምራለች። ይሁንና ሚስት እናትን አምርራ ትጠላለች። ለተወሰነ ጊዜ ጠበቀችና ልክ ስትወልድና ልቡን እንዳሸነፈች ስታውቅ በእናቱና በሚስቱ መሀል አንዱን እንዲመርጥ ታስገድደዋለች። እናትም ሳትታይ ሹልክ ብላ ትወጣለች። እና በእናት እምነት መሠረት እግዚአብሔር በእያንዳንዱ እርምጃዎቿ እየተከተላት ነው። ዛሬም ጨዋታ እንዳማራቸው አውቆ አቶ ወንዳፍራሽን ላከላቸው።

## 5. ራትና መብራት

ዐይነ ስውሩን ሰውዬ የሚመራቸው የአምስት ዓመት የልጅ ልጃቸው ነው። ከእለታት አንድ ቀን ሲለምኑ ውለው ብርሌ ጠጅና እራት ወደሚያገኙበት የእማማ ታንጉት ቤት እንዲወስዳቸው ይጠይቁታል። በመንገዳቸው ላይ ውብ ሊቀርን ያገኙታል። ውብ ሊቀር እግረ

ሰላላ ነው። በወሬ መሀል የባልንጀራቸውን የዝምበላቸውን ታሪክ ይነግራቸዋል። ዝምበላቸው ያለ መሪ ሲንቀሳቀስ አዳልጦት ወድቆ ጭንቅላቱ ተተርትሮ ከሞት ለጥቂት መትረፉን ይሰማሉ። በዚህ ጊዜ የልጅ ልጃቸውም እንደዝምበላቸው ልጅ ጥሏቸው እንዳይኮበልል ስጋት ይወድቅባቸዋል። በመንገዳቸው ላይ እስኪርቢቶና ደብተር እንደጨረሰ ሲነግራቸው ሊገዙለት ይስማማሉ። ምክንያቱም የዝምበላቸውን ታሪክ ሰምተዋል። አሁንም በድጋሚ እንጎቻ እንዲገዙለት ሲጠይቃቸው ይገዙለታል። አሁን ጠጅ እንደማይጠጡ አውቀዋል። ምክንያቱም የባልንጀራቸውን ታሪክ ሰምተዋል። አሁን በድጋሚ ለትምህርት ቤት መዋጮ እንደሚያስፈልግ ይነግራቸዋል። እሳቸውም አማራጭ ስላልነበራቸው የእራታቸውን ብር ሊሰጡት ይወስናሉ። ምክንያቱም የዝምበላቸው ታሪክ አስደንግጧቸዋል። እማማ ታንጉት በር ላይ ሲደርሱ ህጻኑ መልሶ ወደቤት እንዲወስዳቸው ይነግሩታል።

## የዋና ዋና ገፀባህሪያት አሳሳል ትንተና

በአምስቱም ልብወለዶች ውስጥ ጉልህ ሚና ካላቸው ዐይነ ስውራን ገጸባህርያት መካከል ታሪኩ (ማሙዬ ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ)፣ ውበቱ (ወይ አዲስ አበባ)፣ በርጠሎሜዎስ (የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ)፣ ሽማግሌው (ራትና መብራት)፣ አሮጊቷ (ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ) ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የገጸባህርያት አሳሳል ትንተናውም በእነዚህ ገጸባህርያት ላይ ብቻ ያተኩራል።

## 3.2 ታሪኩ (ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ)

ታሪኩ ደን ብርቱ በምትባል ትንሽ ከተማ ውስጥ ተወለደ። በኋላም የዐይኑን ብርሃን ካጣ በኋላ ለቤተሰቦቹ ሸክም ላለመሆን መካነ ሥላሴ ወደሚባል ትልቅ ከተማ ተሰደደ። በኋላም ሀብት አግኝቶ፣ የዐይኑን ብርሃን በህክምና አስመልሶ ወዳደገበት ማህበረሰብ ተመለሰ። ለማህበረሰቡም ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤትና የአምልኮ ስፍራ አሳነጸ።...

### 3.2.1. ገጸባህሪው ከግለወጥነት አሳሳል አንፃር

ገጸባህሪያት በተሳሉበት ጊዜና ቦታ የየራሳቸው ባህሪ፣ ድርጊት፣ አስተሳሰብ፣ አካላዊ መልክ እንዲሁም አቋም ኖሯአቸው አንዱ ከሌላው የሚለይባቸው መልኮች በውል ከታዩ ግለወጥነት አላቸው እንላለን። ከዚህ አኳያ በ“ምራኝና እንሂድ” ልቦለድ ውስጥ ዋና ገፀባህሪ

ሆኖ የተሳለው ታሪኩ ከግለወጥነት አንጻር በአግባቡ ተስሏል፡፡ ታሪኩ በልቦለዱ ውስጥ የተሳለው እንደ ዋና ገፀባህሪ ነው፡፡ ታሪኩ የሚያጠነጥነውም በሱ ህይወት ዙሪያ ነው፡፡ ይህ ገፀባህሪ ስለ አካላዊ ሁኔታዎች በመፅሀፍ ውስጥ በብዛት አልተገለፀም፡፡ ታሪኩ በልቦለድ ውስጥ ድርጊት ሲፈፅም፣ ድርጊት ሲፈፀምበት፣ በሁኔታዎች ሲሰቃይ፣ ሲንገላታ እናየዋለን እንጅ በአካላዊ ገለጻ ብዙ አናውቀውም፡፡ ይህ ሲባል ግን ውስንነቱን ለመግለጽ ነው እንጂ ስለ ገጸባህሪው አካላዊ ቁመና የቀረበበት ምንም ዓይነት ክፍል የለም ማለት አይደለም፡፡

በልቦለድ ውስጥ ገፀ ባህሪያትን በቀጥታ መግለፅ ከሚቻልባቸው የልቦለድ አቀራረብ ዘዴዎች መካከል ገለፃ አንዱ ነው፡፡ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ዘይቤያዊነት ስሜትንና ማንነትንም የሚጠቀምበት ጊዜ ይኖራል፡፡ በ"ምራኝና እንሂድ" ልቦለድ ውስጥ ስለ ታሪኩ የተደረጉ የተወሰኑ አካላዊ ገለፃዎችን እናገኛለን፡፡

> ዓይነ ስውሩ ከማየት የራቀ ይሁን እንጂ እጅና እግሩ ደህና ነው፤ አካላቱም ግዙፍና ጠንካራ ነው፡፡ ጆሮዎቹ ከመስማታቸው የተነሳ በዐይን የሚያዩት፣ የሚገምቱት፣ ዙሪያ አካላቸውን እንደሚጠብቁ ሁሉ እርሱም ንቃቱና ጠርጣሪነቱ የበዛ ነው፡፡ ይህን የመሰለ ተሰጥኦ እያለው ባለማየቱ ግን ብስጩና ንዴተኛ ነበር፡፡ ተፈራ (1960፣ 53)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ታሪኩ በአካለ ቁመናው ግዙፍ እንደሆነ ነው፡፡ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኑ መጠን በታላቅ ክብካቤ አድጓል፡፡ ይህም ገጸባህሪው በሰውነቱ ግዙፍና ጤናማ እንዲሆን አግዞታል፡፡ አስረጅ ጥቅስ እንመልከት፡-

> የታሪኩ ወላጆች ከመሳሳታቸው የተነሳ ከመጋረጃ ውስጥ ሳያወጡ ብርሃን ነስተው ጠቃሚ የመሰላቸውን ምግብና መጠጥ በገፍ ያቀርቡለት ስለነበር እያደገ በሄደ ቁጥር ከዚያ ከጨለማ ቦታ የተሻለ ኑሮ ያለ አይመስለውም ነበር፡፡ እንኳን ከውጭ የመጣ እንግዳና አባትና እናቱም ቢሆኑ ልጃቸውን ማጫወት ሲፈልጉ እዚያው ብርሃን ካጣው ክፍል ውስጥ ገብተው የዳበሳ ያህል በሚቆጠረው ውስጥ ነበር፡፡ ተፈራ (1960፣ 11)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ወላጆቹ የውጪውን አየር ጸባይ አላለማመዱትም። ይህም ለአካባቢው እንግዳ እንዲሆንና የተፈጥሮን ጫና መቋቋም እንዳይችል አድርጎታል። ታሪኩ እንዴት የዐይን ብርሃኑን እንዳጣ እንመልከት፦

> ታሪኩ ሹልክ እያለ ከጓደኞቹ ጋር ለመጫወት መውጣት ቀጠለ። ነገር ግን እንኳን ሙሉ ሙቀት ያላት ፀሐይ በወጣችበት ጊዜና በደመናውም ሰዓት ቢሆን ዓይኑ ተገልጾ ፊት ለፊት ለማየት ይሳነው ጀመር። ስለዚህ ዐይኑን ጨፍኖ ሲዳክርና የልጆች ድምፅ እየሰማ ሲከተል ያረፍድ ጀመር። ከዕለታት አንድ ቀንም በዕድሜ ጓደኞቹ ከሆኑት ጋር ባንድ ኩሬ አጠገብ ዐይኑን ጨፍኖ ሲጫወት ከቆየ በኋላ ገለጥ ቢያደርገው ከውሃው ላይ የተወረወረ ጨረር (የፀሐይ ብርሃን) ዓይኑ ላይ ቢያንጸባርቅ ጨርሶ ለመጥፋት በቃ። ወደ ቤቱ ሲመለስም ጓደኞቹ መርተው አደረሱት። በዚህ ሁናቴ የታሪኩ ኑሮ ብርሃን ነስቶት ዓይነ ስውር ሆኖ የወደፊት ተስፋው እተገኘ ድረስ እድለ ቢስነቱ እየቀጠለ በመንደር የሚውል ስንኩል ሆነ። ተፈራ (1960፣ 12)

ቀደም ሲል የገጸባህሪውን አካላዊ ቁመና እንደገለጽነው የተደረገለት ተገቢ ክብካቤ ሰውነቱን ቢያደረጀውም ከአካባቢው ጋር እንዲለማመድ ግን እድሉን አልፈጠረለትም። ይህም በዙሪያው ለከበበው ዓለም እንግዳ እንዲሆን አድርጎታል። በዚህም የተነሳ ገና በህጻንነቱ የዐይን ብርሃኑን እንዲያጣ ምክንያት ሆኗል። ይህ ማንነቱም ታሪኩ ከሌሎች ገፀባህሪያት የሚለይበት ግለ ወጥ ባህሪው ነው።

ይሁንና በደሀ ቤተሰብ ውስጥ ካደገና ለቤተሰቦቹ ሸክም ላለመሆን ብሎ ሀገር ከለቀቀ ሰውነቱ እንዴት አልተጎሳቆለም? ከልጅነቱ አንስቶ በዓይነ ስውርነት ያደገና ህይወት ያንገላታው ሰው ይህንን የመሰለ ድርጁ ተክለ ቁመናና ሰውነት የመኖር እድሉ ምን ያህል ነው? እዚህ ላይ ታሪኩ በምኞት ባደገ የዐይናማ ተክለ ቁመና ተስሎ እናየዋለን። ይሄ ደግሞ ወደ በኋላ በምንመለከተው በኢ-ፍጹምነት ላይ ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል።

## 3.2.2 ገጸባህሪው ከዘላቂነቱ አሳሳል አንፃር

ዘላቂነት በልቦለድ ገፀባህሪያት አቀራረፅ ላይ መኖር ከሚገባቸው መሰረታዊ ቁምነገሮች አንዱ ሲሆን ይህ ዘላቂነት በባህሪያቸው፣ በድርጊታቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በአቋማቸው

በአጠቃላይ በውስጣዊና በውጫዊ መልካቸው መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም “ምራኝና እንሂድ” ልቦለድ ውስጥ ከሚገኙት ገፀ ባህሪያት መካከል አንዱና ዋናው ገፀባህሪ ታሪኩ የባህሪ ዘላቂነት ይስተዋልበታል፡፡ ለዚህ ማሳያ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን አስረጅ እንመልከት፤

> የሁለቱ አካል ጉዳተኞች እጣ አንድ በመሆኑ ለወላጆቻቸው ሸክም ሆነው ከመኖርና ከጎደኞቻቸው ዘንድ ዝቅተኛ ግምት ከሚኖርባቸው ወደ ሌላ አውራጃ ሄደው ለምነው ቢያድሩ መሻሉን በምስጢር መርጠው አንድ ረጅም ዘንግ ካዘጋጁ በኋላ ዐይነ ስውሩ እግረ ሰላላውን ተሸክሞ ዘንጉን ለሁለት ይዘው እየተደጋገፉ ርቀው ሄዱ፡፡ ተፈራ (1967፣ 16)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ታሪኩና ባልንጀራው በጥገኝነት ዙሪያ የመረረ ጥላቻ እንዳላቸውና ራሳቸውን ለመቻል የሚያደርጉትን እልህ አስጨራሽ ጥረት ነው፡፡ ታሪኩ ዓይነ ስውር ቢሆንም ለቤተሰቦቹ ሸክም መሆን አይፈልግም፡፡ ይህ አቋሙ ነው፡፡ ይህ አቋሙ ልቦለዱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ አብሮት ይዘልቃል፡፡ ስለሆነም የባህሪ ዘላቂነት አለው ማለት እንችላለን፡፡

> እስከመቼ የሰው እጅ አይተን እንኖራለን፤ ስለዚህ በመጠኑ ብንሰራ ግን የድካማችንን ዋጋ ተቀብለን ያዘነም ተረፍ አድርጎ ይሰጠናል፡፡ ሲል አዋየው፡፡ ዐይነ ስውሩም ለዚህ ሀሳብ የሚቃወምበት መንገድ ስለሌለ ተቀብሎ የሚሰሩትን ሲያሰላስሉ... ተፈራ (1967፣ 32-33)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ደግሞ ታሪኩና ባልንጀራው ከልመና ህይወት ወጥተው ሰርተው ራሳቸውን የሚደግፉበትን መንገድ ሲያሰላስሉ ነው፡፡ የመጀመሪያው የቤተሰብ ሸክም ያለመሆን ፍላጎት ነበር፡፡ እሱን አሳክተዋል፡፡ አትክልት እርሻ ውስጥ ተቀጥረው ሰርተዋል፡፡ ቀለም ቀቢ ሆነዋል፡፡ የመኪና መካኒክም ነበሩ፡፡ ይሄ ሁሉ ከልመና ህይወት ወጥቶ ወደ ተሻለ ደረጃ ለመድረስ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ በዚህም ታሪክ ውስጥ ዘላቂነት ያለው ጠባይና ለውጥ እንመለከታለን፡፡ በመጨረሻም ተሳክቶላቸውና ከድህነት ወጥተው እናያለን፡፡ “በዚህ ሁናቴ ሁለት ባይተዋሮች ጋሼ ምራኝ አብዬ ተሸከመኝ ከማለት ተላቀው ማሰብ መስራት በሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰው የወደፊት ኑሯቸውን ማሰላሰል ጀመሩ፡፡” ተፈራ (1967፣

70) ከዚህ ታሪክ ለመረዳት እንደምንችለው ገጸባህርይው በጊዜ ብዛት የማይፈተን ዘላቂ ባሕሪ አለው፡፡

ለአብነት ያህል ታሪኩ ከዐይነ ስውርነት፣ ምንተስኖት ከእግረ ሰላላነት የተፈወሱበትን ክፍል ማንሳት እንችላለን፡፡ ሁለቱ ገጸኛማቾች ተዝቆ የማያልቅ ጥሪት ካገኙ በኋላ ከአንድ ዓመት በላይ የዘለቀ ህክምና አድርገው ከህመማቸው ይፈወሳሉ፡፡ እዚህ ላይ የታሪኩስ ይሁን የገጸኛው እግረ ሰላላነት እንዴት በህክምና ሊድን ይችላል? የሚል ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ታሪኩም ሆነ ምንተስኖት (ገጸኛው) ለቤተሰቦቻቸው የመጀመሪያ ልጆች ሲሆኑ ቤተሰቦቻቸው ከብዙ ዓመታት ጸሎትና ጥበቃ በኋላ ስለሆነ ያገኟቸው ከቤት እንዲወጡ አይፈቅዱላቸውም ነበረ፡፡ በኋላ ግን ቆይቶ ሁለቱ ታዳጊዎች ላይ በጥንቃቄ ጉድለት የሚፈጠር የጤና እክል ገጥሟቸዋል፡፡ ይህም ሲባል ህመማቸው በተፈጥሮ የመጣ ስላልሆነ በህክምና እርዳታ የመፈወስ እድል አለው ማለት ነው፡፡ ይህም የታሪኩና የምንተስኖት አካል ጉዳት ከዚህ ዓይነቱ የአካል ጉዳት መካከል የሚመደብ ነው፡፡ ስለዚህም ገጸባህርያቱ ላይ የታየው አካላዊ ለውጥ አመክንዮአዊ ስለሆነ የገጸባህሪውን የባህሪ ዘላቂነት ጥያቄ ውስጥ አይከተውም፡፡

## 3.2.3. ገፀ ባህሪው ከኢፍጹምነት አሳሳል አንጻር

በገፀባህሪያት አቀራረፅ ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ ገፀባህሪያት በሰብዕናቸው ኢ-ፍጹም ናቸው፡፡ ስለዚህ በመልካቸውም ሆነ በአስተሳሰባቸው ፍፁም ሆነው መሳል የለባቸውም፡፡ የገሀዱ አለም ሰዎች በመልክ፣ በቁመና፣ በባህሪ በአስተሳሰብ ወዘተ ፍፁም አይደሉም፡፡ ገፀባህሪያትም እንደዚሁ መሳል መቻል አለባቸው፡፡ በምራኝና እንሂድ ልቦለድ ውስጥ ታሪኩ ፍፁም ሆኖ የተሳለበት አጋጣሚ አለ፡፡ ታሪኩ በልቦለዱ ውስጥ የተሳለው ሰናይ ባህሪ ብቻ ይዞ ነው፡፡ ለአስረጅነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> ዓይነ ስውሩ፦ እኔ ሞቴን መርጫለሁ፤ መሆንም አለበት፣ ግን ጓደኛዬ እንዴት ሆኖ ሊኖር ነው? ማንስ አላውሶት? ሌላው ቀርቶ እዳሪ እንኳን ሲወጣ እኔ ካልወሰድኩት ችሎ አይሄድ ውሃስ ቀድቶ የሚያጠጣው ማን አለ? ስለዚህ ለኔ ሕይወት ሳስቼ ሳይሆን ለርሱ ስል በስቃይ ብኖር ይሻላል፡፡
>
> የሰማዩ ጌታ የምድሩ ባለቤት

አረ ለምንድን ነው ይሄ ሁሉ ምሬት

ዓለም ጠፍጣፋ ነች ወይም ክብ ትሁን

እኔ አንዱ ፍጡርህ ደካማ ምስኪን። ተፈራ (1960፣ 18)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ታሪኩ ለባልንጀራው አዛኝና ሩህሩህ እንደሆነ ነው። ታሪኩ በሌሎች አጋጣሚዎችም ቅንና ሁሌም መልካሙን ነገር ከማድረግ ወደኋላ የማይል ገጸባህርይ ተደርጎ ተስሏል። ታሪኩ ምንም እንኳን ችግረኛ ቢሆንም ለተቸገረ የሚረዳ ደግ ሰው እንደሆነ ከጥቅሱ እንረዳለን። ስለሆነም ገጸባህርይው ከድርጊትና ከኹለንተና ባሕሪ አንጻር ፍጹም ሆኖ ተስሏል ማለት እንችላለን። ይሄ ደግሞ ገጸባህሪውን ሰዋዊ ሳይሆን መልአክአዊ ጠባይ ያላብሰዋል። ይሄ ደግሞ ከነባራዊው የገሀዱ ዓለም እውነታ ጋር ያጣርሰዋል።

በመጨረሻም የገጸባህርይውን ፍፁምነት በግልፅ ለመረዳት ያህል ቀጣዩን ጥቅስ እንመልከት።

> ያለው ደስ ይላል እንደሚባለው ታሪኩና ምንተስኖት ከፍ ያለ ሀብት ያላቸው ባለፀጎች ከመሆናቸው በላይ የድውያን መፈወሻ የሕፃናት ትምህርት መመገቢያ ሕንፃ በማሰራታቸው የአገሬው ህዝብ ከመጠን በላይ ይወዳቸውና ያከብራቸው ስለነበር ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ በታላቅ ናፍቆት ይጠባበቅ ነበረ። ተፈራ (1967፣ 105)

ቀደም ሲል በአጽመ ታሪኩ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ታሪኩ ከልጅነቱ ጀምሮ ዓይነ ስውር ነበር። ይሁን እንጂ ዐይነ ስውርነቱ በህክምና የሚመለስ ዓይነት ስለነበረ በአንድ ዶክተር አማካኝነት ብርሃኑን መልሶ ያገኛል። ብርሃኑንም ካገኘ በኋላ እንደ ብድር ቆጥሮት በአካባቢው ለሚገኙ ነዋሪዎች የልጆች ትምህርት ቤትና ሆስፒታል ያሳንጻል። ታሪኩን ፍጹም የሚያሰኘው ግን ይሄ አይደለም። ይሄ ማህበረሰብ ብርሃኑን መልሶ ስለሰጠው ትምህርት ቤትና ሆስፒታል ቢያንስበት እንጂ አይበዛበትም። ታሪኩን ፍጹም የሚያሰኘው ለገፋውና ለተወለደበት ማህበረሰብ ሆስፒታልና ትምህርት ቤት ማሰራቱ ነው።

> ሰፊ በሆነው በአትክልቱ ቦታ ውስጥ ተማሪ ቤትና ሆስፒታል አሰርተው የመቀራረብንና የመዛመድን ልምድ ለመመስረት አቀዱ። ወዲያውም ለዚህ ስራ ችሎታ ያላቸውን ከመካነ ሥላሴ አስመጥተው ሥራው በመፋጠን ይሰራ

> ጀመር።… ታሪኩና ምንተስኖት ከወላጆቻቸው ዘንድ ለብዙ ወራት ከቆዩ በኋላ የቤተክርስቲያኑ የሆስፒታሉና የትምህርት ቤቱ ሥራ እንደተጀመረ ወደ መካነ ሥላሴ ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው ጋር ደስታቸውን ሲፈጽሙ ቆይተው የሕንጻው ስራ እንዳለቀ ለምርቃቱ አማቾቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ወደ ደጎ ብርቱ ከተማ በታላቅ ጉዞ ሄደው ከቤታቸው አረፉ። ተፈራ (1960፣ 120)

ከጥቅሱ የምንረዳው ታሪኩ ፍፁም ደግና ሳደገበት ማህበረሰብ ታማኝ እንደሆነ ነው። ስለሆነም ታሪኩ አደርጋለሁ ያለውን የሚያደርግ መልካም ሰው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ታሪኩን ከኢ-ፍፁምነት አንጻር ስንመለከተው ፍፁም ሆኖ ተስሎ እናገኘዋለን። ይህም ገጸባህርያት ሲሳሉ ኢ-ፍጹም ሆነው መሳል አለባቸው ከሚለው ቴክኒክ አንጻር ልብወለዱ ላይ በሰፊው እንደተስተዋለ የልብወለዱ ደካማ ጎን መጥቀስ ይቻላል።

## 3.3. ሽማግሌው (ራትና መብራት)

ሽማግሌው በልመና የሚተዳደሩ አዛውንት ናቸው። የሚመራቸውና ወደ ሚፈልጉበት ቦታ የሚያደርሳቸው የአምስት ዓመቱ የልጅ ልጃቸው ነው። እሳቸው ደግሞ በምላሹ ለትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን በማሟላት ይደግፉታል። በዚህ ታሪክ ውስጥ በዋናነት የሚታየው ዐይነ ስውሩ አዛውንት መሪያቸው የልጅ ልጃቸው እንደ ጓደኛቸው ልጅ እንዳይኮበልልባቸው የሚያደርጉትን ጥረት ነው።

### 3.3.1. ገፀ ባህሪው ከግለ ወጥነት አንፃር

ሽማግሌውን ከግለ ወጥነት አንፃር ስንመረምራቸው ከሌሎች ገፀ ባህሪያት ተለይተው የሚታወቁበት ግለ ወጥ ባህሪ አላቸው። አስረጅ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

> "ጥሩ ልጆች የማይሆኑ ልጆች ግን ፈጣሪ ይቀጣቸዋል። በምድር ላይ ረሀብተኞችና ተቅበዝባዦች ይሆናል። አይወልዱም አይከብዱም።
>
> አንድ ልጅ አያቱን ከድቶ ተሆነ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር 'በእርጅና ዘመኑ የታወረውን አያትህን ለምን ከዳህ?' ብሎ ይጠይቀዋል። ልጁም የሚመልሰው

> አይኖረውም። ተዚያማ... ሲያል መግባት ዕጣ ክፍሉ ይሆናል። በዕውቀቱ (1995፣ 101)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሽማግሌው የልጅ ልጃቸውን ልብ ለማለዘብ የሚያደርጉትን ጥረት ነው። የባልንጀራቸውን የዝምበላቸውን ታሪክ ከሰሙ ወዲህ ከባድ ፍርሀት ውስጥ ወድቀዋል። የፍርሀታቸው ምንጭ ደግሞ ጥሎኝ ቢሄድስ? የሚል ስጋት ነው። ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ሽማግሌው ምንም እንኳን መሪያቸው ጥሏቸው የትም ለመሄድ ባያስብም ትልቅ ስጋት ይዟቸዋል፡፡ ይህ አስተሳሰባቸውም ሽማግሌው ከሌሎች ገፀባህሪያት የሚለዩበት ግለ ወጥ የሆነ ባህሪያቸው ነው፡፡ ታሪኩን አንብበን ከጨረስን በኋላም አእምሯችን ላይ የሚቀረው ብቸኛው ምስል የሽማግሌው ስጋትና ፍርሀት ብቻ ነው።

## 3.3.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር

በ"ራትና መብራት" ልቦለድ ውስጥ እንደዋና ገፀባህሪያት ከተሳሉት ገፀባህሪያት መካከል አንዱ የሆኑትን ሽማግሌውን ከዘላቂነት አንፃር ስንመረምራቸው የባህሪ፣ የድርጊትና የአቋም ዘላቂነት የሚታይባቸው ሆነው ተስለዋል፡፡ ደራሲው ገፀ ባህሪውን ሲስል በባህሪ፣ በምግባር በአጠቃላይ እንቅስቃሴአቸው ዘላቂ የሆነ አቋም አላብሷቸዋል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፡፡

> "ቀበሮ የማሰው ጉድጓድ አደናቅፎት ሲወድቅ ጥርብ ድንጋይ አግኝቶ ጭንቅላቱን ተረተረው!"
>
> "በስመ አብ ወወልደ መንፈስ ቅዱስ! ያለ መሪ ምን አስከጀለው?"
>
> ውስጣቸው በድንጋጤ ተናጠ። ድንገት የዝምበላቸው ገጽታ በሀሳባቸው መስኮት ብቅ አለ። ኧ ብሎ ተኝቶ፣ ከጭንቅላቱ የፈሰሰው የረጋ ደም ፊቱ ላይ ደለል ሰርቶ፣ እንደ ዐይኑ ብርሃን የልቡ ተስፋ ጠፍቶ... በዕውቀቱ (1995፣ 102)

ከጥቅሱ የምንረዳው ሽማግሌው ስጋታቸው የተዋረሳቸውን ቅጽበት ነው። ሽማግሌው ከዚህ በፊት ይህን መሰሉ ገጠመኝ የማያስፈራቸው፣ በፈለጉት ጊዜ የልጅ ልጃቸው የሚመራቸው፣ ይኮበልላል የሚል ስጋት ያልተዋረሳቸው ሰው ነበሩ። ውብ ሊቀር ይህንን የባልንጀራቸውን መሪ መኮብለልና ጭንቅላት መተርተር ከነገራቸው በኋላ ግን ፍርሀት

በመላ ሰውነታቸው ሲሰፍር እንመለከታለን። ሽማግሌው ልጁ ከኮበለለ የሚገጥማቸውን ፈተና አስበው ለልጅ ልጃቸው ያላቸውን ሁሉ ይሰጡታል።

> ....ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ 'ደሞ የምን ስፖርት ነው?' ብለው ኩም ያረጉት ነበር። ዛሬ ግን ሳግ በተቀላቀለበት ድምፅ "ምን ያህል?" ብለው ጠየቁት።
>
> "እንደተገኘው... አምስትም አራትም ሦስትም"
>
> ሀሳብ ገባቸው።
>
> "ሁለት ይበቃህ ይሆን?"
>
> "እኔንጃ ይበቃኝ ይሆናል!"
>
> በዕውቀቱ (1995፣ 108)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ምርጫ ያጡት አዛውንት የመሪያቸውን ልብ ለመግራት ሲሉ ቀኑን ሙሉ የሰሯትን አምስት ብር ሲሰጡት እንመለከታለን። ይህም እንዲሁ በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን ጥሎኝ ቢሄድስ ከሚል ስጋት የመነጨ ነው። እሳቸውም ራታቸውን በመብራት ሲለውጡ እንመለከታለን። ይህም የሽማግሌው ስጉ ባህሪያቸው ዘላቂና የማይለወጥ ነው። በአጠቃላይ ሽማግሌውን ከዘላቂነት ባህሪ አንፃር ስንመረምራቸው የባህሪ ዘላቂነት ይስተዋልባቸዋል ።

## 3.3.3. ገፀ ባህሪው ከኢ-ፍፁምነት አሳሳል አንፃር

ሽማግሌውን ከኢ-ፍፁምነት አንፃር ስንመረምራቸው በባህሪ፣ በአቋምና በአስተሳሰብ ኢ-ፍፁምነትን ተላብሰው እናገኛቸዋለን። ለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን እንመልከት።

> የባልንጀራቸው የዝምበላቸው ስዕል ህሊናቸው ውስጥ ገዘፈ። አወዳደቁ! እንደ ዋርካ በቁሙ ሲገነደስ ምድር ላይ የተተከለ ስል ድንጋይ ከታች ሲቀበለው...
>
> "አያቴ!"
>
> "አቤት አቡዬ!"
>
> "ደብተሬና እስክርቢቶ ሊያልቅብኝ ነው!"

ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ "አንድ ቀን ይገዛልሃል!" ብለው ያዘናጉት ነበር፡፡ አሁን ግን ግብራቸውን ለወጡት፡፡ እጃቸው ወደ ኪሳቸው ፈጠነ፡፡

"በል ባለ አስራ ስድስት ሉክ ደፍተር እና አንድ እርሳስ ገዝተህ ና!"

የጠወለገች የሰንሰል ቅጠል የመሰለችውን አሮጌ ብር ተቀብሏቸው ቱር ብሎ ሄደ፡፡

በዕውቀቱ (1995፣ 103-104)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሽማግሌው ሁልጊዜ ፍፁም አሸናፊ ብቻ እንዳይደሉና አንዳንዴ ልክ እንደ ገሀዱ ዓለም ሰው ሁሉ ተሸናፊ እንደሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ሽማግሌው በልቦለዱ ውስጥ የኢ-ፍፁምነት ባህሪን ተላብሰው የተሳሉ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ከፈሪው ድፍረት፣ ከቀጣፊው እውነት፣ ከሀቀኛው ውሸት፣ ከጀግናው ፍርሀት፣... አይጠፋም እንዲሉ ከዚህ ቀደም ግድ ያልነበራቸው አዛውንት ልባቸው በፍርሀት ሲናጥ፣ ያለልማዳቸው ሲለሳለሱ፣ ... እንመለከታለን፡፡ ይህም ዓይነቱ የኢ-ፍጹምነት ባህርይ ማንኛውም ዓይነት የገሀዱ ዓለም ሰው ላይ የሚንጸባረቅ በመሆኑ ሽማግሌው ከባህሪ ኢ- ፍጹምነት አንጻር በተገቢው መንገድ ተስለዋል ማለት እንችላለን፡፡

የአዛውንቱ ኢ-ፍጹምነት በጉልህ የተንጸባረቀበት ሌላኛው የልቦለዱ ክፍል አዛውንቱ ህጻኑን በገሃነም እሳት የሚያስፈራሩበት ክፍል ነው፡፡ አካል ጉዳተኛው የባልንጀራዬ እጣ ይገጥመኝ ይሆናል፤ መሪዬ ሊኮበልል ይችላል የሚለው ስጋት መጽሀፍ ላይ የሌለ ነገር እያጣቀሱ ወላጆቹን አልታዘዝም ያለን ህጻን እግዚአብሄር እንዴት እንደሚቀጣው፣ ወላጆቹን የሚታዘዘውን ልጅ ደግሞ እንዴት እንደሚክሰው ሲተርኩለት እንታዘባለን፡፡ ይሄ የልቦለዱ ታሪክ ደግሞ የገጸባህሪውን ኢ-ፍጹምነት ከማንጸባረቅ ባሻገር ፍልስፍናዊ አንድምታም አለው፡፡ ጥሩ የሰራ በሰማይ ቤት ይካሳል፣ መጥፎ የሰራ ደግሞ በሰማይ ቤት ይቀጣል የሚለው ሃሳብ መነሻው ተመሳሳይ ታሪክ ይሆንን? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡ ይሄ ደግሞ ዓይነ ስውራን የእለት ጉርሳቸው ለማግኘት የሚከፍሉትን ውጣ ውረድ እንዲሁም ያለውን ፈተና ያሳየናል፡፡ የአዛውንቱ ማባበያ ዘዴ ደግሞ የሰውን ልጅ ተፈጥሮና በህይወት ለመኖር የሚያደርገውን መፍጨርጨር ያንጸባርቃል፡፡

## 3.4. አሮጊቷ

ሰባት ጊዜ ወልዳ ሰባቱም በህጻንነታቸው ሞቱባት:: ለስምንተኛ ጊዜ ጸነሰች:: ይሄኛው ያደገላት መሰለ:: ቆንጆና ጤናማ ህጻን ሆኖ አደገ:: እየቆየ ግን ህመም ያመው ጀመረ:: እናትም ተደናግጣ አዋቂ ጋር ወሰደችው:: አዋቂውም "አዲስ አበባ የሚባል ረሀብና በሽታ የሌለበት ከተማ አለ እዛ ውሰጅው" አላት:: እናትም ልጇን ይዛ አዲስ አበባ ገባች:: ህጻኑም ወደ ጤንነቱ ተመለሰላት:: እናትም እንጨት እየሰበረች፣ ጠላ እየጠመቀች ልጇን አስተምራ አሳደገችው:: በትምህርቱም በርትቶ፣ ጥሩ ሥራ ይዞ፣ ሚስት አግብቶ መኖር ጀመረ:: እናት ስታረጅ የዐይን ብርሃኗን ስታጣ አብራው እንድትኖር ያደርጋል:: ሚስት ግን በዚህ ለውጥ ደስተኛ አልነበረችም:: ከተወለደችለት በኋላም በልጁና በእናቱ መካከል እንዲመርጥ ትጠይቀዋለች:: እናትም "ሀገሬን ጥዬ የጠፋሁት ለልጄ ነው እሱንም የልጅ ፍቅር እናቱን እንዲገፋ ያስገድደዋል:: ከማስኮንነው ብጠፋ ይሻላል::" ብላ ቤቱን ጥላ ትጠፋለች::

ዐይነ ስውሯ አሮጊት ቤተክርስቲያን በር ላይ ቆመው ሲለምኑ ይውላሉ:: እንደመታደል ሆኖ በሚኖሩበት ሠፈር ሰዉ ሁሉ ይወዳቸዋል:: ሴቶች ቡና ያፈሉላቸዋል:: አንዱ ባለ ጸጋ ደግሞ ማደሪያ ተሰጥቷቸዋል:: ሲያልፉ ሲያገድሙ ደግሞ የሚመራቸው ሰው ሞልቷል:: …

### 3.4.1. ገጸባህሪዋ ከግለወጥነት አንፃር

አሮጊቷን ከግለወጥነት አንፃር ስንመረምራቸው ከሌሎች ገፀባህሪያት ተለይተው የሚታወቁበት ግለወጥ ባህሪ አላቸው:: አስረጅ ይሆነን ዘንድ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት::

> "ይኸውልህ፣ ሰባት ወለድኩና ሰባቱም ሞቱ:: ስምንተኛ እንደወለድኩ አዋቂ ቤት ሄድኩ:: አዲሳባ 'ሚሉት አገር ሂጂ፣ እዚያ ሞት የለም፣ አሉኝ:: አንድ ቀን ሳልውል፣ ስንቄን ጨርቄን ሳልል ተነሳሁና ወደ አዲሳባ መንገዴን አቀናሁ:: ሞት እንዳይደርስብኝ፣ ልጄን እንዳይወስድብኝ፣ ስሄድ ሰንብቼ ስሄድ ከርሜ፣ ምግቤንም መጠጊያዬንም እየለመንኩ ስሄድ ከርሜ፣ ሰኔ ሚካኤል ካገሬ የወጣሁ ለህዳር ተክለሃይማኖት አዲሳባ ገባሁ::"

> "እንደተባለውም አዲሳባ ሞት የሌለበት አገር ሆነና፣ ልጄ አደገልኝ። እንጨት ከጫካ እየለቀምኩ፣ ጠላ ከገብስ እየጠመቅኩ፣ እንጀራ በጉልት እየሸጥኩ አሳደግኩት። ሰው ሆነ። ለሰው ወግ ደረሰ፤ ሚስት አገባ" ስብሃት (2004፣ 63)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ገጸባህሪዋ በብዙ መከራና ችግር ውስጥ አልፋለች። ልጇን ለማሳደግ አገር ለቃለች። ያን ሁሉ መሰዋዕትነት ከፍላ ግን ማግኘት የሚገባትን ክብር አላገኘችም። በሚስትና በምራት መካከል ምን እንደተፈጠረ ሙሉ ታሪክ ባይኖርም ለአሮጊቷ መጥፋት የአንበሳውን ድርሻ የምትይዘው ምራት ናት። ይሄ ደግሞ አሮጊቷን እንደ ተበዳይ እንድንመለከታቸው ያደርገናል። ተበዳይነትም ገጸባህሪዋ ከሌሎች ገጸባህርያት ተለይታ የሚታወቁበት ግለወጥ ባህሪ አላቸው።

## 3.4.2. ገጸባህሪዋ ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር

በ"ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ" ልቦለድ ውስጥ እንደዋና ገፀባህሪ ከተሳሉት ገፀባህሪያት መካከል አንዷ የሆነችው አሮጊቷ ከዘላቂነት አንፃር ስንመረምራት የባህሪ፣ የድርጊትና የአቋም ዘላቂነት የሚታይባት ሆና ተስላለች። ደራሲው ገፀባህሪዋን ሲስል በባህሪዋና አስተሳሰቧ ዘላቂ አድርጎ ስሏታል። ይህን ለማረጋገጥ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

> "ዋ ልጄ! ከዚያማ ሚስት ሳትፈልገኝ ቀረች። ከንግዲህ ምን ልረባ? ለራሴ አሮጊት! ቤት ከማጣበብ፣ እንጀራ ከመፍጀት አልፌ ምን ልጠቅማት? አልፈጭላት፣ አልጋግርላት። አንድ ወለደችና፣ ባል ልጁን መውደዱን እርግጠኛ ከሆነች በኋላ፣ እቺን አሮጊት ካላስወጣህልኝ ፍታኝ አለችው"
>
> "እና አስወጣዎት?"
>
> "እኔ ወጣሁለት 'ንጂ። ለምን ላስኰንነው? የልጅ ፍቅር አይደል አገሬን፣ ጕረቤቴን ጥዬ እንድኮበልል ያደረገኝ? እሱንም የልጅ ፍቅር እናቱን እንዲያባርር ያረገዋል አልኩና፣ የገዛ እናቱ ሀጢአት ኩነኔ ከምሆንበት ብዬ፣ ወጥቼ ጠፋሁ"

ልጃቸውን ሞት እንዳይበላው ካገራቸው ከወንዛቸው ኮበለሉ፣ ገሃነም እንዳይበላው ደሞ ከልጃቸው ከራሱ ኮበለሉ "እውነትም የናት ፍቅር" ብለው አሰቡ አቶ ወንዳፍራሽ

ከጥቅሱ እንደምንረዳው፣ አሮጊቷ ምንም እንኳ ከልጇ ቤት ብትወጣም ለልጇ ያላት ፍቅር አልቀዘቀዘም። ልጇ ስላልተከላከላት አልጠላችውም። እሱንና ሚስቱን በመኮነን ፋንታ ራሷን በሱ ቦታ አድርጋ የወሰነው ውሳኔ ፍትሀዊ መሆኑን መሰከረች። ስለዚህ አሮጊቷ ልቦለዱ ውስጥ የባህሪ ዘላቂነት አላት ማለት እንችላለን። ምክንያቱም እንዲህ አይነት ሚዛናዊ ፍርድ መፍረድ የሚችለው በዚያ ሰው ቦታ ራሱን አስገብቶ የሚያውቅ ሰው ብቻ ነው። አሮጊቷ ደግሞ ከአንድም ሁለቴ እንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ነበረች። ይህም የአሮጊቷ ባህሪ ከልብወለዱ ጅማሮ ፍጻሜ ድረስ ሲዘልቅ እንመለከታለን።

## 3.4.3. ገጸ ባህሪዋ ከኢ-ፍፁምነት አሳሳል አንፃር

አሮጊቷን ከኢ-ፍፁምነት አሳሳል አንፃር ስንመረምራት በአቋሟና በአስተሳሰቧ የፍፁምነት ባህሪ ተላብሳ እናገኛታለን። ገጸባህርያት የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ ናቸው። ሲሳሉም ያንን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት። ፍጹም ክፉ ወይም ፍጹም ገራም አድርጎ ማቅረብ ደግሞ በገሀዱ ዓለም ካለው እውነታ ጋር ይጣረሳል። አሮጊቷ ፍጹም ደግ ተደርጋ ተስላለች። ኢ-ፍጹም ሊያደርጋት የሚችል ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ስለገጸባህሪዋ ያለን መረጃ በአንደኛ መደብ (ከራሷ ከገጸባህሪዋ) ብቻ የተገኘ በመሆኑ ነው። ይህም እንደ ልብወለዱ ደካማ ጎን ተስተውሏል።

## 3.5. ውብቴ

ውብቴ ነዋሪነቱ አዲስ አበባ ውስጥ የሆነ በልመና የሚተዳደር ዐይነ ስውር ነው። የሚለምነው ከመጠጥ ቤት መጠጥ ቤት እየተዘዋወረ ስለሆነ የግድ መሪ ያስፈልገዋል። ለረጅም ጊዜ ይመራው የነበረው ጎረቤቱ ሲሆን ከእለታት አንድ ቀን ግን ጎረቤቱ ለሌላ ሥራ ይወጣና መሪ ለመፈለግ ይገደዳል። ውብቱ ለምኖ ከሚያገኘው ላይ የተወሰነ ለመሪዎቹ ይከፍላል። እንደ አጋጣሚ ታድያ በአንድ ቤተክርስቲያን ደጃፍ በሚያልፍበት ወቅት አንድ ከክፍለ ሀገር ኮብልሎ የመጣ ታዳጊ ያገኛል። ታዳጊው ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ ስለሌለው ውብቴን ለመምራት ይወስናል። … የልብወለዱ ታሪክም ታዳጊው ውብቴን

ባገዘባቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ ያሳለፈውን ውጣውረድና የልመና ህይወትን ፈታኝ ገጽታ ያሳያል።

## 3.5.1. ገፀባህሪው ከባህሪ ግለወጥነት አንፃር

ከግለወጥነት አንጻር ስንመለከተው፣ ውበቴ ከሌሎች ገጸባህርያት ተለይቶ የሚታወቅበት የራሱ የሆነ ግለወጥ ባህሪ አለው። ውበቴ በጠባዩ ቁጡና ደፋር እንዲሁም ለመናገር የሚፈልገውን ከመናገር ወደኋላ ከማለት የማይቆጠብ ሲሆን በሁኔታው ግን የሰዎችን አንጀት በቀላሉ የሚበላና ምስኪንነት የሚታይበት ገጸባህሪ ነው። ውበቴን ከሌሎች በልመና ከሚተዳደሩ አካል ጉዳተኞች ለየት ከሚያደርጉት ጠባያቶች መካከል በአለባበሱ፣ በሁኔታው ምስኪን መሆኑ ዋነኛው ነው።

ዐይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ፣

ይችግር የለም ወይ መሪ ማባበሉ፣

ራቴም ምሳዬም ሆኖ በሰው እጅ፣

አልቅሼ እበላለሁ፣ እንደ ሕፃን ልጅ።

ሙሉ አካል ነበረኝ እኔም እንደ ሰው፣

አምላክ ወሰደብኝ የማይከሰሰው።"

የልመና ግጥም ማለቂያ የለውም። ለዚያውም ምኑ ይጥም ብለህ ነው? ውበቴ ይበልጥ የሚያሳዝን እንዲህ ሲል ነው።

"ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም፣

ዕንጨቱም ድንጋዩም ከሰው ፊት አይከብድም።" አውግቼው (2011፣ 100-101)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውበቴ ለልመና የተገደደው ምንም አማራጭ ስለሌለው ነው። ውበቴ ሌሎች እንደሚሉት አይደለም። የሚያውቁት ሁሉ ውበቴ መለመን ይወዳል፤ ውበቴ መጠጣት ይወዳል ይሉታል። አውግቼው (2011፣ 104) እውነቱ ግን እሱ አይደለም።

ውበቴ ባለትዳር ነው። የሚያስተዳድረው ቤተሰብ አለው። የሚለምነው ቤተሰቡን ለማስተዳደር ነው። ውበቴ ብልህ ነው። ብልህነቱ ታድያ የትምህርት ወይም የሌላ አይነት አካዲያሚያዊ ብልህነት አይደለም። ሰዎችን በደንብ ያውቃል። ውበቴ አለማመን ይችላል። ከሰዎች እጅ እንዴት ብር ማግኘት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። ይሄን የመሰለውን አመለካከትና አቋም ማዳበሩም ከአንድ በደሀ ሀገር ላይ ከሚኖር አካል ጉዳተኛ የሚጠበቅ በመሆኑ ደራሲው በአግባቡ ስሎታል ማለት እንችላለን። ተጨማሪ ጥቅስ እንመልከት፦

> ...ደግሞ አዲስ ልብስ መልበስና ጫማ ማድረግ የለብህም። አሮጌ ልብስና አሮጌ ጫማ እንኳ የሌለው ኩሊ ሞልቷል። ታድያ በባዶ እግሩ እየሄደ ላንተ የሚመጸውት ይመስልሃል? አይደለም። የሚመጸውትህ ከሱ ስታንስ መሆኑን አትዘንጋ። ባለባበስም ማሳዘን አለብህ። አውግቼው (2011፣ 114)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውበቴ የእለት ጉርሱን ለማግኘት ሲል ራሱን ዝቅ አድርጎና ማህበረሰቡን መስሎ ለመኖር ሲገደድ እንመለከታለን። ይህም አንድም ማህበረሰቡ ለአካል ጉዳተኞች ያለውን ቦታ ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ የውበቴን ብልህነትና የእለት ጉርሱን ለማግኘት ሲል የሚከፍለውን ውጣውረድ ያሳያል።

ከውበቴ ግለወጥ ባህርያቶቹ መካከል ጠርጣራነቱ ሌላኛው ነው። ውበቴ ሲበዛ ጠርጣራና ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ከመመልከት የማይቆጠብ ሰው ነው።

> "የጃንሆይ ብር ይሰጣል ወደሚባልበት ቦታ እንዳትወስደኝ" አለኝ።
>
> "ለምንድን ነው ጃንሆይ ለድሆች አዝነው ብር ሲመጸውቱ እርስዎ አልቀበልም የሚሉ?" ብዬ ጠየቅሁት።
>
> "አንተ የእንትናን (የለማኝ አለቃውን ስም ጠርቶ) ዘዴ አታውቅም። አዝነው መሰለህ? አይደለም።..." አውግቼው (2011፣ 100)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውበቴ ከንጉሡ (ከመንግሥት) የሚደረግለትን እርዳታ አምርሮ ሲቃወም እንመለከታለን። ከእርዳታው ጀርባ ሌላ የተሸረበ ተንኮል ያለ ይመስለዋል። ይሄም የውበቴን ብልህነትና ጥንቁቅነት እንዲሁም የሞራል ልዕልና ያሳያል። በጃንሆይ ዘመነ መንግስት ትልልቅ አህጉራዊ ስብሰባዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የከተማይቱን ብሎም

የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት ሲባል አካል ጉዳተኞች እየተሰበሰቡ ይታጎሩ ነበር። ውብቴ እንደሌሎች ባልንጀሮቹ በቁራኝ ሳይታለል ከመንግሥት ወኪሎች እገታ ራሱን የሚጠብቅበትን ዘዴ ዘይዷል። ይሄም የገጸባህሪውን ብልህነትና ጥንቁቅነት ያሳያል። እኒህም የገጸባህሪው ባህሪያት ከሌሎች ገጸባህሪያት ተለይቶ የሚታወቅባቸው ግለወጥ ባህሪያቶቹ ናቸው።

## 3.5.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር

በ"ወይ አዲስ አበባ" ልቦለድ ውስጥ እንደዋና ገፀባህሪያት ከተሳሉት መካከል አንዱ የሆነው ውብቴ ከዘላቂነት አንፃር ስንመለከተው የባህሪ፣ የድርጊትና የአቋም ዘላቂነት ይታይበታል። ደራሲው ገፀባህሪውን ሲስል በአስተሳሰቡና በአቋሙ እንዲሁም በአጠቃላይ እንቅስቃሴው ዘላቂ በሆነ መንገድ ስሎታል። ይህን ለማረጋገጥ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

> አንድ ላይ ተቀምጠን የዓርብ ዳቦ ስንጠብቅ፣ አንድ ዐይነ ሥውር ዱላውን እያወዛወዘ ወደኛ መጣ። የቤተክርስቲያኑ ዘበኛ ወዴት እንደሚሄድ ከጠየቀው በኋላ፣ "ሒድና መንገድ ዳር ያለውን የወይዘሮ ዓለምነሽን ጠጅ ቤት አሳየው" አለኝ በዱላ እየጎሸመኝ።...
>
> ዐይነ ሥውሩ ትክሻዬን ይዞ እንደ መከተል እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሂድ" አለኝ።
>
> ጠጅ ቤቱ ስንደርስ ሥራዬን ጠየቀኝ። ኩሊ መሆኔን ስነግረው፣ "እንግዲያውስ ከኩሊነት ልመና ይሻላልና እኔን ምራኝ" ብሎ እጄን አጥብቆ ይዞ ይለምነኝ ጀመር። አውግቼው (2011፣6)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውብቴ ከመሸከም መለመን እንደሚሻል የሚያምን፣ መጠጣት መስከር የሚወድ፣ ከገንዘብ ውጭ ሌላ ነገር የማይቀበል ሰው ነው። ይህ ባህሪያቶችና ድርጊቶች ታድያ ልቦለዱ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ የማይቀየሩ ዘላቂ ባህሪያቶቹ ናቸው። ውብቴ ታድያ መጠጣት፣ መስከር፣ መለመን፣... የሚወድ ብቻም አይደለም፤ ውብቴ ደፋርም ነው። መሪዎቹ ከዚህ ሁሉ ሰው መሀል ቆመን መለመን አፈርን ሲሉት እንዲህ እያለ ያበረታታቸዋል፦

> "ደግሞ ምን ያሳፍርሃል? አልሰረክ፣ አልቀጠፍክ፣ እኔ ለለመንኩ አንተ ምን ያሳፍርሃል? ይልቅስ እንደ አህያ ከመሸከም፣ ለምኖ መብላት አይሻልም? አውግቼው (2011፣ 97)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውብቴ በልመና ዙሪያ የማይናወጽ አቋም አለው:: ከመስራት መለመን እንደሚሻል ደጋግሞ ይገልጻል:: ይህ ጠባዩም እስከ ታሪኩ ፍጻሜ ድረስ ይዘልቃል:: ከዚህና ከመሳሰሉት በልብወለዱ ውስጥ ዘላቂነት ካላቸው ድርጊቶችና ባህርያቶቹ በመነሳት ውብቴ ከባህሪ ዘላቂነት አኳያ በአግባቡ ተስሏል ማለት እንችላለን::

## 3.5.3. ገጸባህሪው ከባህሪ ኢ-ፍፁምነት አንፃር

ኢ-ፍጹምነት ገጸባህርያት ሲሳሉ መረሳት ከሌለባቸው ቁምነገሮች መካከል አንዱ ሲሆን ገጸ ባህርያት የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ እንደመሆናቸው መጠን በመልካቸው፣ በባህሪያቸው፣ በአመለካከታቸው ሆነ በሌሎች መለያ ባህርያቶቻቸው ፍጹም ሆነው መሳል የለባቸውም የሚል ነው:: ከብርቱው ድካም ከሀቀኛው ቅጥፈት፣ ከስግብግቡ ልግስና፣ ከጨካኙ ርህራሄ፣ ከምስኪኑ ተንኮል… አይጠፉምና ገጸባህርያትም ሲሳሉ ይሄንን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት::

ውብቴ ከኢ-ፍጹምነት አንጻር እንዴት ተስሏል?

የገጸባህሪው ግለወጥ ባህሪ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ ውብቴ በልመና የሚተዳደር ምስኪን ዐይነ ስውር ነው:: ይህ ሲባል ግን ውብቴ ሁልጊዜ ምስኪን ነው ማለት አይደለም:: ውብቴ አንዳንድ ጊዜ ከአዘቦት ጠባዩ ወጣ ያለ ነገር ያሳያል::

> ጡረታ ሠፈር የለማኞች ሠፈር ነው:: እቤት እንደደረስን ከዚህ ቀደም ይመራው የነበረው ሰውዬ ሲፈልገው ኑሮ፣ ዐይነ ስውሩ ሰውዬ ቤት ውስጥ ተቀምጦ አገኘነው:: እኔን አይቶ አዝኖልኝ ይሁን፣ ተመቀኝቶ እንዲህ አለኝ:: "ምናልባት የውብቴን ጠባይ አታውቀውም ይሆናል:: በጣም ርጉም ሰው ነው:: መለመን፣ መስከር፣ መረበሽ ያበዛል:: እንኳን አንተ እኔንኳ እየመከርኩና እያስፈራራሁ አልቻልኩትም:: ሲጠጣ እብድ ነው:: ካልጠጣ ደግሞ መንቀሳቀስ አይችልም:: አውግቼው (2011፣ 98)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውበቴ  የሆነ የመጠጥ ሱሰኛ ነው። ጠጥቶ የመስከር፣ የመረበሽ አባዜ አለበት። ይህም ውበቴ ሁልጊዜ ምስኪን፣ ሁልጊዜ የዋህ፣ ሁልጊዜ ብልህ፣... እንዳልሆነና እንደማንኛውም ሰው ኢ-ፍጹም እንደሆነ ያስረዳናል። ይህንን ጽንሰሀሳብ በደንብ የሚገልጽልን ሌላ ተጨማሪ ጥቅስ ደግሞ እንመልከት።

> ውበቴ ...አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የልጅ የመሰለ ጥያቄ ይጠይቃል። "ሴቶችና ወንዶች በምን ተለይተው ይታወቃሉ?"
>
> "በብዙ ነገር ይለያያሉ። ሴቶች ድምጻቸው ቀጭን ነው። ጉትቻ ያደርጋሉ። ጸጉራቸውን ያሳድጋሉ። ይተኮሳሉ። ሻሽ ያስራሉ። ቀሚስ ይለብሳሉ፣ የሴት በርሜ ይይዛሉ። መልካቸው ያምራል። ሲስቁ ያምራሉ።..." አልኩት። አውግቼው (2011፣ 104)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ውበቴ የልጅ የመሰሉ ጥያቄዎች ሲያነሳ እንመለከታለን። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ገጸባህሪያት የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ እንደመሆናቸው መጠን ፍጽምና (Perfection) የላቸውም። *ከአዋቂው ሞኝነት፣ ከቂል ብልሀነት አይጠፋም* እንዲሉ እንዲህ ዓይነት የነገሮች መዛነቅን ማየታችን የተለመደ ነው። ከዚህ በመነሳት ውበቴ ከኢ-ፍጹምነት አንጻር በተገቢው መንገድ ተስሏል ማለት እንችላለን።

## 3.6. በርጠሎሜዎስ (የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ)

በርጠሎሜዎስ ከሌሎች ገጸባህርያት ለየት የሚያደርገው መጽሀፍ ቅዱሳዊ መነሻ ያለው መሆኑ ነው። በሀዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሷቸዋል ተብለው ከሚታመኑ አካል ጉዳተኞች መካከል በርጠሎሜዎስ አንዱ ነው። በርጠሎሜዎስ እድሜ ልኩን ዐይነ ስውር ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ታድያ ታምራት ይሰራል ስለሚባል የናዝሬት ሰው ይሰማል። በመንገድ ሲያልፍም "ኢየሱስ! ኢየሱስ!" ብሎ ይጠራውና የታዕምራቱ በረከት ይደርሰዋል። ዓይኖቹም ይገለጣሉ። ለመጀመሪያ ጊዜም በዙሪያው ያለውን ዓለም ይመለከታል። ደስም ይሰኛል። ይሁን እንጂ ደስታው ብዙ አልዘለቀም። የሚያየው ነገር በሙሉ ልቡን ያሳዝነው ይጀምራል። ዓለም ኢ-ፍትሀዊ እንደሆነች ይረዳል። ዐይኖቹ እንዲገለጡ የፈለገበትንም ቀን ይረግማል። ...

### 3.6.1. ገጸባህሪው ከባህሪ ግለወጥነት አንፃር

በርጠሎሜዎስን ከግለወጥነት አንፃር ስንመረምረው ከሌሎች ገፀባህሪያት ተለይቶ የሚታወቅበት የራሱ የሆነ ግለወጥ ባህሪ አለው፡፡ አስረጅ ይሆነን ዘንድ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፡፡

> በጨለማው ጊዜ የማውቀውን መንደሩን፣ ምኩራቡን ሁሉ በዐይኔ ዐየሁት፡፡ በጆሮዬ ብቻ ነበር ለመረዳት የምሞክረው፡፡ የታሸገ ስልቻ ውስጥ እኖር እንደነበር ቆጠርኩት፡፡ ግን ብዙ አልቆየ መገረሜ፤ ወዲያው ዐይናማ ሆኜ የተፈጠርኩ ያህል ዕውርነቴን እረሳሁት፡፡ ሁሉን ነገር ዐየሁት፡፡ አቤት ስንት ጉድ ነገር ተፈጥሯል፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ መኖር አልፈልግም፤ ባላይ ይሻለኝ ነበር፡፡ አሁን ያን የጨለማው ዘመኔን ናፈቅሁ፡፡ ፈጽሞ መታወር እፈልጋለሁ፡፡ ዳንኤል (2007፣ 38)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው በርጠሎሜዎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ማየት ሲችል ማንኛውም ዓይነ ስውር ሊሰማው ይችላል ብለን የምንገምተውን ዓይነት ግብረ መልስ (reaction) ሲያሳይ እንመለከታለን፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ብርሃንን መለየት መቻል ምን ዓይነት ስሜት ሊያሳድርብን ይችላል? ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማይ ምድሩን፣ ሰዉን እንሰሳዉን፣ ወንዙን ተራራውን… ማየት የሚያሳድረው ስሜት ምን ይመስላል? በርጠሎሜዎስ በአድናቆት ሲሞላ እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን በርጠሎሜዎስ በጆሮው ለመረዳት ሲሞክረው የነበረው ዓለም ከእውነታው ጋር በእጅጉ የሚጣረስ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ “በዚህ ዓለም ውስጥ መኖር አልፈልግም፤ ባላይ ይሻለኝ ነበር” የሚለን በርጠሎሜዎስ በአይኖቹ የሚያየው አለም በጆሮው ገንብቶት ከነበረው አለም ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም ሆኖበታል፡፡ ይሄን የዓለም ፍርደ ገምድልነት ከማየት ይልቅ መታወር እንደሚሻል ደጋግሞ ይነግረናል፡፡ ዓይኖቹን በገዛ እጆቹ ለማጥፋትም ከጅሎት ነበር፡፡ ተጨማሪ ጥቅስ እንመልከት፦

> በገዛ እጄ ዐይኖቼን ላጠፋቸው ብዙ ጊዜ ከጅሎኝ ነበር፡፡ …ግን ዐይኔን ባጠፋውም ከውስጤ፤ ከመታወሬ በፊት የነበረኝን ስለዚች ዓለም ሥዕል መልሼ ላመጣው እንደማልችል ይሄ ሽባ ጓደኛዬ አረዳኝ፡፡ እሱ ምንም አልጎደለበትም፡፡ የሚያውቀው ዓለም ነበር፡፡ መሮጥ ነበር የተነፈገው፣ እሱንም

አገኘ። የተፈወሰ እለት መንደርዋን በሩጫ አካለላት። አሁን ተሯሩጦ ነግዶ ይኖራል። ምንም የተቀማው ህልም የለም። እኔ ግን ፊት የነበረኝን ይህችን ዓለም በኀሊናዬ ሳያት የኖርኩትን ነው ያጣሁት። አሁን ደግሜ ራሴን ባሳውር ከመወለዴ ጀምሮ አእምሮዬ ውስጥ የነበረውን ሥዕል ማግኘት እንደማልችል ይህ ሽባው ጓደኛዬ 'አሁን አንድ ጊዜ ዐይተሀል። ታልማት የነበረችውን ዓለም በማየትህ ምክንያት ጠፍታለች። በድጋሚ ብትታወርም መልሰህ ፊት ታልም የነበረውን ልታይ አትችልም።" ብሎ አረዳኝ። ዳንኤል (2007፣ 38-39)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው በርጠሎሜዎስ ቀድሞ አካል ጉዳተኛ ከነበሩ ጓደኞቹ የተለየ ነው። ይሄም ከገጸባህሪው ግለወጥነት አንጻር በተገቢው መንገድ ተስሏል ለማለት ያስደፍረናል። ታድያ በርጠሎሜዎስን ከሌሎች ገጸባህርያት ለየት የሚያደርገው ከሌሎች ገጸባህርያት ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሪው ምንድን ነው? በርጠሎሜዎስ መታወር ይፈልጋል። የዚህን ዓለም ክፋት፣ ድንቁርና፣ መድልዎ፣ ስግብግብነት፣... ወደማያይበት የቀድሞ ዓይነ ስውርነቱ እንዲመለስለት ይፈልጋል። በርጠሎሜዎስ ባልለመደው ዓለም ከመኖር ይልቅ ቢታወር ይመርጣል። ይሄም የልብወለዱ ዋነኛ ማጠንጠኛ ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ገጸባህሪው ከሌሎች ገጸባህርያት ተለይቶ የሚታወቅበት ግለወጥ ባህሪው ነው።

## 3.6.2. ገጸባህሪው ከባህሪ ከዘላቂነት አንፃር

በ"ጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ" ልቦለድ ውስጥ በዋና ገጸባህርያትነት የተሳለው በርጠሎሜዎስ ከባህሪ ዘላቂነት አንፃር ስንመለከተው የባህሪ የድርጊትና የአቋም ዘላቂነት ይታይበታል። በርጠሎሜዎስ በአስተሳሰቡና በአቋሙ እንዲሁም በአጠቃላይ እንቅስቃሴው የባህሪ ዘላቂነት ይታይበታል። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው *ገጸባህሪው በኢየሱስ እጅ ከተፈወሰ በኋላ* ጸጸት ውስጥ ሲወድቅ እንመለከታለን። ዓለምን በማየቱ ደስ አልተሰኘም። ለዚህ የዳረገው ደግሞ ዓለም ላይ የሚያየው ፍርደ ገምድልነት ነው። በርጠሎሜዎስም ኢየሱስን ፍለጋ ባዝኗል። ሊያገኘው ግን አልቻለም። ይሄም የገጸባህሪው ግለወጥ ባህሪ ልብወለዱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ዘልቋል።

ፈጽሞ መታወር እፈልጋለሁ። አሁን የት ባገኘሁት? ከሰዎች ጋር ተቀላቅሏል። ... ደግና ሩሩህ ነው ብለው ብዙ ሰዎች ያወሩለታል። አሁን ግን

እፈልገዋለሁ። ፈጽሞ መፈወስ አልፈልግም። ደግሜ መታወር እፈልጋለሁ።... ሲያቀብጠኝ ነው የጮኽኩት፤ ሰው ሲያደርግ ዐይቼ። አሁን እፈልገዋለሁ። ያው የጨለማ ቤቴ ይሻለኛል። ያው አለማየቴ ይሻላል። ምን ለማየት ዐይኖቼን አበራው? ...ምንም የሚታይ ነገር የለም። እፈልገዋለሁ። እሱ አለ በተባለበት ቦታ ሁሉ፣ ደረሰ በተባለበት ቦታ ሁሉ እንደባከንኩ ነኝ" ዕውርነቴን ይመልስልኝ፤ በጨለማ ውስጥ ዐየው የነበረውን ሕልሜ ይሻለኛል። ዳንኤል (2007፣ 36-39)

ገጸባህሪያት ከገጸባህሪያት የሚለዩበት ግለወጥ ባህሪ እንዳላቸው ሁሉ ግለወጥ ባህሪያቶቻቸውም ከልብወለዱ ጅማሮ ፍጻሜ ድረስ ሲዘልቁ ገጸባህሪያቶቹ የባህሪ ዘላቂነት አላቸው እንላለን። ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው በርጠሎሜዎስ በኢየሱስ እጆች *የተፈወሰበትን* ቀናት ሲረግም እንመለከታለን። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የዐይን ብርሃኑን መልሶ ማጣት መፈለጉ የገጸባህሪው ግለወጥ ባህሪ ነው። ይህም የገጸባህሪው ግለወጥ ባህሪ እስከ ልብወለዱ ፍጻሜ ድረስ ሲዘልቅ እንመለከታለን። ከዚህም በመነሳት ገጸባህሪው ከባህሪ ዘላቂነት አንጻር በተገቢው መንገድ ተስሏል ማለት እንችላለን።

## 3.6.3. ገጸባህሪው ከባህሪ ከኢ-ፍፁምነት አንፃር

በርጠሎሜዎስ ከኢ-ፍፁምነት አንፃር ስንመለከተው በባህሪው፣ በአቋሙና በአስተሳሰቢ ኢ-ፍፁምነትን ተላብሶ እናገኘዋለን። ለዚህ ማስረጃ ይሆነን ዘንድ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

ሁለመናዬን አንዳች ነገር ወረረኝ። እጆቹን በዐይኖቼ ላይ አሳረፋቸው። 'እምነትህ አድኖሃል' ሲለኝ አመንኩ። እጆቹን ከዐይኔ ላይ ሲያነሳቸው ዐይኔ በብርሃን ተሞላ። ተገረምኩ። 'ያን ያክል እምነት አልነበረኝም፤ በእምነቴ ነው የዳንኩት?' አልኩኝ።

ፀሐይን ዐየኋት አጥወለወለኝ፣ ዞረብኝ። ሁሉንም ከበው የሚያዩትን አፍጥጬ ዐየኋቸው። እንደ ትንግርት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ ፊቱን፣ ጆሮውን፣ ትኩር ብዬ አየሁት። ድፍት ብዬ ለፍጥረታት ጌታ ሰገድኩ። ዐይኔን መጨፈን ግን አልፈለኩም። እንደገና አፈጠጥኩ።

'ተነስ እምነትህ አድኖሃል' አለኝ።

ተመልሼ እግሩ ላይ ወደቅሁ። አንዳች መገረም ሰውነቴን ወረረኝ። ዳንኤል (2007፣ 38)

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢ-ፍጹምነት ገጸባህርያት ሲሳሉ መረሳት ከሌለባቸው ቁምነገሮች መካከል አንዱ ነው። ጽንሰ ሀሳቡም ገጸባህርያት የገሀዱ ዓለም ሰዎች ነጸብራቅ እንደመሆናቸው መጠን በባህርያቸው፣ በአመለካከታቸው ኢ-ፍጹም ሆነው መሳል አለባቸው የሚል ነው። ከጥቅሱ ላይ ለመረዳት እንደምንችለው ኢየሱስ ለበርጠሎሜዎስ 'እምነትህ አድኖሃል' ሲለው 'እምነት ነበረኝ እንዴ?' ብሎ ራሱን ሲጠራጠር እንመለከታለን። ይህም የበርጠሎሜዎስ ጥርጣሬ፣ ገጸባህሪው እንደማንኛውም ሰው በራሱ ያለውን እምነት የሚጠራጠር መሆኑን ያሳየናል። እዚህ ላይ የታሪኩን እና የምንተስኖትን ታሪክ ማንሳት እንችላለን። ምንተስኖትና ታሪኩ ተወልደው ያደጉበትን አካባቢ ጥለው ከተሰደዱ በኋላ አለም እንዳሰቡት ቀላል ሆኖ አላገኙትም። የእለት ጉርሳቸውን እንኳ ለማግኘት ሲቸገሩ እንመለከታለን። ይሄ ደግሞ ገጸባህርያቱ በእግዚአብሄር ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው አድርጓቸዋል። በተደበቀ ሀብት ከመንበሽበሻቸው በፊት ታሪኩ ተማርሮ ራሱን ሊያጠፋ የሞከረበትን አጋጣሚ እናስታውሳለን። ይሄ ደግሞ ገጸባህርያቱ ምንም ያህል በልዕለ ተፈጥሮ ቢያምኑም በዚያው መጠን ደግሞ ጥርጣሬም እንዳለባቸው ያስገነዝበናል። ይሄ ደግሞ ገጸባህርያቱ እንደማንኛውም ሰው ጥርጣሬ ያለባቸውን ኢ-ፍጹም ናቸው ወደሚል ድምዳሜ ይወስዳል።

በዚህ ክፍል፣ ለአምስት ዐይነሥውራን ገጸባህሪያት (ታሪኩ፣ ሽማግሌው፣ አሮጊቷ፣ ውበቱ እና በርጠሎሜዎስ) ጥልቅ ትንተና ተካሂዷል። በሥነ ጽሑፍ ሂስ ውስጥ ተአማኒ ገጸባህሪን ለመፍጠር የሚያገለግሉትን ሦስት መሠረታዊ መመዘኛዎች – ማለትም ግለወጥነት፣ የባህሪ ዘላቂነት እና ኢ-ፍጹምነት – ምን ያህል እንዳሟሉ መመርመር ላይ ያተኮረ ነበር።

ግለወጥነት፣ አንድ ገጸባህሪ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት፣ የራሱ የሆነ ልዩ የአስተሳሰብ፣ የአነጋገር፣ የድርጊትና የአመለካከት አሻራ ነው። ከዚህ አንጻር፣ ትንተናው እንደሚያሳየው፣ አምስቱም ገጸባህሪያት ግለወጥ የሚያደርጋቸው ጠንካራ መሠረት ቢኖራቸውም፣ የአንዳንዶቹ አሳሳል ከሌሎቹ የበለጠ ተአማኒነት ያለውና ከጅምላ ፍረጃ (Stereotype) የጸዳ ሆኖ ተገኝቷል።

ጠንካራ ግለወጥነት (በውበቴ እና በሽማግሌው)፦

የውበቴ (ከ"ወይ አዲስ አበባ") ግለወጥነት፣ ዐይነሥውርነትንና ልመናን እንደ ውርደት ሳይሆን፣ እንደ "ሙያ" እና ከጉልበት ሥራ እንደሚሻል አድርጎ በፕራግማቲክ (Pragmatic) ፍልስፍና መቀበሉ ላይ ነው። እሱ "ምስኪን" ተረጂ ሳይሆን፣ የልመናን ጥበብ የተካነ፣ "ብልህ"፣ ሰዎችን እንዴት ማሳመን እንዳለበት የሚያውቅ፣ አልፎ ተርፎም ፖለቲካዊ ንቃተ-ህሊና ያለው (የ"ጃንሆይ ብር" ተንኮልን የሚረዳ) ገጸባህሪ ነው። ይህ አሳሳሉ፣ ከተለመደው የ"አሳዛኝ" ዐይነሥውር ምስል ፍጹም ያወጣዋል።

የሽማግሌው (ከ"ራትና መብራት") ግለወጥነት ደግሞ፣ በጥልቅ የሕልውና ፍርሃት ላይ የተገነባ ነው። የባልንጀራውን የዝምበላቸውን ታሪክ (በመሪ መከዳት) ከሰማ በኋላ፣ መሪውን (የልጅ ልጁን) ላለማጣት ሲል የሚጠቀመው "ስውር ተንኮል" (Subtle Manipulation) የእሱ ልዩ አሻራ ነው። ሃይማኖትን ተጠቅሞ ሕፃኑን በ"ሲዖል" ማስፈራራቱ፣ ዐይነሥውርነቱ የፈጠረበት ጥገኝነት፣ እሱን ከ"ተራ ምስኪን" አውጥቶ፣ ውስብስብ (Complex) እና እውነተኛ ግለሰብ እንዲሆን አድርጎታል።

ፍልስፍናዊ ግለወጥነት (በበርጠሎሜዎስ)፦

የበርጠሎሜዎስ (ከ"የጢሞቴዎስ ልጅ...") ግለወጥነት፣ ከሁሉም እጅግ ሥር-ነቀል ነው። የእሱ ልዩ አሻራ፣ ዐይነሥውርነትን እንደ "ሰላም"፣ ማየትን ደግሞ እንደ "ስቃይ" መቁጠሩ ነው። ዐይኑ ሲበራ ያየው የዓለም ክፋትና "ጉድ"፣ በጨለማ ሳለ የነበረውን "ህልም" ስለነጠቀው፣ ፈውሱን መጥላቱና ወደ ዐይነሥውርነቱ ለመመለስ መመኘቱ፣ የተለመደውን የ"ብርሃን = በጎ" ዘይቤ የሚገለብጥ አሳሳል ነው።

አርአያዊ ግለወጥነት (በታሪኩ እና በአሮጊቷ)፦ የታሪኩ (ከ"ምራኝና እንሂድ...") ግለወጥነት፣ ጥገኝነትን አጥብቆ መጸየፉ እና ከሸባው ምንተስኖት ጋር "ጉድለትን በጉድለት" የሚሞላ አጋርነት መፍጠሩ ላይ ነው። ይህ "ሸክም አልሆንም" የሚል ጠንካራ አቋሙ ልዩ ያደርገዋል።

የአሮጊቷ (ከ"ኤሊን ድንጋይ...") ግለወጥነትም፣ በተመሳሳይ፣ "ሸክም" መሆንን በመጥላት፣ የልጇን ትዳር ለማዳን ስትል፣ በክብር ራስን መስዋዕት አድርጋ ከቤት መውጣቷ ነው።

የግለወጥነት ክፍተት፦ በታሪኩ አሳሳል ላይ፣ ደራሲው ከጅምላ ፍረጃ ለመውጣት ሲሞክር፣ መልሶ በሌላ ጅምላ ፍረጃ ውስጥ ሲገባ ተስተውሏል። ለምሳሌ፣ ታሪኩን "ግዙፍና ጠንካራ" አድርጎ መሳሉ፣ በጨለማ ክፍል ውስጥ ታጉሮ ካደገበት የሕይወት ታሪክ ጋር ተአማኒነት ያጣል። እንዲሁም፣ ዐይነሥውራን "ልዕለ-ሰሚ" ይሆናሉ የሚለው የተለመደ እሳቤ (Compensation Stereotype)፣ በታሪኩ ላይ መንጸባረቁ፣ የግለወጥነቱን ጥንካሬ አዳክሞታል።

2. በባህሪ ዘላቂነት (Consistency) ዙሪያ የተገኙ ግኝቶች

የባህሪ ዘላቂነት፣ አንድ ገጸባህሪ በታሪኩ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙት ፈተናዎች፣ የመሠረታዊ አቋሙንና ባህሪውን በአመክንዮአዊ መንገድ የሚፈትኑበትና የሚያዳብሩበት መመዘኛ ነው። ከዚህ አንጻር፣ ትንተናው እንደሚያሳየው፣ አምስቱም ገጸባህሪያት እጅግ ጠንካራና አሳማኝ የባህሪ ዘላቂነት አሳይተዋል።

የታሪኩ "ራስን የመቻል" ጽኑ ፍላጎት፣ ቤተሰቡን ጥሎ ከመሰደድ፣ ልመናን ከመጸየፍ፣ ወደ ጉልበት ሥራ (መካኒክነት) እስከ መግባት ድረስ በዘላቂነት ታይቷል። በመጨረሻ በሕክምና መፈወሱም፣ ዐይነሥውርነቱ በተፈጥሮ ሳይሆን በቸልተኝነት የመጣ መሆኑ ስለተገለጸ፣ ፈውሱ ከታሪኩ አመክንዮ ጋር የሚሄድና ዘላቂነቱን ያረጋገጠ ነው።

የሽማግሌው የባህሪ ዘላቂነት፣ በአመክንዮአዊ ለውጥ ላይ የተመሠረተ ነው። የዝምበላቸውን ታሪክ ከመስማቱ በፊት፣ የልጅ ልጁን ጥያቄ ያዘናጋ ነበር። ከሰማ በኋላ ግን፣ ፍርሃቱ ባህሪውን በዘላቂነት ለውጦታል ("ግብራቸውን ለወጡት")፤ ከዚያ ቅጽበት ጀምሮ እያንዳንዱ ድርጊቱ (ገንዘቡን በሙሉ መስጠት)፣ ያንን ፍርሃት ለማስወገድ የሚደረግ ዘላቂ ጥረት ሆኗል።

የአሮጊቷ መሠረታዊ ባህሪ "የእናትነት መስዋዕትነት" ነው። ይህ ባህሪዋ፣ ልጇን ከሞት ለማዳን አገሯን ስትለቅ እንደታየው ሁሉ፣ ልጇን ከ"ኩነኔ" (ከትዳር መፍረስ) ለማዳን ቤቱን ስትለቅ በዘላቂነት ተንጸባርቋል።

የውብቴ ዘላቂነት፣ በእሱ ፍልስፍና ("ከኩሊነት ልመና ይሻላል") እና ከዚሁ ጋር በተያያዙ ድክመቶቹ (ስካር) ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህ ባህሪያቱ፣ ከታሪኩ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሳይለወጡ አብረውት ዘልቀዋል።

የበርጠሎሜዎስ ዘላቂነትም፣ ከፈውሱ ቅጽበት በኋላ በተፈጠረው “ጸጸት“ ላይ የተመሠረተ ነው። “ደግሜ መታወር እፈልጋለሁ“ የሚለው አዲሱ አቋሙ፣ ቀሪ ሕይወቱን በሙሉ ኢየሱስን ፍለጋ “እንዲባክን“ ያደረገው ዘላቂ ግቡ ሆኗል።

3. በኢ-ፍጹምነት (Imperfection) ዙሪያ የተገኙ ግኝቶች

ኢ-ፍጹምነት፣ ገጸባህሪያት እውነተኛ ሰው እንዲመስሉ የሚያደርጓቸው ድክመቶች፣ ስህተቶችና የባህሪ ግድፈቶች ናቸው። ትንተናው፣ ከዚህ መመዘኛ አንጻር፣ እጅግ ትልቅ የአሳሳል ስኬትና፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ እጅግ ትልቅ የአሳሳል ድክመት አግኝቷል።

የአሳሳል ድክመት (ፍጹምነት/Idealization)፦

ትንተናው፣ በሁለት ገጸባህሪያት ላይ፣ ተአማኒነትን የሚጎዳ “ፍጹም ሰናይነት“ (Perfection) አግኝቷል።

ታሪኩ፣ ምንም ዓይነት የባህሪ ግድፈት የሌለው ሆኖ ተስሏል። እሱ “ፍጹም ቅን“፣ ለጓደኛው መስዋዕት ሊሆን የሚፈልግ፣ እና በመጨረሻም፣ ለገፋው ማኅበረሰብ የህክምና ተቋምና ትምህርት ቤት የሚሠራ “መልአክ“ ሆኖ ቀርቧል። ይህ፣ ከገሃዱ ዓለም እውነታ የራቀ አሳሳል ነው።

አሮጊቷም በተመሳሳይ፣ “ፍጹም እናት“ ሆነው ተስለዋል። በልጃቸው ሚስት ምክንያት ከቤት ቢወጡም፣ በልጃቸው ላይም ሆነ በምራታቸው ላይ ምንም ዓይነት ምሬት ወይም ቂም አያሳዩም። ይልቁንስ፣ ለልጃቸው ድርጊት መከላከያ ያቀርባሉ (“እሱንም የልጅ ፍቅር...“)። ይህ ፍጹም ይቅር ባይነት፣ ገጸባህሪዋን ከሰውነት ይልቅ ወደ “ቅድስት“ ደረጃ ያቀርባታል። ትንተናው፣ ይህ ምናልባት ታሪኩ በአንደኛ መደብ (በራሷ በአሮጊቷ) በመተረኩ የመጣ የአተራረክ ክፍተት ሊሆን እንደሚችል ጠቁሟል።

የአሳሳል ጠንካራ ጎን (እውነተኛ ኢ-ፍጹምነት)፦

በተቃራኒው፣ ትንተናው፣ በሦስቱ ገጸባህሪያት (ሽማግሌው፣ ውብቱ፣ በርጠሎሜዎስ) ላይ፣ እጅግ ተአማኒነት ያለው፣ ሰብዓዊ ኢ-ፍጹምነት አግኝቷል።

ሽማግሌው ኢ-ፍጹም ናቸው፣ ምክንያቱም ድርጊታቸው (ለልጁ ገንዘብ መስጠት)፣ ከንጹሕ ልግስና ሳይሆን፣ ከራስ ወዳድ የህልውና ፍርሃት እና ከተንኮል (ልጁን በሲያል ማስፈራራት) የመነጨ ነው። ይህ ስብጥር ተነሳሽነት (Mixed Motive)፣ እሳቸውን እጅግ እውነተኛ ሰው ያደርጋቸዋል።

ውብቱ፣ በግልጽ፣ "ኢ-ፍጹም" ነው። እሱ፣ ምስኪን ተረጂ ብቻ ሳይሆን፣ የአልኮል ሱሰኛ፣ "ርጉም ሰው"፣ አልፎ ተርፎም የቀድሞ መሪውን እንደሚመሰክረው "ገንዘቡን ነጥቆ የሚገርፍ"፣ ማለትም "በዳይ" (Abusive) ነው። ደራሲው፣ ዐይነሥውርን እንደ በዳይ አድርጎ መሳሉ፣ ከ"ምስኪን" ጅምላ ፍረጃ ያወጣዋል። ከዚህም በላይ፣ "ብልህ" ሆኖ ሳለ፣ "ሴቶችና ወንዶች በምን ይለያያሉ?" ብሎ መጠየቁ፣ ዐይነሥውርነቱ የፈጠረበትን እውነተኛ የዕውቀት ክፍተት በማሳየት፣ ገጸባህሪውን እጅግ ሰብዓዊ ያደርገዋል።

የበርጠሎሜዎስ ኢ-ፍጹምነት፣ ከሁሉም የላቀና ፍልስፍናዊ ነው። የእሱ ትልቁ ድክመት፣ ለፈውስ ያነሳሳው እምነት ሳይሆን "ማቀባጠር" እና "ሰውን መከተል" ("ሲያቀብጠኝ ነው የጮኽኩት፤ ሰው ሲያደርግ ዐይቼ") መሆኑ ነው። ከፈውሱ በኋላም፣ እምነቱ ፍጹም ሳይሆን፣ በጥርጣሬ የተሞላ ("ያን ያክል እምነት አልነበረኝም") መሆኑ፣ ገጸባህሪውን ከ"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጀግና" አውጥቶ፣ ወደ ተጠራጣሪ፣ ተጸጸታችና ኢ-ፍጹም ሰው ይለውጠዋል።

በአጠቃላይ፣ ትንተና እንዳሳየው፣ ደራሲያኑ የዐይነሥውራን ገጸባህሪያትን የባህሪ ዘላቂነት በመገንባት ረገድ በአብዛኛው የተሳካላቸው ሲሆን፣ በግለወጥነትና በኢ-ፍጹምነት ረገድ ግን ተሳክቶላቸዋል።

አንዳንዶቹ (ተፈራ ይኄይስ እና ስብሐት ገ/እግዚአብሔር)፣ ገጸባህሪያቸውን (ታሪኩንና አሮጊቷን) ከ"ምስኪን" ጅምላ ፍረጃ ለማውጣት ሲሞክሩ፣ ወደ ተቃራኒው ጫፍ በመሄድ "ፍጹም ሰናይ" (Idealized) አድርገዋቸዋል፤ ይህም ተአማኒነታቸውን ጎድቷል።

ሌሎቹ (በዕውቀቱ ሥዩም፣ አውግቼው ተረፈ፣ እና ዳንኤል ታዬ)፣ በገጸባህሪያቸው (በሽማግሌው፣ በውብቱ፣ እና በበርጠሎሜዎስ) ላይ፣ ጥልቅ የሆኑ ሰብዓዊ ድክመቶችን (ፍርሃትን፣ ተንኮልን፣ ሱስን፣ ዓመፅን፣ ጥርጣሬንና ጸጸትን) በመጫን፣ ከጅምላ ፍረጃ

የጸዱ፣ ውስብስብ፣ ኢ-ፍጹም፣ እና እጅግ ተአማኒነት ያላቸው ገጸባህሪያትን በመፍጠር ረገድ ተዋጥቶላቸዋል።

## 3.7 የዋና ገጸባህርያት ተመሳስሎ

በዚህ ክፍል በዋናነት የምንመለከተው በ5ቱም አጫጭር ልብወለዶች የሚገኙትን ዋና ዋና ገጸባህርያት ተመሳስሎ ብቻ ነው። ገጸባህርያት የገሃዱ ዓለም ሰዎች ወኪሎች መሆናቸው ግልጽ ነው። ወኪልም በመሆናቸው የገሃዱ ዓለም ሰው በውጫዊም በውስጣዊም ማንነት ከሌላው ጋር ተመሳስሎ እንደሚያሳዩት ሁሉ በልብወለድ ውስጥ የሚገኙ ገጸባህርያትም እርስበርሳቸው ተመሳስሎ ይታይባቸዋል። የገሃዱ ዓለም ሰዎች የጋራ ባህሪያት አላቸው። ከነዚህም ውስጥ የጋራ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ሰብእና፣ ሥራ፣ ወዘተ. ናቸው። የልቦለድ ዓለም ሰዎችም እኒህን ጥቃቅን ነገሮች ይጋራሉ። በዚህ ክፍል በዋናነት የምንመለከተውም ዓይነስውራን ገጸባህርያቱ በጥቅሉ የሚመሳሰሉባቸውን ነጥቦች ነው።

### 3.7.1 የአመለካከት/የአቋም ተመሳስሎ

ከላይ ገጸባህርያት ስንስል መረሳት የሌለባቸው ሦስቱ ቁምነገሮች በሚል ርዕስ ዐይነ ስውራን ገጸባህርያቱ እንዴት እንደተሳሉ በዝርዝር ለማሳየት ሞክሪያለሁ። በትንተናውም ለመረዳት እንደቻልኩት በአሳሳል ረገድ ጠንካራም ደካማም ጎኖች ተስተውለዋል። ለአብነት ያህል በቀዳሚነት የተተነተነውን "ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ" የሚለውን ልብወለድ ብንመለከት በግለወጥነት ረገድ ዋና ገጸባህሪው ታሪኩ ከሌሎች ገጸባህርያት ተለይቶ የሚታወቅበት አካላዊ ቁመና፣ መልክ፣ አመለካከት ያለው ሲሆን፣ ከዚህ የገጸባህርያት አሳሳል መመዘኛ መስፈርት አንጻር ስናየው በአግባቡ ተስሏል ማለት እንችላለን። ይህ ማለት ግን ታሪኩ በሁሉም የገጸባህርያት አሳሳል መመዘኛ መስፈርቶች በአግባቡ ተስሏል ማለት አይደለም። ለምሳሌ ኢ-ፍጹምነት ከሚባለው የገጸባህርያት አሳሳል መመዘኛ መስፈርት አንጻር ስንመለከተው በገሀዱ ዓለም ከምናውቀውና ከምንመለከተው የዐይነ ስውራን አመለካከትና አቋም ወጣ ያለ፣ እንዲሁም በስነ ልቦና ረገድ ከዐይነ ስውራን ገጸባህሪ ይልቅ የዓይናማ ስነ ልቦናዊ ጥንካሬ ሲያሳይ እንመለከታለን። ምን ማለቴ ነው? ላብራራው።

ታሪኩ ዓይነ ስውር ነው። የታሪኩ ጓደኛ ምንተስኖት ደግሞ አካል ጉዳተኛ ነው። እግረ ሰላላ ነው። ሁለቱ ባልንጀራማቾች ቀያቸውን ጥለው ከሄዱ በኋላ የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት በልመና ተግባር ላይ ለመሰማራት ተገደዋል። ይሄ የሁለቱ ጓደኛማቾች ድርጊት ታድያ እምብዛም ላያስደንቀን ይችላል። ቤተሰብ የሌለው፣ አጋዥ የሌለው፣ ተሰጥዖ የሌለው፣ ትምህርት የሌለው፣ ገንዘብ የሌለው አካል ጉዳተኛ ከልመና ውጭ በምን ተግባር ላይ ሊሰማራ ይችላል?

ጉዳዩን ከተጨባጩ ነባራዊ ሀቅ አንጻር ስንመለከተው የተረት ዝንባሌ ስላለበት የአመክንዮአዊነት ችግር ይታይበታል። ልብወለዱን የተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ግን ይሄ አይደለም። ልብወለዱን ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ቀጥሎ የሚያመነጩት ሀሳብ ነው። ለተወሰነ ጊዜ በልመና ሲተዳደሩ ከቆዩ በኋላ ልመና በጣም አጸያፊ ተግባር እንደሆነና በላባቸው መተዳደር እንዳለባቸው ይወስናሉ። ገጸባህርያቱም አንድ ጊዜ በአትክልተኝነት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመካኒክነትና በቀለም ቀቢነትና በመሳሰሉት ጉልበት በሚጠይቁ ሥራቸው ተሰማርተው ሲሰሩ እንመለከታቸዋለን። ጉዳዩ ማንኛውም አካል ጉዳተኛ ሊያደርገው የሚችለው ዓይነት ቢመስልም ልብ ብለን ካጤኔነው ግን የሀሳቡ ጥንስስ በራሱ የዓይናማ እንጂ የአካል ጉዳተኛ አይመስልም።

ልብወለዱ ከኢ-ፍጹምነት አንጻር በርካታ ደካማ ጎኖች አሉበት ለማለት ያበቃኝ ይሄ ነውን? ከእነዚህ ምክንያቶች ላይ ብቻ ተነስቶ ልብወለዱን መፈረጅ ተገቢ ነው? አይደለም። ልብወለዱ ውስጥ የጉልበት ሥራ የሚሰሩ፣ ልመናን የሚጸየፉ፣ አካል ጉዳተኞች አሉበት ማለት ልብወለዱ ከኢ-ፍጹምነት አንጻር ደካማ ጎን አለበት ማለት አይደለም። የልብወለዱን አመክንዮአዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው በልብወለዱ ታሪክ መገባደጃ አካባቢ ገፀባህርያቱ ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን ሊያጠፉ በሚሞክሩበት ወቅት ዛፍ ላይ ተሰቅሎ የሚያገኙት ተዝቆ የማያልቅ ገንዘብ ነው። ገጸባህርያቱ ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን ሊያጠፉ ሲሉ ገንዘብ ያገኛሉ። ይሄን ከኢ-ፍጹምነት አንጻር ስንመለከተው ወደ ተረት የሚያደላ ዝንባሌ እንዳለበት እናስተውላለን። ታሪኩ ከገሀዱ ዓለም ነጸብራቅነት ይልቅ የተረት ተረት ለዛ ይስተዋልበታል። ስንቱ ነው ተስፋ ቆርጦ ራሱን ሊያጠፋ ዛፉ ላይ ገመድ ሲያስር ብር የሚያገኝ? ታሪኩስ ምን ያህል እውነተኝነት አለው?

በአምስቱም ሥራዎች ላይ በተደረገው ትንተና በልብወለዶቹ ውስጥ የተስተዋሉ ጠንካራም ደካማም ጎኖች አሉ። በትንተናው ወቅት በዐይነ ስውራን ገጸባህርያት መካከል ያለውን ተመሳስሎ ለመፈተሽ ምንም ዓይነት እድል አልገጠመኝም ነበር። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት በአምስቱም ገጸባህርያት አሳሳል ዙሪያ የታዩ የዓይነ ስውራን ገጸባህርያት ተመሳስሎዎችን በዝርዝር ለመመልከት እሞክራለሁ። ይሄም በአሳሳል ወቅት የተስተዋሉ ክፍተቶችና ጠንካራ ጎኖችን ለመለየት ይረዳኛል።

በዚህም ክፍል በዋናነት የምንመለከተው በዐይነ ስውራን ገጸባህርያቱ መካከል ያለውን የአመለካከት ወይም የአቋም ተመሳስሎ ነው። አመለካከት ወይም አቋም ስል ምን ማለቴ ነው?

የገጸባህርያት አመለካከት ወይም አቋም ስንል ገጸባህርያቱ በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን አስተሳሰብ ማለታችን ነው። ገጸባህርያቱ የሚያስቡት እንዴት ነው? የሚያፈልቋቸው ሀሳቦችስ አመክንዮአዊነት አላቸው ወይ? ከአንድ ዓይነ ስውር ሊፈልቁ የሚችሉ ናቸውን? … የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል።

በቀዳሚነት የምንመለከተው "ማሙዬ ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ" የተሰኘው ልብወለድ ውስጥ በዐይነ ስውርነት የተሳለውን ታሪኩ የተሰኘውን ገጸባህሪ ነው።

ታሪኩና ጓደኛው ምንተስኖት ጥገኝነትንና ሸክም መሆንን አብዝተው የሚጸየፉ ገጸባህርያት ሲሆኑ ለቤተሰቦቻቸው ሸክምና ተጨማሪ ጣጣ ላለመሆን ሲሉ አገር ለቀዋል። ሸክም መሆንን ይጸየፋሉ። ራሳቸውን ችለው ለምነውም ሆነ ሰርተው መብላትን ይመርጣሉ። ይሄ ዓይነቱ ስነልቦናዊ ብርታት በሌሎች ገጸባህርያት ላይ ይንጸባረቃልን? በሚገባ።

"ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ" የተሰኘው የስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ልብወለድ ውስጥ ስሟ በግልጽ ያልተጠቀሰው አሮጊቷ ዓይነ ስውር ገጸባህሪ ከልጇ ቤት የኮበለለችው ለልጇና ለምራቷ ሸክም ላለመሆን እንደሆነ ልብ ይሏል። በታሪኩና በአሮጊቷ መካከል ይህንን የመሰለውን የመንፈስ ጥንካሬ እንመለከታለን። ይሄም የጋርዮሽ ጠባይ አንዳንድ ሰዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ የልባቸውን በልባቸው አድርገው፣ ረሀብና መከራን ተቋቁመው፣ ሀሩሩንና ቁሩን ችለው … ከጥገኝነት መላቀቅን እንደሚመርጡ ያስረዳናል። ይሄም ዓይነ ስውራን ገጸባህርያት እንደማንኛውም ሰው አንዱ እምነቱን በሌሎች ላይ

ሌላኛው ደግሞ እምነቱን በራሱ ላይ መጣልን እንደሚመርጥ ያሳየናል። ለአብነት ያህል የአውግቼው ተረፈ "ወይ አዲስ አበባ..." ውስጥ የቀረበውን ውበቴ ስንመለከት ከመስራት ይልቅ መለመንን ይመርጣል። አንዳንዴም "እንደ ኩሊ ከመሸከም መለመን አይሻልም?" እያለ ዓይናማ ወዳጆቹን ሲተች እንመለከታለን። ይህንን ስንል ገጸባህሪው ከስራ ይልቅ ልመናን መምረጡን በመጥቀስ የሰው ልጅን ልዩ ልዩ ጠባይ ብቻ ለማሳየት ነው።

## 3.7.2 የትምህርት ታሪክና የሥራ መስክ ተመሳስሎ

አምስቱም ገጸባህርያት የሥራ መስክ ተመሳስሎ ይታይባቸዋል። አምስቱም ገጸባህርያት የረባ የዘመናዊ ትምህርት አልቀሰሙም። የተለየ ተሰጥዖም የላቸውም። ገጸባህርያቱ እንደማንኛውም ሰው ከአንድ ደሀና መካከለኛ ቤተሰብ የመጡ ናቸው። በቀዳሚነት የበዕውቀቱ ሥዩም "እራትና መብራት" የተሰኘው ልብወለድ ውስጥ አይነ ስውሩን አዛውንት ማንሳት እንችላለን። አዛውንቱ በልመና ሥራ የሚተዳደሩ እድሜ ጫናና የብርሃን እጦት የሚያንገላታቸው ሰው ናቸው። ልጆቻቸውም ሆነ ቤተ ዘመዶቻቸው መጦር ስላልሆነላቸው በልጅ ልጃቸው መሪነት መንደር ለመንደር እየተንከራተቱ ሲለምኑ ይውላሉ። ታድያ ልጃቸው የልጅ ልጃቸውን በመሪነት በመስጠቷ/ቱ በተዘዋዋሪ እየጦራቸው/ቻቸው ነውን? አይመስለኝም። አዛውንቱ ለልጅ ልጃቸው የትምህርት ቤት የጽህፈት መሣሪያዎችን ብሎም አንዳንድ ተጨማሪ ቁሶችን በማሟላት ረገድ ያግዙታል። በተዘዋዋሪ አዛውንቱ ጧሪም ተጧሪም ናቸው። ይሄም የኑሮ ጫና አዛውንቱን ልመናን ሙጥኝ እንዲሉ አስገድዷቸዋል። ምን ምርጫ አላቸው?

ቀጥሎ የምንመለከተው የአውግቼው ተረፈን "ወይ አዲስ አበባ..." ዓይነ ስውር ገጸባህሪ ውበቴ ነው። ውበቴ ከአንድም ሁለቴ ከመሸከም ወይም ከጉልበት ሥራ ለምኖ መኖር በስንት ጣሙ!" ሲል ብናደምጠውም ተገዶ እንጂ ወዶ አይመስለንም። ውበቴ ባለ ትዳር ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ጠንካራ የአልኮል ሱስ አለበት። ውበቴ ምንም ዓይነት የቀለምም ሆነ የመንፈሳዊ እውቀት ወይም ሰዎችን የሚያዝናናበት ሆነ የሚያስደስትበት ተሰጥዖ የለውም። ስለዚህ በልመና ላይ ተሰማርቶ ሕይወቱን ለመምራት ተገዷል። ምን ምርጫ አለው?

ቀጥሎ የምንመለከተው የስብሀት ገብረ እግዚአብሔር "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ" የተሰኘው ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸውን ስማቸው በግልጽ ያልተጠቀሰውን አሮጊት ነው። ገጸባህሪዋ

በእድሜ የገፉ እንዲሁም በእርጅና ሰበብ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ በልጇ ቤት ሲጦሩ ኖረዋል። ጤናማ ህይወትም ነበራቸው። ይሁን እንጂ ከምራቷ ጋር ጥሩ ግንኙነት አልነበራቸውም። ምራቷ አትወዳቸውም። ይህቺ አዛውንት ታድያ በነጋ በጠባ ቁጥር ከምራቷ ጋር እየተጨቃጨቁ ልጃቸውን ሊያስከፉት አልወደዱም። በዚህም የተነሳ ቤቱን ጥለው ይጠፋሉ። አሮጊቷ የታወሩት በቅርቡ ስለሆነ ሁሉ ነገር ያልለመዱት ነው። ስለዚህም እንደድሮው ተሯሩጠው መስራት አይችሉም። ስለዚህም ቤተክርስቲያን አካባቢ በመጠጋት በልመና ሕይወት ለመተዳደር ይወስናሉ።

ቀጥሎ የምንመለከተው ደግሞ የተፈራ ይኸይስን “ማሙዬ ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ” የተሰኘው ልብወለድ ውስጥ በዋና ገጸባህሪነት የተሳለውን ታሪኩ የተሰኘውን ገጸባህሪ ነው። ታሪኩ ከላይ ከተጠቀሱት ገጸባህርያት በመጠኑም ቢሆን ለየት ይላል። ታሪኩ በበቂ ህክምና እጦት ምክንያት በለጋ እድሜ ለመታወር የበቃ ገጸባህሪ ነው። ታሪኩ ለቤተሰቦቹ የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን ከሱ በኋላ የተወለዱ ታናናሽ ወንድሞችና እህቶች አሉት። ይሁንና ታሪኩ እድሜው እየገፋ በመጣ ቁጥር ለቤተሰቦቹ ተጨማሪ ሸክም የሆነ እየመሰለው ነፍሱ ትጨነቃለች። ይህ ዓይነቱ ሀሳብ ጭንቅላቱ ውስጥ ከገባ በኋላ እንደወትሮው ለማሰብ አላስችል ይለዋል። በወጣትነቱ እየተጦረ ለመኖርም እምቢ ይላል። ከአንድ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ከሚሰቃይ ባልንጀራው ጋር በመሆን ያደገበትን ቀዬ ጥሎ ይጠፋል። ለተወሰነ ጊዜም በልመና ሲተዳደር ከቆየ በኋላ ቤተሰቦቹ ላይ የተሰማው ዓይነት የጥገኝነት ስሜት ይሰማው ይጀምራል። በመጨረሻም ከልመና ይልቅ ሰርቶ መብላትን ይመርጣል። ቀስ በቀስም ከአትክልተኝነት እስከ መኪና መካኒክነት ብሎም ቀለም ቀቢነት የመሳሰሉ ሥራዎችን በመስራት ሀብትና ወዳጅ በማፍራት የራሳቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን ብሎም የአካባቢያቸውን ገጽታ ለመቀየር ይበቃሉ። ገጸባህሪውን ከሌሎች ገጸባህርያት ለየት ያለና እንደ አርአያ ሊጠቀስ የሚችል ልዩ ገጸባህሪ ያደርገዋል።

በመጨረሻም የምናነሳው በሀዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሷቸዋል ተብለው ከሚታመኑ ዐይነ ስውራን መካከል አንዱ የሆነው በርጠሎሜዎስን ነው። በርጠሎሜዎስ ሲወለድ ጀምሮ ዐይነ ስውር ስለነበረ ከልመና ውጭ የሚያውቀው ሌላ ዓለም አልነበረም። ሀዲስ ኪዳን እውነተኛ የታሪክ መዝገብ ነው ወይስ የአስተምህሮ ድርሳን የሚለውን ሙግት ለጊዜው እናቆየውና የበርጠሎሜዎስን ህይወት ለአፍታ እንቃኘው። በርጠሎሜዎስ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የኖረ ሰው ነው። የጥንቱ ዓለም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አልነበረም።

ስለዚህም በርጠሎሜዎስ እንደማንኛውም በዘመኑ እንደኖረ አካል ጉዳተኛ በልመና ህይወት ለመተዳደር ተገዷል።

ከላይ ከቀረበው ትንተና ለመረዳት እንደምንችለው አምስቱም ገጸባህርያት በልመና የሚተዳደሩ እንደሆኑ መገንዘብ ችለናል። ይሄም በገጸባህርያቱ ላይ ከታዩ ምስስሎሾች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ነው። አምስቱም ገጸባህርያት ታድያ በልመና ተግባር ላይ መሰማራታቸው ምን ይነግረናል? የዓይነ ስውርነት ህይወት በእጅጉ ፈተና ይበዛበታል። ፈተናውን ተቋቁሞ በህይወት ለመቆየት (survive) ታድያ የሆነ ብልሃት መፈለግ ግድ ይላል። ከአምስቱ ዓይነ ስውራን ገጸባህርያት ውስጥ ከልመና ህይወት መውጣት የቻለው ታሪኩ ብቻ ነው። ታሪኩ እንዴት ተሳካለት? ሰርቶ ነው ወይስ አንዳች ተሰጥዖ ስላለው? ሁለቱም አይደለም። ታሪኩ ሰርቶም ሆነ ድብቅ ተሰጥዖውን ተጠቅሞ ያካበተው ሀብት የለም። ሀብቱን ያገኙት በአጋጣሚ እንጂ በላባቸው አይደለም። አለዚያ ግን ከችግሩ መውጣት አይችልም ነበር። ይሄ ዓይነቱ ሁነት ደግሞ በማስረጃ ሊደገፍ ስለማይችል እንደ ስኬት ሊቆጠር አይችልም። በሌላ አማርኛ ታሪኩ ከችግሩ አልወጣም። ታሪኩ አሁንም በልመና ውስጥ የሚንገላታ ገጸባህሪ ነው። በሌላ ጎኑ ስንመለከተው ደግሞ የታሪኩ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ማግኘት ራስን ለመቻል ካለው ጽኑ ፍላጎት የመነጨ ይሆንን? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል። ፍላጎትና ቁርጠኝነቱ ካለ ማንኛውም ሰው ሀብት ማካበት ይችላል የሚል አንድምታ ለማንጸባረቅ ተፈልጎ ይሆንን?

## 3.7.3 ጽናት፤ ችግር የወለደው ጽናት ተመሳስሎ

አምስቱም ገጸባህርያት ህይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ መሰዋዕትነት በመክፈል በኩል ተመሳስሎ ይታይባቸዋል። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አምስቱም ገጸባህርያት የሚተዳደሩት በልመና ነው። ልመና ደግሞ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ጫና አለው። ከዚህ በተጨማሪ የሰዉን ፊት፣ ጸሀዩን፣ ወከባውን፣… መቋቋም ያስፈልጋል። ልመና እጅግ ፈታኙ ስራ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህን ስንል ግን ለሁሉም ሰው አንድ ነው ማለት አይደለም። ለአብነት ያህል "የወይ አዲስ አበባው..." ውብቱ ልመና ቀለል ብሎት የሚሰራው ስራ ነው። ለ"ማሙዬ ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ"ው ታሪኩ ደግሞ ልመና ከውርደቶች ሁሉ የላቀው ውርደት ነው። ከሚለምን ራሱን ቢያጠፋ ይመርጣል (ከአንዴ ሁለቴም ሀሳቡ መጥቶለት ነበር።) ለ"ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ" አሮጊት እና ለ"እራትና

መብራት" አዛውንት ደግሞ ልመና ህይወታቸውን የሚያቆዩበት ብቸኛ አማራጫቸው ነው። በዚህ እድሜያቸው ከልመና ውጭ ምን የተሻለ እጣ ፋንታ አላቸው? ለሀዲስ ኪዳኑ በርጠሎሜዎስም ልመና አካል ጉዳተኝነቱ ያወረሰው እጣ ፋንታው ነው። በዚያ ዘመን የኖረ ዓይነ ስውር ከመለመን ውጭ ምን ምን አማራጭ አለው? ዛሬ ዘመኑ ተቀይሯል። ዓይነ ስውራን እንደማንኛውም ሰው ተምረው በተማሩበት የትምህርት መስክ ላይ ተሰማርተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የማስተዳደር እድሉ አላቸው። በርጠሎሜዎስ ለዚህ ዓይነቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የስልጣኔ ጸጋ አልታደለም። ሌሎች ገጸባህርያትም ቢሆኑ የበቀሉበት ዘመን ልክ ቢሆንም የበቀሉበት አካባቢ አካል ጉዳተኞችን በልዩ ክብካቤ የሚይዝ ባለመሆኑ እድሜ ልካቸውን የሰው እጅ እያዩ እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል።

ይህ ሁሉ በእንዲህ እንዳለ ታድያ የገጸባህርያቱን ጽናትና ቁርጠኝነት አለማድነቅ አይቻልም። ምንም ቢሆን በልመና ራስን ማስተዳደር ብሎም ለቤተሰብ መትረፍ መቻል ትልቅ ጽናት ይጠይቃል። አምስቱም ገጸባህርያት ላይ ይሄ ዓይነቱ የመንፈስ ጥንካሬ ይታያል። ውበቴ ከተማ ለከተማ ሲንከራተት ውሎ ቤቱን ያስተዳድራል። አዛውንቱ ደግሞ መንደር ለመንደር ሲንከራተቱ ውለው በሚያገኟት ገንዘብ ለትንሹ የልጅ ልጃቸው ደብተርና ተጨማሪ የትምህርት መሣሪያዎችን ያሟላሉ። ታሪኩና ምንተስኖትም (ምንም እንኳ ሀብቱን ያገኙበት መንገድ አጠያያቂ ቢሆን) ባገኙት ሀብት ራሳቸውን በህክምና ከአካል ጉዳተኝነታቸው በመፈወስ ለመኖሪያ አካባቢያቸው ብሎም ተወልደው ላደጉበት ስፍራ የትምህርት፣ የጤናና የአምልኮ መሠረተ ልማቶችን ማሳነጽ ችለዋል። ይሄ ደግሞ በሁሉም ገጸባህርያት የሚታይ አንድ የጋርዮሽ ጠባይ እንዳለ ያስረዳናል። እኒህም የጋርዮሽ ጸባይ ጽናት፣ ብርታትና ቁርጠኝነት ናቸው። ይሄ ጽናት፣ ብርታትና ቁርጠኝነት ታድያ ዝም ብሎ በአንድ አዳር የመጣ አይደለም። ረዳት አልባነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ የሰው እጅ እያዩ የመኖር ሰቀቀን፣ የህክምና እጦት፣… የወለደው ነው። የታሪኩ እና ምንተስኖት አካል ጉዳተኝነት በቤተሰቦቻቸው የግንዛቤ እጥረት የመጣ ነው። በወቅቱ የህክምና እርዳታ ማግኘት ቢችሉ ኖሮ ለዚህ አይነቱ ሁኔታ አይጋለጡም ነበር። ከሚኖሩበት ከተማ ወደ ዋና ከተማዋ እንዲመጡ የገፋፋቸው ምናልባትም ሰርተን ከምናገኘው የተወሰነ ቆጥበን የሕክምና እርዳታ እናገኛለን ብለው በማሰብ ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነውም በመጨረሻ ያሰቡትን ሁሉ ያሳካሉ። እንዲሁም ተወልደው ላደጉበት አካባቢ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ይገነባሉ። እነሱ እድሉን ባያገኙም ለታናናሾችን ይሆናል በማለት የህክምና ተቋማቱን መርቀው

ሲከፍቱ እናያለን፡፡  ይሄ ደግሞ የገጸባህርያቱን የሞራል ልዕልና ያሳያል፡፡ ታድያ የገጸባህርያቱ ስኬት እንዲሁ ተወልደው ያደጉበትን ከተማ ጥለው ስለተሰደዱ ብቻ የመጣ አይደለም፡፡ የበርካታ አመታት ጥረትና ላብ ውጤት ነው፡፡ በተመሳሳይ ውበቴን ብንወስድ የገጸባህሪውን የመንፈስ ብርታትና ጥንካሬ እንመለከታለን፡፡ ውበቴ ኩሩና አስተዋይ ነው፡፡ ይሄ የገጸባህሪው ብልህነት ታድያ እንዲሁም የተገኘ ሳይሆን ከዓመታት ፈተናና የሕይወት ልምድ የመጣ ነው፡፡ አሮጊቷም ልጇ እንዳይከፋው ቤታቸውን ጥለው ሲጠፉ ብዙ መከራ እንደሚገጥማቸው ሳያውቁ ቀርተው አይደለም፤ ገጥሟቸዋልም፡፡ ይሁንና አሁን የሚገጥማቸው መከራ አንድያ ልጃቸውን ለማሳደግና ለቁምነገር ለማብቃት ከዋሉት መሰዋዕትነት እንደማይበልጥ ያውቃሉ፡፡ ልጃቸውን ድጋሚ ላያዩት ተሰደዋል፡፡ ግን ደግሞ ይሄ ስደት ብዙ ነገር አስተምሯቸዋል፡፡ እንዳይርባቸው የሚያበላቸው፣ እንዳያደናቅፋቸው የሚመራቸው፣ ዝምታው እንዳይጫጫናቸው የሚያጫውታቸው ሰው እግዚአብሔር አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይሄ ሁሉ በረከት ታድያ እንዲሁም የመጣ ሳይሆን ደስታና መከራ ሲፈራረቅባቸው በእግዚአብሄር ላይ ያላቸውን እምነት ባለማጓደላቸው ያገኙት ካሳ ነው፡፡ አምስቱም ታሪኮች ከሞላ ጎደል በደስታ የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡ አካል ጉዳተኞቹ በብዙ መከራና ችግር ከተፈተኑ በኋላ ቀድሞ ከነበሩበት በአንጻሩ ሻል ያለ ሁኔታ ይገጥማቸዋል፡፡ እዚህ አንጻራዊ ቦታ ላይ ለመድረስ ታድያ ብዙ ተፈትነዋል፡፡ ይሄ ችግር ደግሞ ገጸባህሪያቱ ጽኑ እንዲሆኑና ችግሮቻቸውን መቋቋም እንዲችሉ አድርጓቸዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የተተነተኑት አምስቱ ዐይነሥውራን ገጸባህሪያት – ታሪኩ (ከ“ማሙዬ ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ“)፣ ሽማግሌው (ከ“ራትና መብራት“)፣ አሮጊቷ (ከ“ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ“)፣ ውበቴ (ከ“ወይ አዲስ አበባ“) እና በርጠሎሜዎስ (ከ“የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ“) – በተለያዩ ደራሲያንና በተለያዩ ዘመናት ቢጻፉም፣ በጥልቅ ሲመረመሩ እጅግ አስገራሚ የሆኑ ተመሳስሎዎችንና በዚያው ልክ ደግሞ ጉልህ ልዩነቶችን ይስተዋልባቸዋል፡፡

በአምስቱም ገጸባህሪያት መካከል የሚታየው ዋነኛ፣ ጉልህ እና ወጥ የሆነ ተመሳስሎ ሁሉም በሕይወታቸው በአንድም ሆነ በሌላ ወቅት በልመና ሥራ ላይ ተሰማርተው መገኘታቸው ነው፡፡ ይህ ነጥብ፣ በራሱ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ዐይነሥውራን ገጸባህሪያት እንዴት በጅምላ እንደሚፈረጁ (Stereotyped) የሚያሳይ ጠንካራ ማስረጃ ሆኖ ይቀርባል፡፡

ሽማግሌው፣ ውበቴ፣ አሮጊቷ እና በርጠሎሜዎስ ዋነኛ መተዳደሪያቸው ልመና ነው። ይህ የኑሮ ዘይቤ እንደ ዕጣ ፈንታ የተጫነባቸው ይመስላል። ሽማግሌው በእድሜና በዐቅም ማነስ፣ አሮጊቷ ከልጃቸው ቤት ከወጡ በኂላ ባጋጠማቸው የእርጅናና የዓይን ማጣት ድርብ ችግር፣ ውበቴ ምንም ዓይነት የሥራ ክህሎት ባለመኖሩና ትዳርን ማስተዳደር ስለነበረበት፣ በርጠሎሜዎስ ደግሞ በኖረበት ጥንታዊ ዘመን ለአንድ ዐይነሥውር ከልመና ውጭ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ በዚህ የሕይወት ጎዳና ላይ ወድቀዋል።

ከዚህ ጅምላ ፍረጃ ለመውጣት የሚሞክረው ብቸኛው ገጸባህሪ ታሪኩ ነው። ታሪኩ ልመናን "የጥገኝነት ስሜት" በማለት አጥብቆ ይጸየፈዋል። ከጓደኛው ምንተስኖት ጋር በመሆንም እንደ አትክልተኝነት፣ መካኒክነትና ቀለም ቀቢነት ያሉ የጉልበት ሥራዎችን በመሥራት ከዚህ ዕጣ ፈንታ ለማምለጥ ይታገላል። ይህ ገጸባህሪ፣ በመጀመሪያ ሲታይ፣ ደራሲው (ተፈራ ይኄይስ) ከጅምላ ፍረጃው ለመውጣት ያደረገውን ሙከራ ያሳያል።

ሆኖም፣ የዚህ ጥናት ትንተና እንደሚያሳየው፣ የታሪኩ ከችግር መውጣት ተአማኒነት (Credibility) የጎደለው ነው። ታሪኩና ጓደኛው ከድህነት የተላቀቁት በሠሩት የጉልበት ሥራ ሳይሆን፣ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሲሉ "በአጋጣሚ" ባገኙት ተዝቆ የማያልቅ የተደበቀ ሀብት ነው። ይህ የሴራ አፈታት (Plot resolution)፣ በተጨባጩ ዓለም ዐይነሥውራን በሥራና በልህቀት ራሳቸውን ሊለውጡ እንደሚችሉ ከማሳየት ይልቅ፣ መፍትሔው በተአምር ወይም በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ዕድል ላይ የተመሠረተ እንዲመስል ያደርገዋል። ይህም፣ በተዘዋዋሪ፣ ደራሲው ራሱ ዐይነሥውር ገጸባህሪው በገሃዱ ዓለም በሚታወቅ የሥራ መስክ ተሰማርቶ እንዲሳካለት ለማድረግ መቸገሩን ያሳያል። በመሆኑም፣ ከአምስቱም ደራሲያን ውስጥ አንዳቸውም ዐይነሥውር ገጸባህሪን ከልመና ውጭ በሆነ ተጨባጭና ተአማኒነት ባለው የሥራ መስክ ላይ አሰማርተው፣ በዚያው እንዲጸናና እንዲሳካ አድርገው ለመሳል አለመቻላቸው፣ በጥናቱ ውስጥ የተገኘ ትልቅ የአሳሳል ድክመትና የጋራ ተመሳስሎ ነው።

የገጸባህሪያቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ (ልመና) ቢመሳሰልም፣ ለዚህ ሁኔታ የሚሰጡት ሥነ ልቦናዊ ምላሽና ያላቸው አመለካከት ግን እጅግ የተለያየ ነው። ይህ ልዩነት፣ ደራሲያኑ "ዐይነሥውርነት"ን እንደ አንድ ወጥ ስብዕና ሳይሆን፣ በግለሰቦች ላይ ሲከሰት የተለያየ ምላሽ እንደሚፈጥር መረዳታቸውን ያሳያል።

ጥገኝነትን በጽኑ መጸየፍ (ታሪኩ እና አሮጊቷ)፦ በዚህ ንጽጽር ውስጥ ጎልቶ የሚወጣው የአመለካከት ልዩነት በታሪኩ እና በአሮጊቷ ላይ የሚታየው ጠንካራ "ሸክም ላለመሆን" የመፈለግ አቋም ነው። ታሪኩ በወጣትነቱ በቤተሰቡ ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖርን በመጸየፍ ይሰደዳል። አሮጊቷም፣ በእርጅና ዘመናቸው፣ በልጃቸው ቤት በምራቷ ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባት ተከትሎ፣ የልጃቸውን ትዳር ከማናጋትና "ሸክም" ከመሆን ይልቅ፣ ስደትንና ብቸኝነትን በጸጋ ተቀብለው ከቤት ይጠፋሉ። ይህ አቋም፣ ሁለቱም ገጸባህሪያት ለራሳቸው ክብር (Dignity) ትልቅ ቦታ እንደሚሰጡና መከራን ተቋቁመው ነጻነታቸውን ለማስከበር እንደሚጥሩ ያሳያል።

ጥገኝነትን እንደ ሥራ መቀበል (ውብቴ)፦ በተቃራኒው ጫፍ ላይ የሚገኘው ውብቴ ነው። ውብቴ ልመናን እንደ ውርደት ሳይሆን፣ እንደ አንድ የሥራ ዘርፍና ከከባድ የጉልበት ሥራ (እንደ ኩሊነት) እንደሚሻል አድርጎ የሚቆጥር ገጸባህሪ ነው። "እንደ አህያ ከመሸከም፣ ለምኖ መብላት አይሻልም?" በማለት ለመሪው የሚሰጠው ምክር፣ ለኑሮ ያለውን ተግባራዊ (Pragmatic) አመለካከት ያሳያል። ውብቴ በልመና አያፍርም፤ ይልቁንም፣ እንዴት አድርጎ ከሰዎች ገንዘብ ማግኘት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። ይህ ባህሪው፣ እውነታውን ከመካድ ይልቅ፣ እውነታው በፈቀደለት ገደብ ውስጥ ሕይወቱን የሚመራ ሰው አድርጎ ይስለዋል።

ጥገኝነትን እንደ ግዴታ መቀበል (ሸማግሌው እና በርጠሎሜዎስ)፦ የሸማግሌው እና የበርጠሎሜዎስ ሁኔታ ከሁለቱም የተለየ ነው። ለእነሱ ልመና የፍልስፍና ምርጫ ጉዳይ ሳይሆን፣ ብቸኛው አማራጭ ነው። በርጠሎሜዎስ በኖረበት ዘመን፣ ሽማግሌው ደግሞ በደረሱበት የእድሜና የጤና ሁኔታ ምክንያት፣ ሌላ ምርጫ ስላልነበራቸው ሕይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ የተቀበሉት ግዴታ ነው።

ምንም እንኳ አምስቱም ገጸባህሪያት በልመና አዘቅት ውስጥ ቢገኙም፣ ሌላው ትልቅ ተመሳስሏቸው የሚያሳዩት አስደናቂ ጽናት (Fortitude) ነው። ይህ ጽናት ዝም ብሎ መከራን መቀበል ሳይሆን፣ በችግር ውስጥ ሆነውም ለሌሎች የመትረፍና ዓላማ ያለው ሕይወት የመምራት ጥረት ነው።

ሽማግሌው፣ ከራሳቸው የዕለት ጉርስ አልፈው፣ ለመሪ የልጅ ልጃቸው የትምህርት መሣሪያዎችን በመግዛት፣ እሱ ከእሳቸው የተሻለ ሕይወት እንዲኖረው መሠረት ይጥላሉ።

ውበቱ፣ በስካርና በሁከት የተሞላ ሕይወት ቢኖረውም፣ በየቀኑ እየተንከራተተ የሚለምነው ቤተሰቡን ለማስተዳደር ነው።

አሮጊቷ፣ ብቸኝነትንና ድህነትን ተቋቁመው፣ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ጋሻ በማድረግ፣ የልጃቸውን ደስታ ከራሳቸው ምቾት አስበልጠው በጽናት ይኖራሉ።

ታሪኩ፣ ምንም እንኳ መነሻው ተአምራዊ ቢሆንም፣ ሀብት ካገኘ በኋላ ራሱን ከመፈወስ አልፎ፣ ተወልዶ ላደገበትና ምንም ነገር ላላደረገለት ማህበረሰብ የህክምና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤትና ቤተክርስቲያን በማሠራት ትልቅ የሞራል ልዕልና ያሳያል።

ይህ ጽናት እንዲሁ የተገኘ ሳይሆን "ችግር የወለደው ጽናት" ነው። የገጸባህሪያቱ ጥንካሬ የመነጨው ከገጠማቸው ረዳት አልባነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ከሕክምና እጦትና ከጥገኝነት ሰቀቀን ነው። ሕይወት በራሱ ያስታጠቃቸው ትልቁ መሣሪያቸው ነው።

ይህ ንጽጽር እንደሚያሳየው፣ አምስቱም ደራሲያን ዐይነሥውራንን ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና አንጻር ሲስሉ፣ በልመና ጅምላ ፍረጃ (Stereotype) ውስጥ ተጠቃለው ይገኛሉ። ይህ የጥናቱ ትልቁ ግኝትና የአሳሳል ድክመት ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ ውጫዊ ተመሳስሎ በስተጀርባ፣ ደራሲያኑ የገጸባህሪያቱን ውስጣዊ ዓለም፣ ሥነ ልቦናዊ ምላሽና አመለካከት በተለያየ መንገድ በመቅረጽ ረገድ ተሳክቶላቸዋል። ጽናትን፣ ኩራትን፣ ተንኮልን፣ ፍርሃትንና እምነትን አጣምረው በመያዝ፣ "ዐይነሥውርነት" አንድ ወጥ ስብዕና እንዳልሆነ፣ ይልቁንም በችግር የተፈተኑ የተለያዩ ሰብዓዊ ማንነቶች ስብስብ መሆኑን አሳይተውናል።

## 3.7.4 ባይተዋርነት

ባይተዋርነት አንድ ግለሰብ ከራሱ፣ ከሌሎች፣ ከማኅበረሰቡ፣ ከሥራው እና በአጠቃላይ ከዓለም ጋር ያለውን የመከፋፈል እና የመራቅ ስሜት ያመለክታል።

ባይተዋርነትን በተመለከተ በርካታ ፈላስፎች እና ማኅበረሰብ ተመራማሪዎች የተለያዩ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

ካርል ማርክስ ባይተዋርነትን በካፒታሊዝም ስርዓት ውስጥ ካለው የሰው ጉልበት ብዝበዛ ጋር ያያይዘዋል። በ"Economic and Philosophic Manuscripts of 1844" ላይ እንዲህ

ይላል፦ "The worker becomes all the poorer the more wealth he produces, the more his production increases in power and size."

ኤሚል ዱርኬም ደግሞ ባይተዋርነትን ከ"አኖሚ" (normlessness) ጋር አያይዞ ያብራራል። ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው ማኅበራዊ ደንቦች ሲፈርሱ ነው። ዱርኬም ማህበራዊ ደንቦች ሲፈርሱ ወይም ግልጽ ሳይሆኑ ሲቀሩ ግለሰቦች ግራ ይጋባሉ፤ የህይወት አቅጣጫቸውን ያጣሉ ይላል። ይህ አኖሚ ወይም ደንብ ማጣት ይባላል። ይህ ሁኔታ ወደ ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥ እና ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ሊያመራ ይችላል። በ"Suicide" መጽሐፋቸው እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ "Anomie is impossible whenever interdependent organs are sufficiently in contact and sufficiently extensive." ይህ ማለት የማኅበረሰቡ ክፍሎች በቂ ግንኙነት ከሌላቸው አኖሚ ሊከሰት ይችላል።

ማክስ ዌበር ባይተዋርነትን በዘመናዊው ዓለም ካለው ከፍተኛ ምክንያታዊነት (rationalization) እና ቢሮክራሲ ጋር አያይዞ ያብራራል። ይህ ስርዓት ግለሰቡን በጥብቅ ደንቦች እና መመሪያዎች ውስጥ ያጠምደዋል፣ ይህም ደግሞ ከራሱ ፈጠራ እና ነፃነት እንዲርቅ ያደርገዋል።

ሌላኛው የባይተዋርነት መገለጫ መገለል (Isolation/Social Isolation) ነው። ዱርኬም አርስቶትልን ጠቅሶ "Man is a social animal; whoever is unsocial naturally and not accidentally is either beneath our notice or more than human. Society is something that precedes the individual." ማህበረሰባዊ ግንኙነት ለሰው ልጅ ደህንነት ወሳኝ ነው። ከሌሎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት ማጣት የመገለል እና የብቸኝነት ስሜት ይፈጥራል። ይህም ወደ ባይተዋርነት ሊያመራ ይችላል።

ትርጉም ማጣት (Meaninglessness) ሌላኛው የባይተዋርነት መገለጫ ነው። "The absurd is born of this confrontation between the human need and the unreasonable silence of the world." - Albert Camus, The Myth of Sisyphus ካሙስ ህይወት በተፈጥሮዋ ትርጉም የለሽ እንደሆነች ይከራከራል። የሰው ልጅ ትርጉም እና ዓላማ ለማግኘት ይፈልጋል፣ ነገር ግን አለም ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ አትሰጥም። ይህ ግጭት የከንቱነት ስሜት ወይም የትርጉም ማጣት ስሜት ይፈጥራል።

ሌላኛው የባይተዋርነት መገለጫ ከራስ መራቅ (Self-Estrangement) ነው። "Modern man lives under the illusion that he knows what he wants, while he actually wants what he is supposed to want." - Erich Fromm, Escape from Freedom ፍሮም የዘመናዊው ሰው ከእውነተኛ ፍላጎቱ እና ምኞቱ እንደሚርቅ ያብራራል። ይልቁንም በማህበረሰቡ፣ በሚዲያ እና በሌሎች ውጫዊ ኃይሎች የተጫኑትን ፍላጎቶች እንደራሱ አድርጎ ይቀበላል። ይህ ከራስ መራቅ ወደ እርካታ ማጣት እና ወደ ባዶነት ስሜት ያመራል። በጥቅሉ ባይተዋርነት ሰፋ ያለ ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን የባህል መበታተንን፣ ማኅበራዊ መገለልን እና ፍልስፍናዊ ጭንቀትን ያካትታል። እነዚህ የባይተዋርነት መገለጫዎች እርስ በርስ የተያያዙ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው።

## 3.7.4.1 ባይተዋርነት በ"ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ"

የተፈራ ይኼይስ "ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ" ከመጠን ያለፈ የወላጅ እንክብካቤና ከውጭው ዓለም መገለል በልጆች ላይ የሚያስከትለውን አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ያሳያል። ልቦለዱ ይህንን በማድረግ በተዘዋዋሪ የሰው ልጅ ህልውና አንዱ ገጽታ የሆነውን ባይተዋርነትን ወይም ከራስ፣ ከሌሎች፣ ከማህበረሰቡና ከአለም ጋር ያለውን ግንኙነት መዛባትና መጥፋት ያሳያል። ይህ ባይተዋርነት ወደ ትርጉም ማጣት (meaninglessness)፣ ወደ አቅም ማነስ (powerlessness)፣ ወደ ማህበራዊ መገለል (isolation) እና ወደ ራስን ከሌላው አለም ማግለል (self-estrangement) ይመራል። ታሪኩና ምንተስኖት (ሁለቱ ዋና ገፀ-ባህሪያት) የዚህን ባይተዋርነት አስከፊ ገጽታዎች ያሳያሉ።

ልቦለዱ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የሚያሳድሩት ከልክ ያለፈ እንክብካቤና ጥበቃ እንዴት ወደ ባይተዋርነት እንደሚያመራ ይተርካል። ወላጆች ልጆቻቸውን ከአለም ክፋትና ጉዳት ለመጠበቅ ባላቸው ፍላጎት ሳያውቁት ልጆቻቸውን ከአለም፣ ከሌሎችና ከራሳቸው እንዲለዩ ያደርጋሉ። ይህም በልጆቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ የባይተዋርነት ስሜትን ይፈጥራል። ይህ ሁኔታ በግልጽ የሚታየው በታሪኩና በምንተስኖት ህይወት ውስጥ ነው።

ታሪኩ በወላጆቹ ከመጠን ያለፈ ጥበቃ ምክንያት ከውጭው ዓለም ተነጥሎ ይኖራል። ወላጆቹ ማንም ሰው እንዳያየው ብለው ጨለማ ቤት ውስጥ ያሳድጉታል። ልቦለዱ ይህንን ሁኔታ ሲገልጽ፡-

> የታሪኩ ወላጆች ከመሳሳታቸው የተነሳ ከመጋረጃ ውስጥ ሳያወጡ ብርሃን ነስተው ጠቃሚ የመሰላቸውን ምግብና መጠጥ በገፍ ያቀርቡለት ስለነበር እያደገ በሄደ ቁጥር ከዚያ ከጨለማ ቦታ የተሻለ ኑሮ ያለ አይመስለውም ነበር። እንኳን ከውጭ የመጣ እንግዳና አባትና እናቱም ቢሆኑ ልጃቸውን ማጫወት ሲፈልጉ እዚያው ብርሃን ካጣው ክፍል ውስጥ ገብተው የዳበሳ ያህል በሚቆጠረው ውስጥ ነበር። ተፈራ (1960፣ 11)

ይህ ጥቅስ የሚያሳየው ታሪኩ ስለ ውጪው ዓለም ምንም ዓይነት እውቀት እንደሌለውና በወላጆቹ የተገነባውን የተዛባ እውነታ እንደሚቀበል ነው። ይህ እውነታ ከዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት አበላሽቶ ለከፋ ባይተዋርነት ዳርጎታል።

ታሪኩ ለፀሐይ ብርሃን ባለመጋለጡ ምክንያት ዓይኑን ማጣቱ ደግሞ ባይተዋርነቱን ያባብሰዋል። ልቦለዱ እንዲህ ይላል፦

ታሪኩ …ሙሉ ሙቀት ያላት ፀሐይ በወጣችበት ጊዜና በደመናውም ሰዓት ቢሆን ዓይኑ ተገልጾ ፊት ለፊት ለማየት ይሳነው ጀመር። ስለዚህ ዐይኑን ጨፍኖ ሲዳክርና የልጆች ድምፅ እየሰማ ሲከተል ያረፍድ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀንም በዕድሜ ጓደኞቿ ከሆኑት ጋር ባንድ ኩሬ አጠገብ ዐይኑን ጨፍኖ ሲጫወት ከቆየ በኋላ ገለጥ ቢያደርገው ከውሃው ላይ የተወረወረ ጨረር (የፀሐይ ብርሃን) ዓይኑ ላይ ቢያንጸባርቅ ጨርሶ ለመጥፋት በቃ። ተፈራ (1960፣ 12)።

ይህ ዓይነ ስውርነት ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት የበለጠ ያበላሸና ለከፋ ባይተዋርነት ያጋልጠዋል። ዓይነ ስውር በመሆኑ ምክንያት ብዙ ነገሮችን ማድረግ አለመቻሉ ደግሞ የአቅም አልባነት ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል።

በነገረ ህልውና ፍልስፍና መሰረት፣ ሰዎች ቀድሞ ያልተጻፈ ህይወት ወይም ዓላማ ወደ አለም ይመጣሉ። ይህ ወደ አለም መወርወር የመገለልና የትርጉም ማጣት ስሜትን ይፈጥርባቸዋል። በ"ምራኝና እንሂድ" ውስጥ ታሪኩና ምንተስኖት ይህንኑ የመወርወርና

ባይተዋርነት ያሳዩናል። ሁለቱም ያለፈቃዳቸው ወደ ዓይነ ስውርነትና ሽባነት ተወርውረዋል፤ ይህም በህይወታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ከማሳደር ባሻገር ከማህበረሰቡና ከአለም ጋር ያላቸውን ግንኙነት አዛብቷል። ልቦለዱ ይህንን የመወርወርና የባይተዋርነት ስሜት በሰፊው ያሳየናል።

## 3.7.4.2 ባይተዋርነት በ"የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ"

በርጠሎሜዎስ ከልጅነቱ ጀምሮ ዐይነ ስውር ነበር። ከዚህ በፊት ስለዓለም የነበረው እውቀት በዙሪያው በነበሩት ሰዎች የእውቀት አድማስ የተወሰነ ነበር። ከሚሰማው ውጭ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ከእለታት አንድ ቀን የናዝሬቱ ኢየሱስ በአጠገቡ እያለፈ መሆኑን ይሰማል። በዚችም ቅጽበት በርጠሎሜዎስ ድምጹን ከፍ አድርጎ መጮኽ ይጀምራል። "የዳዊት ልጅ አድነኝ!" ኢየሱስም ምራቁን ከአፈር ጋር ይለውስና ሲቀባቸው ዐይኖቹ ማየት ይጀምራሉ። ይሁንና የበርጠሎሜዎስ ደስታ ብዙ አልዘለቀም። ባየው ነገር ደስተኛ አይደለም። ዓለም ላይ ያለውን ኢ ፍታሃዊነት ከማየት እውርነትን መርጧል። ታድያ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደግሞ ኢየሱስ ነው። በርጠሎሜዎስም ዐይነ ስውርነቱን ይመልስለት ዘንድ ኢየሱስን ፍለጋ ገባ።

በርጠሎሜዎስ ከዚህ በፊት ስለዓለም የነበረው እውቀት በዙሪያው በነበሩት ሰዎች የእውቀት አድማስ የተወሰነ ነበር። ከሚሰማው ውጭ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

> በጨለማው ጊዜ የማውቀውን መንደሩን፣ ምኩራቡን ሁሉ በዐይኔ ዐየሁት። በጆሮዬ ብቻ ነበር ለመረዳት የምሞክረው። የታሸገ ስልቻ ውስጥ እኖር እንደነበር ቀጠርኩት። ግን ብዙ አልቆየ መገረሜ፤ ወዲያው ዐይናማ ሆኜ የተፈጠርኩ ያህል ዕውርነቴን እረሳሁት። ሁሉን ነገር ዐየሁት። አቤት ስንት ጉድ ነገር ተፈጥሯል። በዚህ ዓለም ውስጥ መኖር አልፈልግም፤ ባላይ ይሻለኝ ነበር። አሁን ያን የጨለማው ዘመኔን ናፈቅሁ። ፈጽሞ መታወር እፈልጋለሁ። ዳንኤል (2007፣ 38)

ይህ ጥቅስ የበርጠሎሜዎስን የመጀመሪያ ግብረ መልስ ያሳያል። ነገር ግን ይህ ደስታ ብዙ አይዘልቅም። የሚያየው ዓለም በክፋት፣ በኢፍትሃዊነትና በውሸት የተሞላች መሆኗ የስነልቦና ቀውስ ውስጥ ይከተዋል። ይህ የሚያሳየው በርጠሎሜዎስ ዓለምን በራሱ ዓይን

ለማየት፣ በራሱ ልምድ ለመረዳት እድል እንዳልነበረው ነው። ይልቁንም በሌሎች ሰዎች አተረጓጎምና ትርክት ላይ ጥገኛ ሆኖ ኖሯል። በርጠሎሜዎስ የሚኖረው ራሱ በገነባው የውሸት ዓለም ውስጥ እንጂ ከእውነተኛው ዓለም ነው።

ኢየሱስ በርጠሎሜዎስን ሲፈውሰው፣ በርጠሎሜዎስ ለረጅም ጊዜ የተመኘውን የማየት ችሎታ ያገኛል። ነገር ግን ይህ አዲስ የማየት ችሎታ በርጠሎሜዎስን ከዓለም ጋር አያቀራርበውም፤ ይልቁንስ የበለጠ ያርቀዋል። የሚያየው ዓለም በክፋት፣ በኢፍትሃዊነትና በውሸት የተሞላች መሆኗ ከፍተኛ የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ይከተዋል። በመጨረሻም በርጠሎሜዎስ ከእውነተኛው ዓለም ይልቅ የቀድሞ ዓይነ ስውርነቱን ይመርጣል። ይህንን የሚያሳየው ለኢየሱስ የሚያቀርበው ልመና ነው።

*ዐይኔን ባጠፋውም ከውስጤ፤ ከመታወሬ በፊት የነበረችን ስለዚች ዓለም ሥዕል መልሼ ላመጣው እንደማልችል ይሄ ሽባ ጓደኛዬ አረዳኝ። ... መሮጥ ነበር የተነፈገው፣ እሱንም አገኘ። ...አሁን ተሯሩጦ ነግዶ ይኖራል። ምንም የተቀማው ህልም የለም። እኔ ግን ፊት የነበረችን ይህችን ዓለም በኅሊናዬ ሳያት የኖርኩትን ነው ያጣሁት። አሁን ደግሜ ራሴን ባሳውር ከመወለዴ ጀምሮ አእምሮዬ ውስጥ የነበረውን ሥዕል ማግኘት እንደማልችል ይህ ሽባው ጓደኛዬ 'አሁን አንድ ጊዜ ዐይተሀል። ታልማት የነበረችውን ዓለም በማየትህ ምክንያት ጠፍታለች። በድጋሚ ብትታወርም መልሰህ ፊት ታልም የነበረውን ልታይ አትችልም።" ብሎ አረዳኝ። ዳንኤል* (2007፣ 38-39)

ይህ የበርጠሎሜዎስ ምርጫ ባይተዋርነት እንዴት ከራስና ከዓለም መገለልን እንደሚያመጣ ያሳያል። በርጠሎሜዎስ ዓለምን እንደ ጨካኝና ኢፍትሃዊ ቦታ በማየቱ ከእውነታው ለመሸሽ ዓይነ ስውርነትን መርጧል። ይህ ከባድ ውሳኔ የሰው ልጅ ከዓለም ጋር ያለውን ግንኙነትና ትርጉም ሲያጣ የሚያደርገውን አሳዛኝ ምርጫ ያሳያል። የበርጠሎሜዎስ ታሪክ ከነገረ ህልውና ፍልስፍና ቁልፍ ጭብጦች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። በርጠሎሜዎስ ልክ እንደ ነገር ህልውና ፍልስፍና ገለጻ፣ ቀድሞ ያልተጻፈ ማንነት ወይም ዓላማ ወደ አለም ተወርውሯል። የዓይነ ስውርነቱ ፈውስ ዓለምን በአዲስ መንገድ እንዲያይ እድል ቢሰጠውም፣ የሚያየው እውነታ ከሚጠብቀው ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም።

## 3.7.4.3 ባይተዋርነት በ“ወይ አዲስ አበባ"

ውበቴ በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚኖሩ፣ በልመና ከሚተዳደሩ ጥቂት ዐይነ ስውራን መካከል አንዱ ነው:: በየመጠጥ ቤቱ፣ በየቤተክርስቲያኑ፣ በየጎዳናውና በየአቅጣጫው እየተመላለሰ በሚያጠራቅማት ትንሽ ሳንቲም ይተዳደራል:: እጅግ በጣም ትሁትና ቅን ሰው ነው:: ይሁንና አንድ ትልቅ ችግር ነበረበት:: እሱም ካልጠጣና ካልሰከረ እንደልቡ መለመን አይሆንለትም:: በዚህም የተነሳ ከመሪዎቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት የለውም:: አንዳንዶቹ ሲሰክር ጠብቀው በመደብደብ ገንዘቡን ይቀሙታል:: በመጨረሻም ውበቴ ገንዘቡን ፈጽሞ ሊቀማው የማይችል፣ ጨዋ፣ ቅንና ታዛዥ ታዳጊ ያገኛል:: ይሄ ታዳጊ ከጎጃም ክፍለ ሀገር ጠፍቶ የመጣ ሲሆን አዲስ አበባ ውስጥ መኖር ከጀመረ የተወሰኑ ወራት ተቆጥረዋል:: ውበቴን በመምራት ለምኖ ከሚያገኘው ሳንቲም በጣም የተወሰነውን ይሰጠዋል::

ልቦለዱ በውበቴ ሕይወት አማካኝነት በድህነት፣ በአካል ጉዳተኝነትና በማህበራዊ ኢፍትሃዊነት የሚሰቃዩ ሰዎች የሚያጋጥማቸውን ባይተዋርነት ያሳያል:: ውበቴ ዓይነ ስውር ስለሆነ ራሱን ችሎ መኖር አይችልም:: ለመለመን መሪ ያስፈልገዋል:: ውበቴ ብዙ ይጠጣል:: መጠጡ ከችግሮቹ ለመሸሽ የሚጠቀምበት መንገድ ነው:: ውበቴ በመጠጥ ራሱን ያደነዝዛል:: ከእውነታው ለመሸሽ ይሞክራል:: የውበቴ መሪዎች ሲሰክር ይደበድቡትና ገንዘቡን ይወስዱበታል:: ይሄ ደግሞ የገጸባህሪውን አቅም አልባነት (powerlessness) እና በዙሪያው የከበቡትን ሰዎች ምግባረ የለሽነት ( normlessness) ያሳያል::

## 3.7.4.4 ባይተዋርነት በ“ቦርጨቅ"

ሰባት ጊዜ ወልዳ ሰባቱም በህጻንነታቸው ሞቱባት:: ለስምንተኛ ጊዜ ጸነሰች:: ይሄኛው ያደገላት መሰለ:: ቆንጆና ጤናማ ህጻን ሆኖ አደገ:: እየቆየ ግን ህመም ያመው ጀመረ:: እናትም ተደናግጣ አዋቂ ጋር ወሰደችው:: አዋቂውም “አዲስ አበባ የሚባል ረሀብና በሽታ የሌለበት ከተማ አለ እዛ ውሰጅው” አላት:: እናትም ልጇን ይዛ አዲስ አበባ ገባች:: ህጻኑም ወደ ጤንነቱ ተመለሰላት:: እናትም እንጨት እየሰበረች፣ ጠላ እየጠመቀች ልጇን አስተምራ አሳደገችው:: በትምህርቱም በርትቶ፣ ጥሩ ሥራ ይዞ፣ ሚስት አግብቶ መኖር ጀመረ:: እናት ስታረጅ የዐይን ብርሃኗን ስታጣ አብራው እንድትኖር ያደርጋል:: ሚስት ግን በዚህ ለውጥ ደስተኛ አልነበረችም:: ከተወለደችለት በኋላም በልጁና በእናቱ መካከል እንዲመርጥ

ትጠይቀዋለች። እናትም "ሀገሬን ጥዬ የጠፋሁት ለልጄ ነው እሱንም የልጅ ፍቅር እናቱን እንዲገፋ ያስገድደዋል። ከማስኮንነው ብጠፋ ይሻላል።" ብላ ቤቱን ጥላ ትጠፋለች።

ዐይነ ስውሯ አሮጊት ቤተክርስቲያን በር ላይ ቆመው ሲለምኑ ይውላሉ። እንደመታደል ሆኖ በሚኖሩበት ሠፈር ሰዉ ሁሉ ይወዳቸዋል። ሴቶች ቡና ያፈሉላቸዋል። አንዱ ባለ ጸጋ ደግሞ ማደሪያ ተሰጥቷቸዋል። ሲያልፉ ሲያገድሙ ደግሞ የሚመራቸው ሰው ሞልቷል።

ይህ ክፍል ደግሞ የባይተዋርነትን ጭብጥ ከነገረ ህልውና ፍልስፍና ጋር እያሰናሰለ ይተነትናል። አሮጊቷ ያሳለፈችው ሕይወት፣ የልጆቿ ሞት፣ ለልጇ የከፈለችው መስዋዕትነት፣ በመጨረሻም ከልጇ ቤት መባረሯና በጎዳና ላይ መውደቋ፣ ይህ ሁሉ የሰው ልጅ በሕይወት ውስጥ ሊያጋጥመው የሚችለውን ትርጉም ማጣት፣ ተስፋ መቁረጥና ከዓለም መገለልን ያሳያል።

የእናትነት ትርጉምና መስዋዕትነት

አሮጊቷ ሰባት ልጆች ወልዳ በሕፃንነታቸው በሞት በማጣቷ ከባድ የስሜት ቀውስ አሳልፋለች። ስምንተኛው ልጇ ሲወለድ ግን በሕይወት እንዲተርፍ ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች። ይህ ጥረትና መስዋዕትነት የእናትነት ፍቅርን ጥልቀት ያሳያል።

"ይኸውልህ፣ ሰባት ወለድኩና ሰባቱም ሞቱ። ስምንተኛ እንደወለድኩ... አዲሳባ 'ሚሉት አገር ሂጂ፣ እዚያ ሞት የለም፣ አሉኝ።" ስብሃት (2004፣ 63)

ይህ ጥቅስ የአሮጊቷን ተስፋና ለልጇ የከፈለችውን መስዋዕትነት ያሳያል። ልጇን ለማዳን ስትል ከቤተሰቦቿና ካገሯ ተለይታ ወደማታውቀው ከተማ ለመሄድ ወሰነች።

የልጅ ቸልተኝነትና ባይተዋርነት

አሮጊቷ ልጇ ካደገ በኋላ ሚስት አግብቶ ጥሩ ኑሮ ሲመሠርት ከእርሱ ጋር ትኖራለች። ነገር ግን የልጇ ሚስት አሮጊቷን እንደ ሸክም በመቁጠር ከቤት እንድትወጣ ታስገድዳታለች። ይህ ድርጊት አሮጊቷን ወደ ከፍተኛ ብቸኝነትና ባይተዋርነት ይከታታል።

> "ዋ ልጄ! ... ባል ልጁን መውደዱን እርግጠኛ ከሆነች በኋላ፣ እቺን አሮጊት ካላስወጣህልኝ ፍታኝ አለችው።"

“እና አስወጣዎት?“

“እኔ ወጣሁለት ’ንጂ::“ ስብሃት (2003፣ 64)

ይህ አጭር ጭውውት የአሮጊቷን ተስፋ መቁረጥና ባይተዋርነት ያሳያል:: ከልጇ ቤት ከመባረሯ በፊት ያደረገችውን መስዋዕትነት ስናስብ ልባችን በሀዘን ይዋጣል::

የአሮጊቷ ታሪክ ከነገረ ህልውና ፍልስፍና ቁልፍ ጭብጦች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው:: ሕይወቷ በተስፋ መቁረጥ፣ በብቸኝነትና በትርጉም ማጣት የተሞላ ነው:: በሕይወቷ ውስጥ የደረሰባት መከራና በመጨረሻም ከልጇ ቤት መባረሯ፣ የሰው ልጅ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥመውን ትርጉም ማጣት፣ ተስፋ መቁረጥና ከዓለም መገለልን በግልጽ ያሳያል:: አሮጊቷ ያሳለፈችው ሕይወት የነገረ ህልውና ፍልስፍና ማዕከላዊ ጥያቄ የሆነውን “የሰው ልጅ ሕልውና ትርጉም ምንድን ነው?“ የሚለውን ጥያቄ እንድናስብ ያስገድደናል::

## 3.7.4.5 ባይተዋርነት በ“እራትና መብራት”

የበዕውቀቱ ሥዩም “እራትና መብራት“ ፣ በአንድ ዓይነ ስውር ሽማግሌና በልጅ ልጁ መካከል ያለውን ግንኙነት በመመርኮዝ የነገረ ህልውናዊ ባይተዋርነትን ያሳየናል:: ሽማግሌው በልጅ ልጃቸው ላይ ባላቸው ጥገኝነት ምክንያት የብቸኝነት፣ የፍርሃትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት ያጋጥማቸዋል::

እራትና መብራት፡ ተምሳሌታዊ ትርጉም

“እራት“ና “መብራት“ የሚሉት ቃላት በልቦለዱ ውስጥ ተምሳሌታዊ ትርጉም አላቸው:: “እራት“ የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልገውን መሰረታዊ ፍላጎት ያመለክታል:: ሽማግሌው እራት ለማግኘት በልጅ ልጃቸው ላይ ጥገኛ ናቸው:: “መብራት“ ደግሞ ተስፋን፣ እውቀትንና መመሪያን ያመለክታል:: ሽማግሌው በዓይነ ስውርነታቸው ምክንያት መብራት የሚሆን ሰው ያስፈልጋቸዋል:: የልጅ ልጃቸው ለእነሱ ሁለቱንም - እራትና መብራት - ያቀርባል::

የነጻነት እጦትና ባይተዋርነት

ሽማግሌው ዓይነ ስውር በመሆናቸው ነጻነታቸውን አጥተዋል፡፡ ይህ የነጻነት እጦት በውስጣቸው የባይተዋርነት ስሜትን ይፈጥራል፡፡

ምርጫና የነገረ ህላዌ ኃላፊነት

የልጅ ልጁ ነፃ ነው፡፡ ሽማግሌውን መርዳት ወይም ጥሎ መሄድ ይችላል፡፡ ይህ ምርጫ የነገረ ህልውናዊ ኃላፊነትን ያመለክታል፡፡ ልጁ ሽማግሌውን በመርዳት ሕይወታቸውን ትርጉም ያለው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ጥሏቸው በመሄድ የነሱን ሕይወት ትርጉም አልባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

> "ጥሩ ልጆች የማይሆኑ ልጆች ግን ፈጣሪ ይቀጣቸዋል፡፡ በምድር ላይ ረሀብተኞችና ተቅበዝባዦች ይሆናል፡፡ አይወልዱም አይከብዱም፡፡
>
> አንድ ልጅ አያቱን ከድቶ ተሆነ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር 'በእርጅና ዘመኑ የታወረውን አያትህን ለምን ከዳህ?' ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ልጁም የሚመልሰው አይኖረውም፡፡ ተዚያማ... ሲያል መግባት ዕጣ ክፍሉ ይሆናል፡፡ በዕውቀቱ (1995፣ 101)

ሽማግሌው ልጁን ለማባበል የሚጠቀሙበት የገሃነም ዛቻም የነሱን ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ያሳያል፡፡ የዝምበላቸው አደጋ የሽማግሌው ፍርሃት ነጸብራቅ ነው፡፡ የዝምበላቸው ታሪክ የሽማግሌውን ፍርሃት አባብሶታል፡፡ ሽማግሌው ልጅ ልጃቸው ጥሏቸው ቢሄድ ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል በማሰብ ይጨነቃሉ፡፡

"እራትና መብራት" የነገረ ህልውናዊ ባይተዋርነትን ጭብጥ በተለያዩ ገጽታዎች ያሳያል፡፡ ሽማግሌው የሚያጋጥማቸው የብቸኝነት፣ የፍርሃትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት የሰው ልጅ በሕይወት ውስጥ ስላለው ትርጉምና ዓላማ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡ "እራትና መብራት" የሚሉት ተምሳሌታዊ ቃላት የሰው ልጅ ለመኖርና ትርጉም ለማግኘት የሚያደርገውን ትግል ያመለክታሉ፡፡ ልቦለዱ በመጨረሻ የሰው ልጅ በነጻነትና በኃላፊነት የተሞላ ሕይወት ለመምራት የሚያደርገውን ዘላለማዊ ፍለጋና በዚህ ፍለጋ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ያሳያል፡፡

## 3.8 የአምስቱ ልቦለዶች ጭብጥ

ጭብጥ ማለት፣ ደራሲው በሥነ ጽሑፍ ሥራው ውስጥ በገጸባህሪያቱ የሕይወት ውጣ ውረዶች፣ በድርጊታቸው፣ በውይይታቸውና በሚገጥሟቸው ፈተናዎች አማካኝነት ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ወይም መሠረታዊ ሀሳብ ማለት ነው። ጭብጥ የሥራው ሁሉ ነፍስና ማዕከላዊ ማጠንጠኛ ነው። በዚህ ጥናት የተመረጡት አምስቱ አጫጭር ልቦለዶች፣ ምንም እንኳ በተለያዩ ደራሲያንና በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ ቢሆኑም፣ ዐይነሥውርነትን እንደ ማጠንጠኛ በመጠቀማቸው፣ በጋራ የሚዳስሷቸውና የሚጋሩዋቸው ጭብጦች አሏቸው።

በአምስቱ ልቦለዶች ትንተና መሠረት፣ ደራሲያኑ በዋናነት ሁለት መሠረታዊ ጭብጦችን አንስተዋል። የመጀመሪያውና በሁሉም ሥራዎች ውስጥ በግልጽ የሚታየው፣ ዐይነሥውርነት የሚያስከትለው 'ጥገኝነት' እና ማኅበረሰቡ ለዚህ ጥገኝነት የሚሰጠው ምላሽ (ብዝበዛ፣ መገለል፣ ወይም መደጋገፍ) ነው። ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ፣ የብርሃንና የጨለማ ፍልስፍና ሲሆን፣ አካላዊ እይታን (ማየትን) ከልቦና ማስተዋል (ከውስጥ እውቀት) ጋር በማነጻጸር የሚነሳ ጥልቅ ጥያቄ ነው። ይህ ክፍል እያንዳንዱን ልቦለድ በሰፊው በመተንተን እነዚህን ጭብጦች ያብራራል።

## 3.8.1 «ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ» (በተፈራ ይኄይስ) ጭብጥ

የታሪኩ ዋና ጭብጦች በሦስት ነጥቦች ዙሪያ የተገነቡ ናቸው፡- ጥገኝነትን መጸየፍ፣ መደጋገፍ፣ እና እድል/አጋጣሚ'።

ሀ) ጥገኝነትን መጸየፍ

የዐይነሥውሩ ታሪኩና የሽባው ምንተስኖት የሕይወት ታሪክ በዋናነት የሚያተኩረው "በሌላ ሰው ላይ ሸክም ላለመሆን" በሚለው ስሜት ላይ ነው። የሚገርመው፣ የሁለቱም አካል ጉዳተኝነት የተከሰተው በተፈጥሮ ሳይሆን፣ በልጅነታቸው በወላጆቻቸው ከልክ ያለፈ ፍርሃትና ጥንቃቄ (ታሪኩ ዐይነሥውር የሆነው በወላጆቹ ጥንቃቄ፣ ምንተስኖት ሽባ የሆነው በራሱ ጥንቃቄ ማነስ ነው) ነው። ይህ ሁኔታ፣ ገጸባህሪያቱ ከጥገኝነት አዙሪት ለመውጣት

ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት ያሳያል። ገና በወጣትነታቸው፣ በቤተሰብ ላይ ጥገኛ ሆኖ ከመኖር ይልቅ፣ ክብርን በመምረጥ ያደገበትን ቀዬ ጥለው ይሰደዳሉ።

ልመናን ለጊዜው እንዲሰሩ ቢገደዱም፣ ሁለቱም ገጸባህሪያት ልመናን እንደ ቋሚ የኑሮ መንገድ በፍጹም አይቀበሉትም። ልመና ለእነሱ ከክብራቸው በታች እንደሆነ ስለሚያምኑ፣ በላባቸው ሰርተው ለመብላት ጽኑ ፍላጎት ያሳያሉ። ይህ አስተሳሰብ፣ ልቦለዱ ከሚያስተላልፋቸው ወሳኝ የማኅበራዊ መልዕክቶች አንዱ ነው፤ ዐይነሥውራንና አካል ጉዳተኞች ለኅብረተሰቡ ሸክም መሆንን የማይፈልጉ፣ የራሳቸው ክብርና ጥንካሬ ያላቸው ግለሰቦች መሆናቸውን ያሳያል።

ለ) የጋራ መደጋገፍ እንደ ብቸኛ መፍትሔ

ይህ ልቦለድ ከሌሎች ሥራዎች ሁሉ በላቀ መልኩ የሚያቀርበው ብቸኛ ጭብጥ 'የጋራ መደጋገፍ' (Interdependence) ወይም 'አንዱ ለአንዱ መሆን' የሚለውን ነው። ደራሲው፣ ዐይነሥውርነትንና አካል ጉዳተኝነትን እንደ ውድቀት ሳይሆን፣ እንደ የትብብር መነሻ ተጠቅሞባቸዋል። ዐይነሥውሩ ታሪኩንና ሽባውን ምንተስኖትን በማጣመር፣ አዲስ የሕይወት ቀመር ፈጥሯል፦ ታሪኩ ለምንተስኖት እግር ሲሆን፣ ምንተስኖት ደግሞ ለታሪኩ ዐይን ሆኗል።

የልቦለዱ ርዕስ ራሱ ይህንን የትብብር ፍልስፍና ያውጃል፦ "ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ፤ ላንተ መሪ እሆናለሁ፤ ለኔ ደግሞ መሪ ትሆነኛለህ።" ይህ አቀራረብ፣ በሌሎች ልቦለዶች ውስጥ በስፋት ከሚታየው ብዝበዛና መገለል ፍጹም ተቃራኒ ነው። እዚህ ጋር፣ የአንዱ አካላዊ "ጉድለት" በሌላው ጉድለት ይሞላል። ጥገኝነት፣ የግድ ብዝበዛን ወይም ብቸኝነትን ሳይሆን፣ እውነተኛ ፍቅርን፣ ትብብርንና ሙሉነትን ሊፈጥር እንደሚችል ደራሲው ያሳያል። ይህም፣ ዐይነሥውርነትን እንደ ማኅበራዊ ችግር ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ማኅበራዊ 'መፍትሔ' መነሻ አድርጎ የሚያሳይ፣ ጭብጥ ነው።

ሐ) እድል/አጋጣሚ

ታሪኩና ምንተስኖት ኅብረተሰቡ የለጠፈባቸውን "ለማኝ" የሚል ስም ለማፍረስ ሲሉ በተለያዩ የጉልበት ሥራዎች ላይ ለመሰማራት ይሞክራሉ። በአትክልተኝነት፣ በመኪና መካኒክነት፣ አልፎም በቀለም ቀቢነት ተቀጥረው ይሠራሉ። ይህ፣ ዐይነሥውራን በትምህርት ብቻ

ሳይሆን፣ በአካላዊ ሥራ ራሳቸውን መለወጥ እንደሚችሉ ለማሳየት የተደረገ ጥሩ ሙከራ ነው።

ነገር ግን፣ ደራሲው (ተፈራ ይኄይስ)፣ ይህንን ተጨባጭ የትግል ጭብጥ በገጸባህሪያቱ የላብ ውጤት አያጠቃልለውም። ይልቁንም፣ ታሪኩና ምንተስኖት ስኬት የሚቀዳጁት፣ በኑሮ ተማርረው ራሳቸውን ሊያጠፉ ሲሉ፣ "በአጋጣሚ" ባገኙት የተደበቀ ሀብት ነው። "የጥንት ዘመን ሰዎች... የዕድሜያቸውን ማለፍ አውቀው በድብቅ ደብቀውት የነበረውን ገንዘብ... ታሪኩና ምንተስኖት አገኙት።" ይህ 'ከተአምር የመጣ መፍትሔ' (Deus Ex Machina)፣ የልቦለዱን ተአማኒነት ይጎዳዋል። ስኬት ከጥረታቸው ሳይሆን ከዕድል መምጣቱ፣ በተዘዋዋሪ፣ ዐይነሥውራን በሥራ ብቻ ሊለወጡ አይችሉም የሚለውን የተዛባ አመለካከት የሚያጠናክር ይሆናል።

ይሁን እንጂ፣ ታሪኩ ይህንን በዕድል ያገኘውን ሀብት፣ ተመልሶ ኅብረተሰቡን ለመለወጥ (ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤትና ቤተክርስቲያን ለማሠራት) መጠቀሙ፣ ለጭብጡ ሌላ ገጽታ ይሰጣል። ይህም፣ ዐይነሥውርነቱና መከራው፣ ሀብት ባልሰጠበት ቦታ፣ የሞራል ልዕልናና የማኅበረሰብ ፍቅር እንዳስተማረው ያሳያል። ገጸባህሪው፣ በሌላው ላይ ብርሃን ለመሆን በቆረጠው የልቡ ብርሃን፣ ከሌሎቹ ገጸባህሪያት ተለይቶ "ፍጹም ሰናይ" (Idealized) ሆኖ ቀርቧል።

## 3.8.2 «ወይ አዲስ አበባ» (በአውግቼው ተረፈ) ጭብጥ

ይህ ልቦለድ፣ በንጽጽር ሲታይ፣ የዐይነሥውርነት ጥገኝነት ከሚያስከትላቸው አስከፊ ማኅበራዊ መስተጋብሮች መካከል አንዱ የሆነውን 'ብዝበዛን' በግልጽ ያሳያል። የታሪኩ ዋና ጭብጦች 'የብዝበዛ ሥርዓት' (Exploitative System)፣ 'ልመና እንደ ኑሮ ስልት' (Survival Strategy)፣ እና 'የሱስ አዙሪት' ናቸው።

*ሀ) ዐይነሥውርነት እንደ የብዝበዛ ሥርዓት አካል*

የልቦለዱ ማዕከላዊ ጭብጥ፣ ዐይነሥውርነት የሚያስከትለው ጥገኝነት እንዴት ወደ "የብዝበዛ ኢኮኖሚክስ" ወይም ሥርዓት እንደሚለወጥ ማሳየት ነው። የዋና ገጸባህሪው የውብቴ

ዐይነሥውርነት፣ በልመና ገበያ ውስጥ ዋነኛ 'መሣሪያው' ነው:: ዐይነሥውርነቱ ሰዎች እንዲያዝኑና ገንዘብ እንዲሰጡት የሚያደርግ ዋና ምክንያት ነው:: ነገር ግን፣ ይህንን መሣሪያ የሚቆጣጠረው ውበቴ ራሱ አይደለም:: ውበቴ፣ በመሪዎቹ የሚበዘበዝ፣ የገቢ ምንጭ ብቻ የሆነ 'ንብረት' ነው::

በመሪውና በዐይነሥውሩ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ የተዛባ የኃይል ሚዛን ያለበት ነው:: የቀድሞ መሪው፣ አዲሱን መሪ ሲያስጠነቅቀው የብዝበዛውን ጥሬ እውነት ያጋልጣል፦ "እኔን ደግሞ ገንዘቤን ነጥቆ ሲገርፈኝ ከርሞ ነው::" ይህ ንግግር፣ ውበቴ ጥገኛ በመሆኑ፣ በገንዘብም በጉልበትም እየተበዘበዘ እንደሚኖር ያሳያል:: ዐይነሥውርነቱ፣ ከጥቃት ከመከላከል ይልቅ፣ ለጥቃትና ብዝበዛ ይበልጥ ያጋለጠው ስስ ብልቱ ሆኗል:: ኅብረተሰቡ ዐይነሥውራንን የሚያያቸው፣ የሰብዓዊ መብት ያላቸው ግለሰቦች አድርጎ ሳይሆን፣ ለሌሎች የሚበዘበዙ 'የምጽዋት መሣሪያዎች' አድርጎ መሆኑን ደራሲው በግልጽ ያሳያል::

ለ) ልመና እንደ ኑሮ ስልት (ተግባራዊነት)

ከ«ምራኝና እንሂድ...» ታሪኩ በተቃራኒ፣ ውበቴ ልመናን በፍጹም አይጸየፍም:: ይልቁንስ፣ ልመናን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍና ከከባድ የጉልበት ሥራ (እንደ ኩሊነት) እንደሚሻል አድርጎ ይቆጥረዋል:: "ይልቅስ እንደ አህያ ከመሸከም፣ ለምኖ መብላት አይሻልም?" በማለት ለመሪው የሚሰጠው ምክር፣ ለኑሮ ያለውን ተግባራዊና የደረቀ አመለካከት ያሳያል:: ውበቴ በልመና አያፍርም፤ ይልቁንም፣ እንዴት አድርጎ ከሰዎች ገንዘብ ማግኘት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል:: ሰዎችን ለማሳመን ምን ዓይነት አለባበስ መልበስ እንዳለበት (አሮጌ ልብስ) መሪውን ይመክራል::

ይህ፣ ዐይነሥውርነት ኅብረተሰቡ በፈጠረው ኢኮኖሚያዊ አጥር ውስጥ ሲገባ፣ ብቸኛ የመኖርያ አማራጭ ሆኖ መቅረቡን ያሳያል:: ልመናው፣ ራሱን ከብዝበዛ ያላቀቀበት ሳይሆን፣ በብዝበዛው ሥርዓት ውስጥ ራሱን አስታርቆ የሚኖርበት የተስፋ መቁረጥ ፍልስፍና ሆኗል::

ሐ) የሱስ አዙሪት

ሦስተኛው ጭብጥ፣ የውበቴን ኢ-ፍጹም ገጸባህሪነት ያሳያል:: ውበቴ የአልኮል ሱሰኛ ነው:: ጥገኝነቱ ድርብ ነው፦ ለመንቀሳቀስ በመሪው ላይ፣ ለመለመን ድፍረት ለማግኘት ደግሞ በአልኮል ላይ ጥገኛ ነው:: ካልጠጣና ካልሰከረ እንደልቡ መለመን አይሆንለትም:: ነገር ግን፣

መስከሩ መልሶ ለብዝበዛ ያጋልጠዋል፤ መሪዎቹ ሲሰክር ጠብቀው ገንዘቡን ይቀሙታል። ይህ፣ ሱስ፣ ድህነትና ጥገኝነት የተሳሰሩበት፣ ለማምለጥ እጅግ አስቸጋሪ የሆነ አዙሪት መኖሩን ያሳያል። ሱሱ፣ የግል ድክመት ብቻ ሳይሆን፣ በሚኖርበት አዋራጅ የልመና ሕይወት የሚደርስበትን የሥነ-ልቦና ጫና መቋቋሚያ ስልትም (Coping Mechanism) ሊሆን ይችላል።

መ) የንቃተ-ህሊናና የዋህነት ቅራኔ

ውበቱ፣ ከጅምላ ፍረጃ (Stereotype) የወጣ፣ ውስብስብ ገጸባህሪ ነው። በአንድ በኩል፣ "ብልህ" (Street Smart) ነው። የፖለቲካ ንቃተ-ህሊና አለው፤ በጃንሆይ ዘመን፣ ትልልቅ ስብሰባዎች ሲኖሩ፣ ለማኞች ተለቅመው ይታሰሩ እንደነበር ያውቃል። ስለዚህም አዲሱን መሪ "የጃንሆይ ብር ይሰጣል ወደሚባልበት ቦታ እንዳትወስደኝ" ሲል ያስጠነቅቃል። ይህ ብልህነቱ ነው። በሌላ በኩል፣ ይህ "ብልህ" ሰው፣ እጅግ የዋህና የልጅ ጥያቄ ይጠይቃል፦ "ሴቶችና ወንዶች በምን ተለይተው ይታወቃሉ?"። ይህ አስገራሚ ጥያቄ፣ ዐይነሥውርነቱ የፈጠረበትን እውነተኛ የዕውቀት ክፍተት ያሳያል። ይህ የብልህነትና የዋህነት ጥምረት፣ ገጸባህሪውን ከ"ፍጹም ሰናይ" ወይም "ፍጹም ክፉ" ጅምላ ፍረጃ አውጥቶ፣ እጅግ ሰብዓዊና ተአማኒ ያደርገዋል።

## 3.8.3 «ራትና መብራት» (በበዕውቀቱ ሥዩም) ጭብጥ

ይህ ልቦለድ፣ ከማኅበራዊ ብዝበዛ ይልቅ፣ ዐይነሥውርነት የሚያስከትለውን ጥልቅ 'የሥነ-ልቦና ጥገኝነት' እና የሕልውና ፍርሃት ከሁሉም ሥራዎች በተሻለ ሁኔታ ይተነትናል። የታሪኩ ዋና ጭብጦች 'ጥገኝነት እንደ ሥነ-ልቦና እስራት'፣ 'የተገለበጠ የኃይል ሚዛን'፣ እና 'የአሁኑን መስዋዕት አድርጎ ለወደፊቱ ብርሃን መታገል' ናቸው።

ሀ) ጥገኝነት እንደ ሥነ-ልቦና እስራት

የልቦለዱ ዋነኛ ጭብጥ፣ ዐይነሥውርነት የሚያስከትለው ጥገኝነት እንዴት ወደ 'ሥነ-ልቦናዊ እስራት' (Psychological Bondage) እንደሚለወጥ ነው። የሽማግሌው ገጸባህሪ ሕልውና፣ ሙሉ በሙሉ የተንጠለጠለው በአንድ የአምስት ዓመት ሕፃን (የልጅ ልጃቸው) ታማኝነት ላይ ነው። የልቦለዱ ድርጊት በሙሉ፣ የዚህ ጥገኝነት አስከፊ የሥነ-ልቦና ጫና ላይ

ያተኩራል። የሽማግሌው ስጋት ረሃብ ወይም ብርድ አይደለም፤ ዋነኛ ስጋታቸው መሪውን ማጣት፣ መከዳትና ብቻውን የመቅረት ፍርሃት ነው።

ይህ ፍርሃት፣ ከስጋት ወደ ድንጋጤ የሚቀየረው፣ የባልንጀራቸውን የዝምበላቸውን ታሪክ ሲሰሙ ነው። ዝምበላቸው፣ ልክ እንደ እሳቸው ዐይነሥውር የነበረ፣ በመሪው (በልጁ) በመከዳቱ ምክንያት፣ "አዳልጦት ወድቆ ጭንቅላቱ ተተርትሮ" መሞቱን ሲሰሙ ነው። ይህ ዜና፣ ለሽማግሌው የራሳቸው የዕጣ ፈንታ ትንቢት ይሆንባቸዋል። "ውስጣቸው በድንጋጤ ተናጠ"። ያቺ ቅጽበት፣ ጥገኝነታቸው የዕለት ተዕለት ኑሮ ሳይሆን፣ በቀላሉ ወደ ሞት ሊቀየር የሚችል አደጋ መሆኑን ይረዳሉ።

ለ) የተገለበጠ የኃይል ሚዛን እና ስውር ብዝበዛ

ይህ የሞት ፍርሃት፣ በእሳቸውና በልጅ ልጃቸው መካከል ያለውን የኃይል ሚዛን ይገለብጣል። ፍቅርና አክብሮት፣ በስውር ድርድርና ሥነ-ልቦናዊ ብዝበዛ ይተካል። የአምስት ዓመቱ ሕፃን፣ ምንም ሳያውቅ፣ በእሳቸው ላይ ፍጹም ሥልጣን እንዳለው ይረጋገጣል። የልጁ የልጅነት ፍላጎቶች– "ለትምህርት ቤት መዋጮ" –በሽማግሌው አእምሮ ውስጥ፣ "ካልገዛሁለት ጥሎኝ ይሄዳል" የሚል የሕልውና ጥያቄ ሆነው ይተረጎማሉ። "ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ 'አንድ ቀን ይገዛልሃል!' ብለው ያዘናጉት ነበር። አሁን ግን ግብራቸውን ለወጡት። እጃቸው ወደ ኪሳቸው ፈጠነ።" ይህ ድርጊት፣ ሽማግሌው የልጁን ታማኝነት ለማረጋገጥ፣ የዕለቱን ልመና በሙሉ ለእሱ ፍላጎቶች ማዋል መገደዳቸውን ያሳያል።

በአሳዛኝ ሁኔታ፣ ጥገኝነቱ ሽማግሌውንም ወደ 'ስውር ተንኮል' (Manipulation) ይገፋቸዋል። ልጁ እንዳይከዳቸው፣ በሃይማኖትና በፈጣሪ ስም ያስፈራሩታል፦ "ጥሩ ልጆች የማይሆኑ ልጆች ግን ፈጣሪ ይቀጣቸዋል። ... ሲያል መግባት ዕጣ ክፍሉ ይሆናል።" ይህ፣ ጥገኝነት ሰለባውን (ሽማግሌውን)፣ ራሱ ሌላውን (ልጁን) በሥነ-ልቦና የሚበዘብዝ አዳኝ እንዲሆን ማስገደዱን ያሳያል። ጥገኝነት፣ ለሁለቱም ወገን እስራት ይሆናል።

ሐ) የአሁኑን መስዋዕት አድርጎ ለወደፊቱ ብርሃን መታገል

የልቦለዱ ርዕስ «ራትና መብራት» ራሱ፣ የጭብጡን ፍልስፍናዊ ትግል ያሳያል። "ራት"፣ ጊዜያዊውን፣ አካላዊውንና የዕለት ፍላጎትን ይወክላል። "መብራት" (በዚህ አውድ፣ ደብተርና እስኪርቢቶ)፣ ዘላቂውን፣ አእምሯዊውንና የወደፊቱን ብርሃን ይወክላል። ሽማግሌው፣

የራሳቸውን አካላዊ ፍላጎት ("ራት") መስዋዕት አድርገው፣ ለልጁ ዘላቂ አእምሯዊ ፍላጎት ("መብራት") ቅድሚያ ይሰጣሉ። ይህ ድርጊት፣ ዐይነ-ሥውርነታቸው የፈጠረባቸውን መከራ በመጠቀም፣ ጥልቅ የሆነ "የልቦና ማስተዋል" (Insight) እንደሰጣቸው ያሳያል። አካላዊ ብርሃን የሌላቸው እኚህ አባት፣ "የትምህርት ብርሃን" ከ"የእራት ጉርስ" የበለጠ ዋጋ እንዳለው ተረድተዋል። አካላዊ ዐይነ-ሥውርነታቸው፣ ከዕለት ጉርስ ባለፈ፣ የትውልድን የወደፊት እጣ ፈንታ እንዲያዩ አስችሏቸዋል። እሳቸው የገቡበት የጥገኝነትና የልመና ጨለማ አዙሪት፣ በልጅ ልጃቸው ተሰብሮ በትምህርት ብርሃን እንዲወጣላቸው ይፈልጋሉ።

## 3.8.4 «ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ» (በስብሐት ገብረ እግዚአብሔር) ጭብጥ

ይህ ልቦለድ፣ በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠረውን 'ስውር ጥገኝነት' እና 'መገለል' ጭብጥ ይዳስሳል። የታሪኩ ዋና ጭብጦች 'ክብርን ከጥገኝነት ማስበለጥ'፣ 'ዐይነ-ሥውርነት እንደ ማኅበራዊ ሸክም' መታየት፣ እና 'የእናትነት መስዋዕትነት' ናቸው።

ሀ) ዐይነ-ሥውርነት እንደ ማኅበራዊና የቤተሰብ ሸክም

ግጭቱ የሚፈጠረው በአሮጊቷና በምራታቸው መካከል ነው። ምራቷ፣ አሮጊቷን የምትጠላቸው፣ ዐይነ-ሥውር በመሆናቸው ምክንያት በቤት ውስጥ "ምርታማ" ባለመሆናቸው ነው። አሮጊቷ እራሳቸው፣ ዐይነ-ሥውርነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዋጋቸውን እንዳሳጣቸው ያምናሉ፡- "ከንግዲህ ምን ልረባ? ለራሴ አሮጊት! ቤት ከማጣበብ፣ እንጀራ ከመፍጀት አልፌ ምን ልጠቅማት? አልፈጭላት፣ አልጋግርላት።" ዐይነ-ሥውርነት፣ ከኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ውጭ ሲያደርጋቸው፣ ከቤተሰቡ ያገለላቸው ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ምራቷ፣ በእናትና በልጇ መካከል የጥርጣሬና የክፋት አየር በመፍጠር፣ አሮጊቷን "ሸክም" አድርጋ በማየት ከልጇ መለየት ትፈልጋለች። ደራሲው፣ ቤተሰብ የሚመስለው የጋራ ኑሮ፣ በውስጡ እንዴት በኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጥያቄ ምክንያት እንደሚበሰብስና ዐይነ-ሥውራንን እንደ ተጨማሪ ወጪ እንደሚመለከት ያሳያል።

ለ) ክብርን ከጥገኝነት ማስበለጥ

ልክ እንደ ታሪኩ («ምራኝና እንሂድ...» ውስጥ ያለው)፣ የአሮጊቷ ገጸባህሪ ጥገኝነትን እንደ ትልቅ ውርደትና 'ኩነኔ' ይቆጥሩታል። የጥገኝነት ሕይወት የሚፈጥረው ሥነ-ልቦናዊ ጫና፣ በልጃቸው ቤት ውስጥ ምቾት ቢኖራቸውም፣ እንዲያመነቱ አድርጓቸዋል። ምራቷ፣ በልጇና

በእናቱ መሀል አንዱን እንዲመርጥ ስትገፋፋው፣ አሮጊቷ ለልጃቸው ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት ያደርጋሉ። ምርጫቸው፣ በልጃቸው ትዳር ውስጥ መከፋፈልን ከመፍጠርና "ሸክም" ሆኖ ከመኖር ይልቅ፣ ስደትን፣ ብቸኝነትንና ልመናን መቀበል ነው።

"እኔ ወጣሁለት 'ንጂ። ለምን ላስኩንነው? የልጅ ፍቅር አይደል አገሬን... ጥዬ እንድኮበልል ያደረገኝ? እሱንም የልጅ ፍቅር እናቱን እንዲያባርር ያረገዋል አልኩና፣ የገዛ እናቱ ሀጢአት ኩነኔ ከምሆንበት ብዬ፣ ወጥቼ ጠፋሁ" ይህ ንግግር፣ ዐይነሥውርነታቸው የፈጠረባትን ማኅበራዊ መገለል (ሸክም መሆንን)፣ በራሳቸው የክብር ምርጫ (ብቸኝነትን በመቀበል) አሸንፈዋለሁ ብለው እንደሚያምኑ ያሳያል።

ሐ) የእናትነት ፍጹም መስዋዕትነት

ይህ ጭብጥ፣ የአሮጊቷን ገጸባህሪ 'ፍጹም ሰናይ' (Idealized) ያደርጋል። አሮጊቷ በልጃቸውም ሆነ በምራታቸው ላይ ምንም ዓይነት ምሬት ወይም ቂም አያሳዩም። ይልቁንስ፣ ለልጃቸው ድርጊት መከላከያ ያቀርባሉ። ይህ ፍጹም ይቅር ባይነት፣ ገጸባህሪዋን ከእውነተኛ የሰው ልጅ ባህሪ አውጥቶ፣ ወደ ተጋነነ የፍቅርና የመስዋዕትነት ምስል ያቀርባታል። ይህም ሆኖ፣ አሮጊቷ በልመና ሕይወት ውስጥ ሆነውም፣ በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት ላይ በመደገፍ፣ የልጃቸውን ደስታ ከራሳቸው ምቾት አስበልጠው በጽናት ይኖራሉ።

## 3.8.5 «የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ» (በዳንኤል ታዬ) ጭብጥ

ይህ ልቦለድ፣ በዐይነሥውርነት ዙሪያ ካሉት ሥራዎች ሁሉ ፍጹም የተለየና ሥር-ነቀል (Radical) ፍልስፍናዊ ጭብጥ ያቀርባል። ታሪኩ፣ ዐይነሥውርነት ስለሚያስከትለው ማኅበራዊ ጥገኝነት (በርጠሎሜዎስ ከመፈወሱ በፊት ለማኝ ነበር) ሳይሆን፣ ማየትና አለማየት ስለሚወክሉት ጥልቅ ትርጉም ነው። የልቦለዱ ዋና ጭብጥ 'የብርሃንና የጨለማን ትርጉም መገልበጥ' ሲሆን፣ ይህም "አካላዊ ብርሃን እንደ ውስጣዊ ጨለማ" እና "ዐይነሥውርነት እንደ ሰላም" የሚሉ ሐሳቦችን ያመነጫል።

ሀ) አካላዊ ብርሃን እንደ ውስጣዊ ጨለማ

የልቦለዱ ማዕከላዊ ፍልስፍናዊ ጭብጥ 'የተለመደውን የብርሃንና ጨለማ ዘይቤ (Metaphor) መገልበጥ' ነው። ለበርጠሎሜዎስ፣ አካላዊ "ጨለማ" (ዐይነሥውርነቱ)፣ ሰላምና ንጽህና

የነበረበት ጊዜ ነው። ዐይነሥውር በነበረበት ዘመን፣ ዓለምን በምናቡ የሳለው እንደ ንጹሕ፣ ቅንና ውብ ቦታ አድርጎ ነበር። በጆሮው በሚሰማውና በልቡ በሚያልመው ዓለም ውስጥ ሰላም ነበረው።

ነገር ግን፣ "ብርሃን" (አካላዊ ማየት) ሲያገኝ፣ ይህ ሰላም ይወገድበታል። አካላዊ ዐይኑ በበራ ጊዜ ያየው ዓለም፣ በውሸት፣ በክፋት፣ በኢ-ፍትሐዊነት፣ በስስትና በግብዝነት የተሞላ ሆኖ አገኘው። አካላዊ ብርሃን፣ የገሃዱን ዓለም አስከፊ 'እውነት' ገለጠለት። ይህ አስከፊ እውነት ደግሞ፣ በጨለማ ሳለ የነበረውን 'ህልም' (የመንፈስ ብርሃኑን) አጠፋበት።

በመሆኑም፣ በርጠሎሜዎስ ማየትን ይጠላል፤ ፈውሱን ይረግማል፤ ወደ ቀድሞ ዐይነሥውርነቱ፣ ወደ "ጨለማ" ቤቱ ይመኛል። "አሁን ያን የጨለማው ዘመኔን ናፈቅሁ። ፈጽሞ መታወር እፈልጋለሁ።... በዚህ ዓለም ውስጥ መኖር አልፈልግም። ባላይ ይሻለኝ ነበር።... በጨለማ ውስጥ አየው የነበረውን ህልሜ ይሻለኛል።" ይህ፣ እኛ 'ዐይናማ' የምንለው ዓለም፣ በሥነ ምግባር የታወረ ዓለም መሆኑን የሚጠቁም ጥልቅ ፍልስፍና ነው። በርጠሎሜዎስ፣ አካላዊ ዐይን ሲያገኝ፣ የነበረውን "የልቦና ዐይን" (ንጽህናውንና ሰላሙን) አጥቷል። ስለዚህም፣ ኢየሱስን ፍለጋ የገባው፣ ፈውሱን እንዲቀለብስለትና ዐይነሥውርነቱን እንዲመልስለት ለመለመን ነው።

ለ) የእምነት ኢ-ፍጹምነት

ይህ ጭብጥ፣ ከማየት ፍልስፍናው ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው። በርጠሎሜዎስ በታሪኩ ውስጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጀግና፣ በፍጹም እምነት የተፈወሰ አይደለም። ገጸባህሪው ራሱ፣ ለፈውስ ያነሳሳው እምነት ሳይሆን 'ማቀባጠር' እና 'ሰውን መከተል' መሆኑን ይመሰክራል። "ሲያቀብጠኝ ነው የጮኽኩት፤ ሰው ሲያደርግ ዐይቼ"። ከፈውሱ በኋላም፣ እምነቱ ፍጹም ሳይሆን፣ በጥርጣሬ የተሞላ ነው። "'እምነትህ አድኖሃል' ሲለኝ አመንኩ።... 'ያን ያክል እምነት አልነበረኝም፤ በእምነቴ ነው የዳንኩት?' አልኩኝ።" ይህ ጥርጣሬና ጸጸት፣ ገጸባህሪውን ከ"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጀግና" አውጥቶ፣ ወደ ተጠራጣሪ፣ ተጸጸታችና ኢ-ፍጹም ሰው ይለውጠዋል። ይህም፣ ታሪኩ ስለ 'ጭፍን እምነት' (Blind Faith) በራሱ ላይ የቀረበ ትችት እንዲሆን ያደርገዋል።

## 4. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በአምስት የተመረጡ የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች (“ምራኝና እንሂድ እኔ አንተን አዝዬ ማሙዬ፤“ “የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ፤“ “እራትና መብራት”፣ “ወይ አዲስ አበባ፤“ እና “ቦርጨቅ“) ውስጥ የተቀረጹ ዐይነ ስውራን ገጸባህሪያትን አሳሳል በጥልቀት መርምሯል። የጥናቱ ዋና ዓላማ፣ ደራሲያኑ እነዚህን ገጸባህሪያት ሲስሉ የተጠቀሟቸውን ቴክኒኮች መገምገም፣ በገጸባህሪያቱ አሳሳል ውስጥ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት፣ እንዲሁም በሥነ ጽሑፉ ውስጥ ዐይነ ሥውርነት እንደ ጭብጥ የተቀረጸበትን መንገድ መተንተን ሲሆን፣ ይህንን ዓላማ ለማሳካት፣ ጥናቱ በሦስት መሠረታዊ የስነ ጽሑፍ የሂስ መመዘኛዎች ላይ አተኩሯል፤ እነሱም የገጸባህሪያት ግለወጥነት (Individuality)፣ የባህሪ ዘላቂነት (Consistency) እና ኢ-ፍጹምነት (Imperfection) ናቸው። በተጨማሪም፣ በአምስቱ ገጸባህሪያት መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት በማነጻጸር እና ልቦለዶቹ የሚያነሷቸውን ማዕከላዊ ጭብጦች በመተንተን አጠቃላይ ግኝቶቹን አጠናቅሯል።

በአምስቱም ገጸባህሪያት አሳሳል ውስጥ ጠንካራ ግለወጥነትና የባህሪ ዘላቂነት ተስተውሏል። እያንዳንዱ ገጸባህሪ የራሱ የሆነ ልዩ ማንነት አለው። ለምሳሌ የውብቴ (“ወይ አዲስ አበባ“) ግለወጥነት፣ ዐይነ ሥውርነትንና ልመናን እንደ ውርደት ሳይሆን፣ ከጉልበት ሥራ እንደሚሻል ፕራግማቲክ ፍልስፍና አድርጎ መቀበሉ ላይ ነው። የሽማግሌው (“እራትና መብራት“) ግለወጥነት ደግሞ፣ በመሪ የመከዳት ጥልቅ የሕልውና ፍርሃት ላይ የተገነባ ሲሆን፣ ይህን ፍርሃቱን ለማስወገድ የሚጠቀመው “ስውር ተንኮል“ (ልጁን በሲያል ማስፈራራት) የእሱ ልዩ አሻራ ሆኗል። የበርጠሎሜዎስ (“የጢሞቴዎስ ልጅ...“) ግለወጥነት ከሁሉም ሥር-ነቀል ሆኖ፣ ዐይነ ሥውርነትን እንደ “ሰላም“፣ ማየትን ደግሞ እንደ “ስቃይ“ በመቁጠር፣ ፈውሱን መጥላቱና ወደ ዐይነ ሥውርነቱ ለመመለስ መመኘቱ ነው። የታሪኩ (“ምራኝና እንሂድ...“) እና የአሮጊቷ (“ኤሲን ድንጋይ...“) ግለወጥነትም፣ በተመሳሳይ፣ “ሸክም ላለመሆን“ በሚል ጠንካራ የክብር አቋም ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህ መሠረታዊ አቋሞቻቸው በታሪኩ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች ተቋቁመው በዘላቂነት ታይተዋል። ለምሳሌ፣ የሽማግሌው ፍርሃት የባልንጀራውን ታሪክ ከሰማ በኋላ ባህሪውን በዘላቂነት በመለወጥ (“ግብራቸውን ለወጡት“) እያንዳንዱን ቀጣይ ድርጊቱን እንዲቆጣጠር

አድርጎታል። የታሪኩ ራስን የመቻል ፍላጎት ከቤተሰብ ስደት እስከ ጉልበት ሥራ (መካኒክነት) ድረስ በዘላቂነት ታይቷል። ነገር ግን በአሳሳል ሂደት የተወሰኑ ክፍተቶች ታይተዋል። ለምሳሌ፣ የታሪኩን ግለወጥነት በሚገነባበት ወቅት፣ ደራሲው "ግዙፍና ጠንካራ" አድርጎ መሳሉ፣ በጨለማ ክፍል ውስጥ ታጉሮ ካደገበት የሕይወት ታሪክ ጋር ተአማኒነት ያጣል፤ እንዲሁም ዐይነ ሥውራን "ልዕለ-ሰሚ" ይሆናሉ የሚለው የተለመደ እሳቤ (Compensation Stereotype)፣ በታሪኩ ላይ መንጸባረቁ፣ የግለወጥነቱን ጥንካሬ አዳክሞታል። ከሁሉም በላይ የገጸባህሪያቱን ተአማኒነት የፈተነው መመዘኛ ኢ-ፍጹምነት ነው። በዚህ መመዘኛ፣ ጥናቱ እጅግ ትልቅ የአሳሳል ስኬትና፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ እጅግ ትልቅ የአሳሳል ድክመት ሆኖ ተስተውሏል። የአሳሳል ድክመቱ፣ በሁለት ገጸባህሪያት ላይ የታየው ተአማኒነትን የሚጎዳ "ፍጹም ሰናይነት" (Perfection) ነው። ታሪኩ፣ ምንም ዓይነት የባህሪ ግድፈት የሌለው ሆኖ ተስሏል። ታሪኩ "ፍጹም ቅን"፣ ለጓደኛው መስዋዕት ሊሆን የሚፈልግ፣ እና በመጨረሻም፣ ለገፋው ማኅበረሰብ የህክምና ተቋምና ትምህርት ቤት የሚሠራ እንከን የለሽ ሆኖ ቀርቧል። ይህ፣ ከገሃዱ ዓለም እውነታ የራቀ አሳሳል ነው። አሮጊቷም በተመሳሳይ፣ "ፍጹም እናት" ሆነው ተስለዋል። በልጃቸው ሚስት ምክንያት ከቤት ቢወጡም፣ በልጃቸው ላይም ሆነ በምራታቸው ላይ ምንም ዓይነት ምሬት ወይም ቂም አያሳዩም፤ ይልቁንስ፣ ለልጃቸው ድርጊት መከላከያ ያቀርባሉ ("እሱንም የልጅ ፍቅር…")። ይህ ፍጹም ይቅር ባይነት፣ ገጸባህሪዋን ከሰውነት ይልቅ ወደ "ቅድስት" ደረጃ ያቀርባታል። ይህ አሳሳል፣ ደራሲያኑ (ተፈራ ይኄይስ እና ስብሐት ገ/እግዚአብሔር)፣ ገጸባህሪያቸውን ከ"ምስኪን" ጅምላ ፍረጃ ለማውጣት ሲሞክሩ፣ ወደ ተቃራኒው ጫፍ በመሄድ "ፍጹም ሰናይ" (Idealized) እንዳደረጓቸው ያሳያል፤ ይህም ተአማኒነታቸውን ያደበዝዘዋል። በተቃራኒው፣ ጥናቱ በሦስቱ ገጸባህሪያት (ሽማግሌው፣ ውብቱ፣ በርጠሎሜዎስ) ላይ፣ እጅግ ተአማኒነት ያለው፣ ሰብዓዊ ኢ-ፍጹምነት አግኝቷል። ሽማግሌው ኢ-ፍጹም ናቸው፣ ምክንያቱም ድርጊታቸው (ለልጁ ገንዘብ መስጠት)፣ ከንጹሕ ልግስና ሳይሆን፣ ከራስ ወዳድ የህልውና ፍርሃት እና ከተንኮል (ልጁን በሲያል ማስፈራራት) የመነጨ ነው። ውብቱ፣ በግልጽ፣ "ኢ-ፍጹም" ነው። ምስኪን ተረጂ ብቻ ሳይሆን፣ የአልኮል ሱሰኛ፣ "ርጉም ሰው"፣ አልፎ ተርፎም የቀድሞ መሪውን እንደሚመሰክረው "ገንዘቡን ነጥቆ የሚገርፍ"፣ ማለትም "በዳይ" (Abusive) ነው። ደራሲው፣ ዐይነ ሥውርን እንደ በዳይ አድርጎ መሳሉ፣ ከ"ምስኪን" ጅምላ ፍረጃ ያወጣዋል። ከዚህም በላይ፣ "ብልህ" ሆኖ ሳለ፣ "ሴቶችና ወንዶች በምን ይለያያሉ?"

ብሎ መጠየቁ፣ ዐይነ ሥውርነቱ የፈጠረበትን እውነተኛ የዕውቀት ክፍተት በማሳየት፣ ገጸባህሪውን እጅግ ሰብዓዊ ያደርገዋል። የበርጠሎሜዎስ ኢ-ፍጹምነት፣ ከሁሉም የላቀና ፍልስፍናዊ ነው። የእሱ ትልቁ ድክመት፣ ለፈውስ ያነሳሳው እምነት ሳይሆን "ማቀባጠር" እና "ሰውን መከተል" ("ሲያቀብጠኝ ነው የጮኽኩት፤ ሰው ሲያደርግ ዐይቼ") መሆኑ ነው። ከፈውሱ በኋላም፣ እምነቱ ፍጹም ሳይሆን፣ በጥርጣሬ የተሞላ ("ያን ያክል እምነት አልነበረኝም") መሆኑ፣ ገጸባህሪውን ከ"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጀግና" አውጥቶ፣ ወደ ተጠራጣሪ፣ ተጸጸታችና ኢ-ፍጹም ሰው ይለውጠዋል።

ገጸባህሪያቱን ስናነጻጽር፣ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተመሳስሎ፣ በስነልቦናዊ ግብራቸው ደግሞ ጉልህ ልዩነት ተመልክተናል። በአምስቱም ገጸባህሪያት መካከል የሚታየው ዋነኛ፣ ጉልህ እና ወጥ የሆነ ተመሳስሎ ሁሉም በሕይወታቸው በአንድም ሆነ በሌላ ወቅት በልመና ሥራ ላይ ተሰማርተው መገኘታቸው ነው። ይህ ነጥብ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ዐይነ ሥውራን ገጸባህሪያት እንዴት በጅምላ እንደሚፈረጁ (Stereotyped) የሚያሳይ የጥናቱ ትልቅ ግኝት ነው። ሽማግሌው፣ ውብቴ፣ አሮጊቷ እና በርጠሎሜዎስ ዋነኛ መተዳደሪያቸው ልመና ነው። ከዚህ ጅምላ ፍረጃ ለመውጣት የሚሞክረው ብቸኛው ገጸባህሪ ታሪኩ ነው፤ እሱ ልመናን "የጥገኝነት ስሜት" በማለት አጥብቆ ይጸየፋል። ነገር ግን፣ የዚህ ጥናት ትንተና እንደሚያሳየው፣ የታሪኩ ከችግር መውጣት ተአማኒነት የጎደለው ነው። ታሪኩና ጓደኛው ከድህነት የተላቀቁት በሠሩት የጉልበት ሥራ (እንደ አትክልተኝነት፣ መካኒክነት) ሳይሆን፣ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሲሉ "በአጋጣሚ" ባገኙት ተዝቆ የማያልቅ የተደበቀ ሀብት ነው። ይህ የሴራ አቀራረብ፣ በተጨባጩ ዓለም ዐይነ ሥውራን በሥራ ራሳቸውን ሊለውጡ እንደሚችሉ ከማሳየት ይልቅ፣ መፍትሔው በተአምር ወይም በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ዕድል ላይ የተመሠረተ እንዲመስል ያደርገዋል። ይህም፣ በተዘዋዋሪ፣ ደራሲው ራሱ ዐይነ ሥውር ገጸባህሪው በገሃዱ ዓለም በሚታወቅ የሥራ መስክ ተሰማርቶ እንዲሳካለት ለማድረግ መቸገሩን ያሳያል። በመሆኑም፣ ከአምስቱም ደራሲያን ውስጥ አንዳቸውም ዐይነ ሥውር ገጸባህሪን ከልመና ውጭ በሆነ ተጨባጭና ተአማኒነት ባለው የሥራ መስክ ላይ አሰማርተው፣ በዚያው እንዲጸናና እንዲሳካ አድርገው ለመሳል አለመቻላቸው፣ በጥናቱ ውስጥ የተገኘ ትልቅ የአሳሳል ድክመትና የጋራ ተመሳስሎ ነው። የገጸባህሪያቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ (ልመና) ቢመሳሰልም፣ ለዚህ ሁኔታ የሚሰጡት ሥነ ልቦናዊ ምላሽና ያላቸው አመለካከት ግን እጅግ የተለያየ ነው። ይህም፣ ደራሲያኑ "ዐይነ ሥውርነት"ን እንደ

አንድ ወጥ ስብዕና ሳይሆን፣ በግለሰቦች ላይ ሲከሰት የተለያየ ምላሽ እንደሚፈጥር መረዳታቸውን ያሳያል። ለምሳሌ፣ ታሪኩ እና አሮጊቷ ጥገኝነትን በጽኑ ይጸየፋሉ። ታሪኩ በወጣትነቱ በቤተሰቡ ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖርን በመጸየፍ ይሰደዳል። አሮጊቷም፣ በእርጅና ዘመናቸው፣ በልጃቸው ቤት "ሸክም" ከመሆን ይልቅ፣ ስደትንና ብቸኝነትን በጸጋ ተቀብለው ከቤት ይጠፋሉ። በተቃራኒው ጫፍ ላይ የሚገኘው ውበቴ ነው። ውበቴ ልመናን እንደ ውርደት ሳይሆን፣ እንደ አንድ የሥራ ዘርፍና ከከባድ የጉልበት ሥራ (እንደ ኩሊነት) እንደሚሻል አድርጎ የሚቆጥር ገጸባህሪ ነው። "እንደ አህያ ከመሸከም፣ ለምኖ መብላት አይሻልም?" በማለት ለመሪው የሚሰጠው ምክር፣ ለኑሮ ያለውን ተግባራዊ (Pragmatic) አመለካከት ያሳያል። የሽማግሌው እና የበርጠሎሜዎስ ሁኔታ ደግሞ ከሁለቱም የተለየ ነው፤ ለእነሱ ልመና የፍልስፍና ምርጫ ጉዳይ ሳይሆን፣ በዘመናቸውና በሁኔታቸው ምክንያት፣ ብቸኛው አማራጭ ሆኖ የተቀበሉት ግዴታ ነው። ምንም እንኳ አምስቱም ገጸባህሪያት በልመና አዘቅት ውስጥ ቢገኙም፣ ሌላው ትልቅ ተመሳስሏቸው የሚያሳዩት የማይናወጥ ጽናት ነው። ይህ ጽናት ዝም ብሎ መከራን መቀበል ሳይሆን፣ በችግር ውስጥ ሆነውም ለሌሎች የመትረፍና ዓላማ ያለው ሕይወት የመምራት ጥረት ነው። ሽማግሌው፣ ከራሳቸው የዕለት ጉርስ አልፈው፣ ለመሪ የልጅ ልጃቸው የትምህርት መሣሪያዎችን በመግዛት፣ እሱ ከእሳቸው የተሻለ ሕይወት እንዲኖረው መሠረት ይጥላሉ። ውበቴ፣ በስካርና በሁከት የተሞላ ሕይወት ቢኖረውም፣ በየቀኑ እየተንከራተተ የሚለምነው ቤተሰቡን ለማስተዳደር ነው። ታሪኩ፣ ምንም እንኳ መነሻው ተአምራዊ ቢሆንም፣ ሀብት ካገኘ በኋላ ራሱን ከመፈወስ አልፎ፣ ተወልዶ ላደገበት ማህበረሰብ የህክምና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤትና ቤተክርስቲያን በማሠራት ትልቅ የሞራል ልዕልና ያሳያል። ይህ ጽናት እንዲሁ የተገኘ ሳይሆን "ችግር የወለደው ጽናት" ነው፤ የገጸባህሪያቱ ጥንካሬ የመነጨው ከገጠማቸው ረዳት አልባነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ከሕክምና እጦትና ከጥገኝነት ሰቀቀን ነው።

አምስቱም ደራሲያን ዐይነ ሥውርነትን እንደ ማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ፍልስፍናዊ መነሻ ተጠቅመው ሁለት ማዕከላዊ ጭብጦችን እንደዳሰሱ አረጋግጧል። በአምስቱም ልቦለዶች ውስጥ ከሁሉም በላይ ጎልቶ የወጣው የመጀመሪያው ጭብጥ፣ ዐይነ ሥውርነት የሚያስከትለው 'ጥገኝነት' (Dependency) እና ይህ ጥገኝነት ከማኅበረሰቡ የሚያገኘው ምላሽ ነው። ጥናቱ ይህ ምላሽ በአብዛኛው አስከፊ እንደሆነ አሳይቷል፤ ጥገኝነት፣ ገጸባህሪያቱን ለከፋ 'ብዝበዛ' (Exploitation)፣ ለጥልቅ የሥነ-ልቦና እስራትና ለማኅበራዊ መገለል

ዳርጓቸዋል:: ይህ ጭብጥ በተለይ በ«ወይ አዲስ አበባ» እና «ራትና መብራት» ላይ ጎልቶ ታይቷል:: በ«ወይ አዲስ አበባ»፣ የውበቴ ገጸባህሪ፣ ዐይነሥውርነት እንዴት ወደ "የብዝበዛ ኢኮኖሚክስ" እንደሚቀየር ያሳያል:: ውበቴ፣ በመሪዎቹ የሚበዘበዝ፣ የገቢ ምንጭ ብቻ የሆነ "ንብረት" ነው:: የቀድሞ መሪው፣ ውበቴን "ርኅም" እና "እብድ" አድርጎ በመሳል፣ የራሱን ብዝበዛ ("ገንዘቤን ነጥቆ ሲገርፈኝ") እንደ ትክክለኛ የቁጥጥር እርምጃ ለማቅረብ ይሞክራል:: ዐይነ ሥውርነቱ፣ ከጥቃት ከመከላከል ይልቅ ለጥቃት ይበልጥ ያጋለጠው ስስ ብልቱ ሆኗል:: በ«ራትና መብራት»፣ ጥገኝነቱ ከኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ይልቅ፣ ወደ ከፋ የሥነ-ልቦና እስራት ተለውጧል:: የሽማግሌው ገጸባህሪ ሕልውና፣ ሙሉ በሙሉ የተንጠለጠለው በአንድ የአምስት ዓመት ሕፃን ታማኝነት ላይ ነው:: የባልንጀራቸውን የዝምበላቸውን ታሪክ ሲሰሙ (መሪው ከድቶት ወድቆ እንደሞተ)፣ የራሳቸውም ዕጣ ፈንታ ይሄ መሆኑን ይገነዘባሉ:: ይህ የሞት ፍርሃት፣ በእሳቸውና በልጅ ልጃቸው መካከል ያለውን ግንኙነት ይመርዘዋል፤ የልጁን ታማኝነት ለመግዛት፣ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ይገደዳሉ:: የልቦለዱ ርዕስ «ራትና መብራት» ራሱ፣ ይህንን ጭብጥ ያጠቃልላል:: ሽማግሌው የራሳቸውን አካላዊ ፍላጎት ("ራት") መስዋዕት አድርገው፣ ለልጁ "መብራት" (የትምህርት ቁሳቁስ) ይገዛሉ:: በአሳዛኝ ሁኔታ፣ ጥገኝነቱ ሽማግሌውንም ወደ ተንኮል ይገፋቸዋል፤ ልጁ እንዳይከዳቸው፣ በሃይማኖትና በፈጣሪ ስም ያስፈራሩታል ("ሲያል መግባት ዕጣ ክፍሉ ይሆናል"):: ይህ፣ የጭብጡን አሳዛኝነት ያጎላዋል፤ ጥገኝነት፣ ሰለባውን (ሽማግሌውን)፣ ራሱ ሌላውን (ልጁን) በሥነ-ልቦና የሚበዘብዝ አዳኝ እንዲሆን ያስገድደዋል:: ልቦለዶቹ፣ ከዚህ አስከፊ ጥገኝነት ለማምለጥ የሚደረጉ ሙከራዎችንም ያሳያሉ:: «ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ» እና «ምራችና እንሂድ...» ውስጥ፣ አሮጊቷ እና ታሪኩ ጥገኝነትን እንደ ትልቅ ውርደት ይቆጥሩታል:: አሮጊቷ፣ በልጇ ቤት የነበራትን ምቹ፣ ግን ጥገኛ ሕይወት፣ በክብር ለመለወጥ ትወስናለች፤ በምራቷ ዘንድ "ሸክም" መሆኗን ስትረዳ ("አልፈጭላት፣ አልጋግርላት")፣ ምርጫዋ ከቤት መውጣት ይሆናል:: ታሪኩም፣ በተመሳሳይ፣ "ለወላጆቻቸው ሸክም ሆነው ከመኖር" መሰደድን ይመርጣል:: «ምራችና እንሂድ...»፣ ከዚህም በተጨማሪ፣ የበለጠ ተጨባጭና አዎንታዊ ጭብጥ ያቀርባል፤ እሱም 'የጋራ ጥገኝነት' (Interdependence) ነው:: ልቦለዱ፣ ዐይነ ሥውሩን ታሪኩን ከእግረ ሰላላው (ሽባው) ምንተስኖት ጋር ያጣምራል:: ታሪኩ ለምንተስኖት እግር ሲሆን፣ ምንተስኖት ለታሪኩ ዐይን ይሆናል:: ይህም፣ ጥገኝነት፣ የግድ ብዝበዛን ሳይሆን፣ እውነተኛ ትብብርን፣ መደጋገፍንና ሙሉነትን ሊፈጥር እንደሚችል

ያሳያል። ሁለተኛው ማዕከላዊ ጭብጥ፣ "ማየት" እና "አለማየት" ያላቸውን ጥልቅ ፍልስፍናዊ ትርጉም ይመረምራል። ልቦለዶቹ፣ አካላዊ ብርሃን (ማየት) ከእውቀት ጋር፣ አካላዊ ጨለማ (ዐይነ ሥውርነት) ደግሞ ከድንቁርና ጋር የሚያያይዘውን የተለመደ ዘይቤ (metaphor) ይሞግታሉ፤ አንዳንዴም ሙሉ በሙሉ ይገለብጡታል። ይህ ጭብጥ፣ በ«የጢሞቴዎስ ልጅ በርጠሎሜዎስ» ውስጥ በኃይል ተንጸባርቋል። በርጠሎሜዎስ፣ ዐይነ ሥውር በነበረበት ዘመን፣ ዓለምን በምናቡ የሳለው እንደ ንጹሕ፣ ቅንና ውብ ቦታ አድርጎ ነበር። አካላዊ ዐይኑ በበራ ጊዜ ያየው ዓለም ግን፣ በውሸት፣ በክፋት፣ በኢ-ፍትሐዊነትና በግብዝነት የተሞላ ሆኖ አገኘው። አካላዊ ብርሃን፣ የገሃዱን ዓለም አስከፊ "እውነት" ገለጠለት፤ ይህ አስከፊ እውነት ደግሞ፣ በጨለማ ሳለ የነበረውን "ህልም" (የመንፈስ ብርሃኑን) አጠፋበት። በመሆኑም፣ በርጠሎሜዎስ ማየትን ይጠላል፤ ወደ ቀድሞ ዐይነ ሥውርነቱ፣ ወደ "ጨለማ" ቤቱ ይመኛል። "አሁን ያን የጨለማው ዘመኔን ናፈቅሁ። ፈጽሞ መታወር እፈልጋለሁ።... በጨለማ ውስጥ አየው የነበረውን ህልሜ ይሻለኛል። "ይህ፣ አካላዊ ዐይነ ሥውርነት፣ ከዓለም ክፋትና ብልሹነት የሚጠብቅ "ጋሻ" ወይም "የልቦና ብርሃን" ሊሆን ይችላል የሚል ጥልቅ ሐሳብ ነው። "ብርሃን" እንደ እውቀትና ትምህርት የመተርጎሙ ጭብጥ፣ በ«ራትና መብራት» ውስጥም ተዳስሷል። የሽማግሌው ገጸባህሪ፣ በአካላዊ ጨለማ (ዐይነ ሥውርነት) እና በማኅበራዊ ጨለማ (የጥገኝነት ፍርሃት) ውስጥ ይኖራል። እሱ፣ ከራሱ አካላዊ ጨለማ መውጣት እንደማይችል አምኗል፤ ነገር ግን፣ መሪያቸው (የልጅ ልጃቸው)፣ እሱ ከገባበት የጥገኝነትና የልመና ጨለማ አዙሪት እንዲወጣ ይፈልጋል። የልጁ ከዚህ ጨለማ መውጫ ብቸኛ መንገድ ደግሞ ትምህርት ("ብርሃን") ነው። ሽማግሌው፣ በልጁ ጥያቄ ሲፈተኑ፣ የራሳቸውን አካላዊ ፍላጎት ("ራት") መስዋዕት አድርገው፣ ለልጁ ዘላቂ አእምሯዊ ፍላጎት ("መብራት") ቅድሚያ ይሰጣሉ። ይህ ድርጊት፣ ዐይነ ሥውርነታቸውና የሕይወት መከራቸው፣ ጥልቅ የሆነ "የልቦና ማስተዋል" (Insight) እንደሰጣቸው ያሳያል። አካላዊ ብርሃን የሌላቸው እኚህ አባት፣ "የትምህርት ብርሃን" ከ"የእራት ጉርስ" የበለጠ ዋጋ እንዳለው ተረድተዋል። ይህም፣ ዐይነ ሥውርነት፣ አንዳንዴ፣ ከማየት በላይ ጥልቅ ጥበብን ሊያስተምር እንደሚችል የሚያሳይ ጭብጥ ነው። በማጠቃለያው፣ ይህ ጥናት እንዳሳየው፣ አምስቱም ደራሲያን ዐይነ ሥውራንን ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና አንጻር ሲስሉ፣ በልመና ጅምላ ፍረጃ (Stereotype) ውስጥ ተቀርቅረው ይገኛሉ። ይህ የጥናቱ ትልቁ ግኝትና የአሳሳል ድክመት ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ ውጫዊ

ተመሳስሎ በስተጀርባ፣ ደራሲያኑ የገጸባህሪያቱን ውስጣዊ ዓለም፣ ሥነ ልቦናዊ ምላሽና አመለካከት በተለያየና በበሰለ መንገድ በመቅረጽ ረገድ ተሳክቶላቸዋል። ጽናትን፣ ኩራትን፣ ተንኮልን፣ ፍርሃትንና እምነትን አጣምረው በመያዝ፣ "ዐይነ ሥውርነት" አንድ ወጥ ስብዕና እንዳልሆነ፣ ይልቁንም በችግር የተፈተኑ የተለያዩ ሰብዓዊ ማንነቶች ስብስብ መሆኑን አሳይተውናል። ዐይነ ሥውራን ገጸባህሪያት፣ የዕለት ተዕለት የሕልውና ትግል የሚያደርጉ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ፣ እኛ "ዐይናማ" የምንለውን ዓለም የምንመረምርበት፣ ኅብረተሰቡ ጥገኛ ለሆኑ አባላቱ የሚሰጠውን ምላሽ (ብዝበዛን፣ መገለልን፣ ቸልተኝነትን) በማሳየት የምንተችበት፣ እንዲሁም "እውነተኛ ብርሃን" ምን እንደሆነ የምንጠይቅበት የሥነ ጽሑፍ መሣሪያዎች ሆነው አገልግለዋል።

## ዋቢ ጽሁፎች

ስብሀት ገብረ እግዚአብሔር:: (2003):: *ቦርጨቅ*:: አዲስ አበባ፣ ማኅሌት አሳታሚ::

በዕውቀቱ *ሥዩም*:: (1995):: *በራሪ ቅጠሎች*:: አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት::

ተፈራ ይኄይስ:: (1960):: *ምራኝና እንሂድ ማሙዬ እኔ አንተን አዝዬ*:: አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ማተሚያ ቤት::

አውግቼው ተረፈ:: (2011):: *ወይ አዲስ አበባ* (4ኛ እትም):: አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት::

የኔዓለም ካሳሁን:: (2007):: "በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቀልዶች":: ለኤምኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: (1993):: *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስአበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ዳንኤል ታዬ:: (2007):: *ቅዠት*:: አዲስ አበባ፣ ሲሞፊክ::

ዘሪሁን አስፋው:: (2002):: *የስነጽሁፍ መሰረታውያን*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

Alice Hall. (2016). *Literature and Disability.* Taylor and Francis group. London & New York.

Almaz Abuhay. (2013). “Challenges and opportunities in learning through information communication technology in Addis Ababa University: the case of students with visually impairment”. M.A Thesis, Addis Ababa University.

Aristotle. (1984). Politics (C. Lord, Trans.). University of Chicago Press. (Original work circa 350 BCE).

Bojörk, Lennart, (1994). *“Teaching expository writing” more about writing.* Ed. Karl-Heinz pogner. Odense working papers in language and communication.

Camus, A. (1955). The Myth of Sisyphus (J. O'Brien, Trans.). Vintage Books. (Original work published in French, 1942).

Clinard, Marshal and B. Meier,R.F. (2008). *sociology of deviant behavior (13th ed).* elmont: Thomson Wadsworth.

Durkheim, É. (1951). Suicide: A Study in Sociology (J. A. Spaulding & G. Simpson, Trans.). The Free Press. (Original work published 1897).

Eagleton, T. (1976). Marxism and Literary Criticism. University of California Press.

Eyob, L, T, Y. (2022). *Lived experience of disabled individuals living ib Bahir Dar City, North west Ethiopia, a phenomenological study.* School of Medicine and health sciences, Department of health promotion and behavioural sciences, Bahir Dar University.

Fromm, E. (1994). Escape from Freedom. Henry Holt and Company. (Original work published 1941).

Kierkegaard, Søren. (1980). Fear and Trembling. Translated by Walter Lowrie. Princeton University Press.

Lukács, G. (1971). History and Class Consciousness: Studies in Marxist Dialectics. MIT Press.

Marx, K., & Engels, F. (1846). The German Ideology.

Mindahun, G/ tsadik. (2006). "Employment opportunities of and dissemination against person with disability". Addis Ababa University.

Monbeck, Michael. (1973). *The meaning of blindness: Attitudes towards blindness and blind people.* Bloomington: Indiana university press.

Nietzsche, Friedrich. (1986). *On the Genealogy of Morals*. Carol Diem (Tra). Vintage Books.

Olga, Tarapata. (2018). *Beyond Disability: Extraordinary Bodies in the Work of William Gibson.* University of Cologne, Faculty of Arts and Humanities.

Oliver, M. (1992). *Changing the social relations of research production. Disability, Handicap & Society*, 7, 101-114.

Sartre, Jean-Paul. (2003). "Being and Nothingness: An Essay on Phenomenological Ontology." Hazel E. Barnes (Tra). Routledge.

Tirusew, Tefera. (1994). *Psychological and educational profile of students with disabilities in Addis Ababa university.* Institute of educational research Addis Ababa University.

Tobin Siebers. (2023). *Disability Theory.* The university of Michigan Press.

Weber, M. (1922). "Economy and society: An outline of interpretive sociology". G. Roth C. Wittich, (Eds.). University of California Press.

Williams, R. (1977). Marxism and Literature. Oxford University Press.